# ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

5ኛ ክፍል

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

ISBN ቁጥር -

ዋጋ ብር -

ሥነ-ጥበባት የተማሪ መጽሐፍ 5ኛ ክፍል

# ሥነ-ጥበባት

የተማሪ መጽሐፍ

5ኛ ክፍል



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ

# የጥንቃቄ መልዕክት

## ተማሪዎች!

## ይህን የተማሪ መጽሐፍ በጥንቃቄ ያዙ!

ይህ መማሪያ መጽሐፍ በቀጣይ ዓመት የናንተ ወንድሞችና እህቶች የሚማሩበት የትምህርትቤታችሁ ንብረት ነው! መጽሐፉ እንዳይበላሽ ወይም እንዳይጠፋ በጣም መጠንቀቅ አለባችሁ። መጽሐፉን በጥንቃቄ ለመያዝ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መመሪያዎች ተግባራዊ አድርጉ፤

1. መጽሐፉን ከጉዳት ለመከላከል በላስቲክና በአሮጌ ጋዜጣ ወይም በካኪ ወረቀት ሸፍኑ፤
2. መጽሐፉን ሁልጊዜ ደረቅና ንጹህ በሆነ ቦታ አስቀምጡት፤
3. መጽሐፉን ለመጠቀም ስትዘጋጁ በቅድሚያ እጃችሁ እርጥበት የሌለውና ንጹህ መሆኑን አረጋግጡ፤
4. በመጽሐፉ ሽፋን ወይም የውስጥ ገጾች ላይ አትጻፉ፤
5. መጽሐፉን እያነበባችሁ እያላችሁ ንባባችሁን አቋርጣችሁ እንደገና ለማንበብ ስትፈልጉ ምልክት ማድረጊያ ብጣሽ ወረቀት ወይም ካርድ ተጠቀሙ፤
6. በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ስእሎችን ወይም ገጾችን አትቅደዱ፤
7. በመጽሐፉ ውስጥ የተቀደደ ወይም የተገነጠለ ገጽ ሲኖር በሙጫ ወይም በሌላ ንጹህ ማጣበቂያ ጠግኑት፤
8. መጽሐፉን ከቦርሳችሁ ስታስገቡ ወይም ስታወጡ ጥንቃቄ አድርጉ፤
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታቀብሉም ሆነ ከሌላ ሰው ስትቀበሉ ተገቢውን ጥንቃቄ አድርጉ። ደህንነቱን አረጋግጣችሁ ተቀበሉ።
10. መጽሐፉን ለመጀመሪያ ጊዜ ስትቀበሉ ሽፋኖቹና ገጾቹ እንዳይገነጣጠሉ መጽሐፉን በጀርባው ጋደም አድርጋችሁ አስቀምጡት፤ ከዚያም ጥቂት ገጾችን ቀስ እያላችሁ በየተራ ግለጡ፤ በግራና በቀኝ እጃችሁ የያዛችሁትን የመጽሐፉን ክፍል በኃይል አትጫኑት (አትመንጭቁት)።

**ማሳሰቢያ፤** እነዚህ መመሪያዎች ሳይተገበሩ ቀርተው በመጽሐፉ ላይ አንዳች ጉዳት ከደረሰ በወጣው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ያደርጋል።

# ሥነ-ጥበባት

## የተማሪ መጽሐፍ

## 5ኛ ክፍል


**አዘጋጆች**

አራጋው የሱፍ

ደስታዬ ይርጋ

**አርታኢዎች**

አታላይ መስፍን

ደምሌ አባተ

**ቡድን መሪ**

አሰፋ ሰማው

**ዲዛይነር**

አትርሳው ጥግይሁን



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተመደበ በጀት በአብክመ ትምህርት ቢሮና በምሁራን መማክርት ጉባዔ ትብብር ነው።

የመጽሐፉ ሕጋዊ የቅጂ ባለቤት © 2015 ዓ.ም. አብክመ ትምህርት ቢሮ ነው።



ምሁራን መማክርት ጉባዔ



በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ

# ማውጫ


መግቢያ ..... v

## ምዕራፍ 1

## የሥነ-ጥበባት አለባውያን

1.1 የዕይታዊ ጥበብ አለባዊያን ..... 2
1.1.1 የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን ምንነት ..... 3
1.1.2 የቀለማት ቻርት (ቀለበታዊ ቀለማት) ..... 9
1.1.3 በእይታ ጥበብ አለባዊያን የንድፍ ስዕሎችን መስራት ..... 13
1.1.4 በቀለማት የተለያዩ ስዕሎችን መስራት ..... 15
1.2 መሰረታዊ የሙዚቃ አለባዊያን ..... 16
1.2.1 የኖታዎችና የእረፍት ምልክቶች አጨዋወት ..... 17
1.2.2 ተለዋዋጭ ምልክቶች ..... 23
1.2.3. የሙዚቃ ድምጽ ቃና ..... 24
1.2.4 የድምፆች ስያሜ ..... 25
1.3 የቴያትር መሰረታዊ አለባዊያን ..... 26
1.3.1 የቴያትር ጥበብ ዋና ዋና አካላት ..... 29
1.3.2 ለቴያትር ድርሰት ሀሳብ የሚገኝበት መንገድ ..... 35
1.4 ቀላል የቪዲዮ ቀረጻ ..... 36
1.4.1 የቪዲዮ ምንነት ..... 36
1.4.2 ቪዲዮ በምንቀርጽበት ወቅት ልብ ልንላቸው የሚገቡ ነገሮች ..... 37

## ምዕራፍ 2

## የፈጠራ ችሎታን መግለጽ

2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መፃፍና ማንበብ ..... 45
2.1.1 ዜማን ማንበብ ..... 53
2.2 ኪነ-ጽህፈት ..... 55
2.2.1 የኪነ-ጽህፈት ምንነትና የእጅ ማፍታቻ መስመሮች ጥናት ..... 55
2.2.2 የነጠላ ፊደላትና የቁጥሮች አጻጻፍ ልምምድ ..... 56
2.2.3 የድርብ ፊደላት አጻጻፍ ልምምድ ..... 60
2.3 የወረቀት ሞዛይክና የብሎክ /ሪሊፍ/ ህትመት ..... 64
2.3.1 የሞዛይክ ምንነት፣ መስሪያዎችና አሰራር ..... 64
2.3.2 የወረቀት ሞዛይክ ..... 66
2.3.3 የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመት ..... 67
2.3.4 የድንች ህትመት ..... 69
2.3.5 የሳሙና ሪሊፍ ህትመት ..... 70
2.4 ሞዴሊንግ (በጭቃ) ..... 72
2.4.1 የሞዴሊንግ ተግባር ስራ ..... 72
2.5 ቴያትርን የመስራት ችሎታ ..... 76

2.5.1 የቴያትር ጥበብን ለመስራት መነሻ የሚሆኑ ዋናዋና ነገሮች ..... 76
2.5.2 የቴያትር ፈጠራ ችሎታን ማሳየት ..... 78

## ምዕራፍ 3

## ታሪክና ባህል

3.1 የባህላዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ አይነቶች ..... 85
3.1.1 ባህል እና የባህላዊ ሙዚቃ ..... 85
3.1.2 ባህላዊ ውዝዋዜዎች (ሶፍፈራዎች) ..... 86
3.2 የዋሻ ውስጥ ጥበብ ..... 89
3.2.1 የዋሻ ውስጥ ጥበብ ታሪክ አጀማመር ..... 89
3.2.2 የዋሻ ውስጥ ስዕሎች ..... 90
3.3 የኢትዮጲያ ባህላዊ ጥበባት ታሪክ ..... 93
3.3.1 የባህል ጥበብ (በእይታዊ-ጥበቡና እጅ ስራዎች አንጻር) ..... 93
3.3.2 የባህል ጥበብ ታሪክ (ከሙዚቃ አንጻር) ..... 99

## ምዕራፍ 4

## ጥበብን ማስተዋወቅ

4.1 በስነ ጥበባት ሃሳብ መናገር ..... 108
4.1.1 ልዩነትና ተመሳሳይ ሀሳቦችን በጥበባት መግለጽ ..... 108
4.1.2 በፉከራ፣ በሽለላ /ቀረርቶ/ና ዘፈን የሀሳብ አንድነትና ልዩነትን መግለጽ . ..... 109
4.1.3 በቴያትር ጥበብ የሀሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን መወያየት ..... 112
4.2 የምስል ጥበባት እና የእጅ ስራዎች ለማህበረሱቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ .... 112
4.2.1 የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ምንነት ..... 112
4.2.2 የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ ..... 113

## ምዕራፍ 5

## ሥነ-ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶችና ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር

5.1 ሥነ-ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ማስተሳሰር ..... 119
5.1.1 በሥነ-ጥበባት ተማሪዎች ይዘቶችን በቀላሉ እንዲገነዘቡ ማድረግ . 119
5.2 አሳሳቢና ወቅታዊ ጉዳዮችን ጥበባትን ተጠቅሞ ማስተማር ..... 125
5.3 አርማ እና ፖስተር ..... 130
5.3.1 አርማ ..... 130
5.3.2 ፖስተር ..... 133

# መግቢያ

## ሥርዓተ ትምህርቱን ማዘጋጀት ለምን አስፈለገ?

ከሥርዓተ-ትምህርቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥናት እና ምርምሮች ተካሂደዋል። ከእነዚህም አንዱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት የተካሄደው የትምህርትና ሥልጠና ፍኖተ-ካርታ ጥናት ዋናው ነው። ይህ እና ሌሎችም ተመሳሳይ ርእሶች ዙሪያ የተካሄዱት ጥናትና ምርምሮች ሥርዓተ ትምህርቱ በይዘት የታጨቀ፣ በትምህርት አይነቶች ብዛት የተወጠረ፣ በአብዛኛው ይዘት ማስታዎስን ትኩረት ያደረገ፣ ከተማሪዎችና ከማህበረሰቡ ህይወትና ኑሮ፣ ምርታማነት እንዲሁም ከሀገር በቀል እውቀት ጋር ያልተቆራኘ፣ ተማሪዎች ተገቢውን ግብረገባዊ እውቀትና ክህሎት እንዲላበሱ ያላደረገ፣ በቴክኖሎጂ ያልተደገፈ እና ልዩ ፍላጎትና ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች በተገቢው መንገድ ከማስተናግድ አኳያ ክፍተት ያለበት መሆኑ ተመላክቷል። በተጨማሪም ስርዓተ ትምህርቱ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የሚጠይቀውን እውቀትና ክህሎት ማለትም ለመማር መማርን፣ በጥልቀት ማሰብና ችግር ፈችነትን፣ የፈጠራ አስተሳሰብና አዳዲስ ግኝቶች ማፍለቅን፣ ተግባቦትን፣ ትብብርን፣ መሪነትና ውሳኔ ሰጭነትን፣ የቴክኖሎጂ እውቀትን እና የባህል ማንነትና አለማቀፋዊ ዜግነትን ማስጨበጥ የማይችል መሆኑን በማመላከት የሥርዓተ-ትምህርት መሻሻል እና ለውጥ እንዲካሄድ የሚያመላክቱ ምክረ-ሃሳቦችን ሰንዝረዋል።

ይህንን መነሻ በማድረግም ሰፊ የውይይት እና የምክክር መድረኮች ተዘጋጅተው ህብረተሰቡ እንዲወያይ በማድረግ የለውጥ መርሃ ግብሮች ተቀርፀው ወደ ትግበራ ተገብቷል። ከእነዚህ የለውጥ መርሃ ግብሮች ውስጥ አንዱ አዲስ የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት መቅረጽ ሲሆን ቀደም ሲል የነበሩትን ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የሥርዓተ-ትምህርት ለውጥ ዝግጅት ተድርጓል።

በዚህም መሠረት አዲሱን የአጠቃላይ ትምህርት ሥርዓተ-ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻል በመጀመሪያ ለመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት የሚያግዙ ሰነዶች ማለትም የተማሪው የባህሪ ገጽታ፣ የሥርዓተ-ትምህርት ማዕቀፍ፣ የይዘት ፍሰት፣ ተፈላጊ የመማር ብቃት እና መርሃ-ትምህርቶች እንደ ሀገር ተዘጋጅተዋል። በእነዚህ ሰነዶች መነሻነትም በክልላችን የመጀመሪያ ደረጃ(ከ1ኛ-6ኛ) እና የመካከለኛ ደረጃ(7ኛና 8ኛ) ክፍሎች የየትምህርት አይነቶች የተማሪዎች መማሪያ እና የመምህራን ማስተማሪያ መጽሐፍት ተዘጋጅተዋል።

## የመጻሕፍት አተገባበር

መጽሐፉ ተማሪዎች ከዚህ ቀደም ከሚያውቁትና ከአካባቢያቸው ይዘውት ከሚመጡት ተሞክሮና እውቀት በመነሳት ተግባር ተኮር እና አሳታፊ በሆነ መልኩ እንዲማሩ ሆኖ ስለተዘጋጀ ተማሪዎች ትምህርቱን በጥልቀት ይገነዘቡታል ወይም ይረዱታል ተብሎ ይታመናል። ተማሪዎችና መምህራን አካባቢያቸውን እና ያካበቱትን ዕውቀትና ተሞክሮ መሰረት በማድረግ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የተለያዩ ተግባራትን በአግባቡ በመተግበር ተማሪዎቻችን ይዘቶችን መማር ብቻ ሳይሆን የመማር ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ ይጠበቃል። በመሆኑም መምህራን ለይዘቱ ተስማሚ ተብለው የተጠቆሙ የማስተማሪያ እና መማሪያ ዘዴዎችን በአግባቡ በመተግበርና ሌሎች ተገቢ ዘዴዎችን ተጨባጭ ሁኔታንና የተማሪዎችን አቅምና ፍላጎት መሰረት አድርጎ በመምረጥ ተማሪተኮር /አሳታፊ አድርገው የመማር ማስተማሩን ተግባር መፈጸም የሚጠበቅባቸው ሲሆን ተማሪዎች ደግሞ በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ መጽሐፍቱን ከእጃቸው ሳይለዩ ትምህርቱን መከታተል ይኖርባቸዋል።

## ውድ ተማሪዎቻችን!

መጽሐፉን በጥንቃቄ በመያዝ በአግባቡ መጠቀም አለባችሁ። በማንኛውም አገርና ሁኔታ መማር የትውልድን የወደፊት ሁኔታ ይወስናል። መማር ለማንኛውም ማህበራዊ፣ ሰብዓዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መሰረት ነው። በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ተግባራት፣ ይዘቶችና ጥያቄዎች በአግባቡ በመስራትና በማጥናት ጥልቀት ያለው ክህሎትን እና ግንዛቤን ማዳበር ይገባችኋል።

## ውድ ወላጆች/ አሳዳጊዎች!

የተማሪዎችን መማር የተሳለጠ ለማድረግ የመማሪያ መጻሕፍት ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ስለሆነም ተማሪዎች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዘው እንዲጠቀሙ ማድረግ ይኖርባችኋል። ከዚህም በተጨማሪ ተማሪዎች መጽሐፉን ት/ቤት ይዘው እንዲሄዱ ማበረታታት፣ ከመምህሮቻቸው የሚሰጡ ተግባራትን በትክክል እንዲፈጽሙና እንዲያጠኑ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ትምህርት ቤት በመሄድ ከመምህራን ጋር በመገናኘት ስለ ልጅዎ የመማር ዕውቀትና የባህሪ ለውጥ በመጠየቅ ክፍተቱን በመለየት ምክር በመሥጠት ማስተካከል ይጠበቅባችኋል። በመሆኑም ትምህርት የሁሉም ነገር መሰረት መሆኑን በመገንዘብ መማርን ከመንግስት ስራ መያዝ ጋር ብቻ ሳታቆራኙት/ሳያያይዙት ልጆችን ሁልጊዜ ወደትምህርት ቤት መላክ አለባችሁ።

# ምዕራፍ 1
# የሥነ-ጥበባት አለባውያን

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡**

## ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- የሥነ ጥበባት አለባዊያንን ትለያላችሁ።
- የእይታዊ ጥበብ አለባውያንን በመጠቀም በምስል ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ።
- የሙዚቃ አለባዊያንን በመጠቀም ዜማ ጽፋችሁ ትዘምራላችሁ።
- ቀላል የቪዲዮ ቀረጻ ዘዴዎችን ትረዳላችሁ።
- የሥነ ጥበባት ስራዎችን ታደንቃላችሁ።

## መግቢያ


በዚህ ምዕራፍ ስለ ዕይታዊ ጥበባት ጽንስ-ሀሳብ፣ በውስጡ የሚካተቱ ጥበባትና መሰረታዊ አለባውያን (መስመር፣ ቅርጽ፣ ፎርም፣ ፍካት... ወዘተ)፣ ስለ ሙዚቃ መሰረታዊ አለባውያን (ምት፣ የድምጽ ቃና፣ ተለዋዋጭ ምልክቶች ወዘተ)፣ ስለ ቴያትር አለባውያን (መቼት፣ ገጸ ባህሪ፣ ሴራ፣ የቴያትር ጽሁፍ፣ ጭብጥ...) እና ስለ ቪዲዮ ቀረጻ እንመለከታለን።

ሥዕል፣ ሙዚቃና ቴያትር የሰዎችን ስሜት በተለየ ሁኔታ ማንፀባረቅ የሚያስችሉ ናቸው። ሥነ ጥበባት ሰዎች ደስታን፣ ሀዘንን፣ አድናቆትን፣ ፍቅርና ወዘተ ስሜቶችን ይገልፁባቸዋል። ሥነ ጥበባትን ለመረዳትና ለመተግበር በቅድሚያ የሥነ ጥበባት አለባውያንን ማወቅ አስፈላጊ በመሆኑ መሰረታዊ የእይታዊ ጥበባት፣ የሙዚቃና የቴያትር ጽንስ-ሀሳቦች በምዕራፍ አንድ ተካተዋል።

## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

1.1. የዕይታዊ ጥበባት አለባዊያን
1.2. የሙዚቃ አለባዊያን
1.3. የቴያትር መሰረታዊ አለባዊያን
1.4. ቀላል የቪዲዮ ቀረጻ ቴክኒኮች

## 1.1 የዕይታዊ ጥበብ አለባዊያን




ስዕል 1 የዕይታዊ ጥበባት አለባዊያን ምስል

እይታዊ ጥበባት የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታውን በመጠቀም ሀሳቡን፣ ስሜቱንና ፍላጎቱን የሚገልፅባቸው ናቸው። ንድፍ፣ ቀለም ቅብ፣ ኪነ-ቅርጽ፣ ፎቶግራፍ፣ ህትመት፣ እደ-ጥበባትና የመሳሰሉት ደግሞ የእይታዊ ጥበባት አካል ናቸው። እነዚህ ጥበባት ሰዎች ስለ ዓለም ያላቸውን ስነ-ውበታዊ ግንዛቤ የሚገልጹባቸው፣ ታሪኮችን የሚነግሩባቸው፣ መረጃዎችን የሚመዘግቡባቸው እና ታሪክን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፉባቸው ናቸው። በሌላ በኩል እይታዊ ጥበባት፦

### ሀ. መግባቢያ ቋንቋ ናቸው።

መግባቢያ ቋንቋ ናቸው ሲባል ከሰዎች ጋር ቃላቶችን በመለዋወጥ መግባባት እንደሚቻል ሁሉ በዕይታዊ ጥበባትም መግባባትና ሀሳብ መለዋወጥ ይቻላል።

### ለ. በማየት የምንረዳቸው ናቸው።

በማየት የምንረዳቸው ናቸው ሲባል ደግሞ በቀለም ቅብ፣ ንድፍ፣ ቅርጽ፣ ህትመትና የመሳሰሉት ስራዎች የሰዓሊውን ሀሳብና ስሜት የምንገነዘበው በማየት ላይ ተመስርተን በመሆኑ ነው። በሌላ መልኩ ለእይታዊ ጥበባት መሰረታዊ ነገሮች ያሉ ሲሆኑ እነዚህም አለባዊያን ወይም አናስሮች ተብለው ይጠራሉ። መሰረታዊ የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን የስዕል ስራ በሚሰራበት ወቅት ሰዓሊው የሚጠቀምባቸው ለስዕሉ የጀርባ አጥንት የሆኑና የስዕሉን መልዕክት የሚሸከሙ ናቸው።

የዕይታዊ ጥበባት ስራዎች አንድና ከአንድ በላይ የሆኑ አለባዊያንን (አናስሮችን) የያዙ ናቸው። የዕይታዊ ጥበባት ስራዎች በዋናነት ከመሰረታዊ አለባዊያን ውጭ ሊሆኑ አይችሉም።

## 1.1.1 የእይታዊ ጥበብ አለባዊያን ምንነት

የዕይታዊ ጥበባት አለባዊያን የምንላቸው፦ መስመር፣ ዝርግ ቅርጽ፣ ፎርም፣ ቴክስቸር፣ ቦታ (ስፍራ)፣ ፍካት (ቫሊዩ)፣ ቀለምና የመሳሰሉት ናቸው።

### ሀ. መስመር

መስመር በየትኛውም የሥነ-ስዕል ውጤቶች ውስጥ በዋነኛነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ግብዓቶች አንዱ ሲሆን አንድ ነገር ከሆነ ነጥብ ተነስቶ በሚንቀሳቀስበት ወቅት የሚፈጥረው ምልክት ነው።

መስመር ለሌሎቹ የስዕል አለባዊያን መነሻ የሆነና ከወርዱ ርዝመቱ የሚበልጥ በእንቅስቃሴ የሚፈጠር ምልክት በመሆኑ የትኛውም ዓይነት መስመር ወርድ፣ ርዝመት፣ አቅጣጫና ስሜት አለው።

በስዕል ስራ መሰረታዊ የሀሳብ መግለጫ የሆነው ንድፍን ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና የሚጫዎቱት መስመሮች ናቸው። እነዚህ መስመሮች ርስበርሳቸው ሲገጣጠሙ የሚፈለገውን ቅርጽ ወይም ፎርም ለማግኘት ያስችላሉ። በሌላ

በኩል መስመር ጠርዝን ለመወሰን፣ ፍካትና ቴክስቸርን ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ነው። የትኛውም የመስመር ዓይነት የራሱ የሆነ ባህሪይና ሊገልፃቸው የሚችላቸው ስሜቶችና ሃሳቦች አሉት። በስዕል ትምህርት ውስጥ መሰረታዊ የሚባሉትን የመስመር አይነቶች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. **ቋሚ መስመር**፦ ያለ ምንም ግድለት ከላይ ወደታች የሚወርድና ከታች ወደ ላይ የሚወጣ ነው። ይህ መስመር ከሚፈጥራቸው ስሜቶች ውስጥ ክብር፣ በህይወት መኖር፣ ጥንካሬ፣ ጽናት ተጠቃሽ ናቸው።

ለ. **አግድም መስመር**፦ ጎን ለጎን የሚሄድ መስመር ሲሆን በባህሪው እረፍትን፣ ሰላማዊነትን፣ ጸጥታን የሚያመለክት ነው።


ሐ. **ሰያፍ (ስላሽ) መስመር**፦ ጋደል ያለ መስመር ሲሆን የሚፈጥረው ስሜት ፍጥነትን፣ እንቅስቃሴን፣ መውደቅን ነው።


መ. **ዚግዛግ መስመር**፦ በሰያፍ መስመሮች ቅንጅት የሚፈጠር የመስመር አይነት ሲሆን በባህሪው መፈረካከስን፣ መሰንጠቅን፣ መሰበርን፣ ቁጣን፣ ድርቅናንና ውጣውረድን የሚያሣይ ሲሆን በሚታጠፍበት ወይም በሚሰበርበት ወቅት አንግል የሚፈጥር ነው።

ሠ. **ጎባጣ (ታጣፊ) መስመር**፦ ቀስ በቀስ አቅጣጫን የሚቀይር በባህሪው በዝግታ የመንቀሳቀስ ስሜትን ያሣያል። ለምሳሌ ዳክየዎች በውሃ ላይ ሲሄዱ መርከብ በውሃ ላይ ሲሄድ በተመሳሳይ እነዚህ መስመራቶች የሚታዩ ናቸው።

## ለ. ዝርግ ቅርጽ

ዝርግ ቅርጽ ርዝመትና ወርድ ያለው ነገር ግን ጥልቀት የሌለው በመስመር የተከበበ ቦታ ሲሆን በዚህም ምክንያት ባለ ሁለት አውታር መጠን ነው። መስመሮች እየተገጣጠሙ ሲሄዱ ቅርጽን የሚፈጥሩ ሲሆን ጅኦሜትሪክ እና ኦርጋኒክ (ተፈጥሯዊ) ተብለው በሁለት ይመደባሉ። ጅኦሜትሪክ የምንለው ልኬት ያላቸውና መሳሪያዎችን ተጠቅመን የምንፈጥራቸው ቅርጾች ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል ክብ፣ ካሬ፣ ሬክታንግል እና ጎነ-ሶስት ተጠቃሽ ናቸው። ተፈጥሯዊ ደግሞ ለዛ ያላቸውና ልኬት የሌላቸው ብዙውን ጊዜ በተፈጥሮ የሚገኙ የሰው፣ የእንስሳትና የእጽዋት ቅርጾች ናቸው።




ስዕል 2 መሰረታዊ ጅኦሜትሪካል ዝርግ ቅርጾች እና ተፈጥሯዊ ዝርግ ቅርጾች

## ሐ. ፎርም

ፎርም ባለ ሦስት አውታር መጠን የሆነ ርዝመት፣ ወርድና ጥልቀት ያለው ቅርጽ ነው። በስዕል ትምህርት ውስጥ ፎርም በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ሲሆን እውነተኛ እና ምናባዊ ተብለው ይጠራሉ። እውነተኛ ፎርም ከቦታ ቦታ ሊንቀሳቀስ ወይም ሊቀመጥ የሚችል ማንኛውም ባለ ሦስት አውታር መጠን ነው። ምናባዊ ደግሞ መስመሮችን፣ ቀለምን፣ ቦታንና ቫሊዩን ተጠቅመን ዝርግ በሆነ ሰሌዳ ላይ ለዕይታችን የምንፈጥረው ሦስት አውታር መጠን ነው። በስዕል ውስጥ መሰረታዊ የሚባሉ ፎርሞች ያሉ ሲሆን እነሱም ስፌር፣ ኩብ፣ ሲሊንደር እና ኮን ናቸው።



ስዕል 3 ስፌር፣ ኩብ፣ ኮን እና ሲሊንደር እንደ ቅደም ተከተላቸው

## መ. ቦታ (ስፍራ)

ቦታ (ስፍራ) በስዕል ስራ በሚገኙ አካላት አካባቢ፣ መካከል እንዲሁም ውስጥ የሚገኝ ስፋት ነው። ይህም በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ሲሆን ፖዘቲቭ እና ነጋቲቭ ተብለው ይመደባሉ። ፖዘቲቭ በስዕል ስራው አካሉ (የተቀመጡት ነገሮች) የያዟቸውን ስፋት ሲሆን ኔጋቲቭ ደግሞ በስዕል ስራው አካሉ ከያዘው ውጭ ያለው ማንኛውም ስፋት ነው።



ስዕል 4 ፖዘቲቭ እና ነጋቲቭን

ከላይ እንደምትመለከቱት መቀመጫዎቹ የያዙት ነጩ ክፍል ፖዘቲቭ ሲባል የጠቆረው ደግሞ ነጋቲቭ ነው።

### መልመጃ 1


1. እርሳስን በመጠቀም ቀላል ስዕሎችን ሰርታችሁ የትኛው ፖዘቲቭና የትኛው ነጋቲቭ ስፋት መሆኑን ለመምራችሁ አሳዩ።

## መ. ቴክስቸር

ቴክስቸር ነገሮችን ስንዳስሰ እና ስንመለከት የምናገኘው የመለስለስ ወይም የመሻከር ስሜት ነው። ማንኛውም ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ነገሮች የራሳቸው ቅርጽ እንዳላቸው ሁሉ ቴክስቸር አሏቸው። ለምሳሌ ስንዳሳቸው የለስላሳነት

ስሜት የሚሰጡ መስታውት፣ ጥጥ፣ ለስላሳ ሱፍና የሸካራነት ስሜት የሚሰጡ ደግሞ ቅርፊት፣ የጡብ ግድግዳ፣ ጆንያን ወዘተ መጥቀስ ይቻላል።

በስዕል ስራ ውስጥ የለስላሳነትና የሸካራነት ገጽታን በእርሳስ ወረቀት ላይ ለመግለጽ መስመሮችን በመስቀልኛ መልክ/ በቀጥታና በአግድም እየደራረቡ ወይም ነጠብጣቦችን በድግግሞሽ /በፓተርን/ መልክ እየተጠቀሙ ሸካራነትን መግለጽ ሲቻል ለስላሳነትን ደግሞ ምንም ሳንነካ ልሙጡን በመተው ወይም የቀባነውን እርሳስ በማሸት ነው።



ስዕል 5 የተለያዩ ቴክስቸር ገጽታዎች


## ሠ. ፍካት

ፍካት ከእይታዊ ጥበባት አለባዊያን አንዱ ሲሆን በስዕል ስራ ውስጥ ያለ የጥቁረትና የንጣት ደረጃ ነው። ፍካት (ቫሊዩ) መሰረታዊ ጽንስ ሀሳቦች ያሉት ሲሆን እነዚህም፦ ማንጣት፣ ማጥቆር እና ቫሊዩ ስኬል ናቸው።

ማንጣት ማለት በቀለማት ላይ ነጭ ቀለምን በመጨመር ንጣትን መፍጠር፣ ማጥቆር በቀለማት ላይ ጥቁር ቀለምን በመጨመር ጥቁረትን መፍጠር ሲሆን ቫሊዩ ስኬል ደግሞ ከንጣት እስከ ጥቁረት ያለ ደረጃን የሚያሳይ ማለት ነው። በቀለማት ላይ ነጭን መጨመር እና ቀለሙን ማንጣት በቀለም ቅብ ውስጥ

ብርሃንን ለመፍጠር ይጠቅመናል።





ስዕል 6 የተለያዩ የፍካት ደረጃዎች

ከላይ እንደምትመለከቱት ፍካት በንድፍ ሲሰራ የእርሳሱ ከጥቁረት እስከ ንጣት ያለው ደረጃ ሲሆን በቀለም ቅብ ደግሞ የቀለሙ የጥቁረትና ንጣት ደረጃ ነው። ከጥቁረት እስከ ንጣት ያለውን የሚያሳየው የፍካት ደረጃ ተብሎ ይጠራል።

## መልመጃ 2

1. 9 ደረጃዎች ያሉት ሰንጠረዥ አዘጋጁና እርሳስን እና ቀለማትን በመጠቀም የፍካት ደረጃዎችን (value scale) ሰርታችሁ ለመምራችሁ አሳዩ።

## ረ. ቀለም

ሌላው መሰረታዊ የስነ-ሥዕል አለባዊያን ቀለም ሲሆን በአንድ አካል ላይ ያለ የብርሃን ነጸብራቅ ውጤት ነው። ይህም ማለት ብርሃን በነገሮች ላይ ሲያርፍ ተንጸባርቆ ከአይናችን ሲደርስ የሚሰጠን ስሜት ነው። በዚህም ምክንያት ቀለማትን ለማየት ሦስት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ። እነዚህም፦ ብርሃን፣

አንጸባራቂ ወለል እና ቀለሙን የሚለየው የስሜት ህዋስ (ዓይን) ናቸው።

ቀለማት በዚህ የክፍል ደረጃ ሦስት መሰረታዊ ባህሪያት ያሏቸው ሲሆን እነዚህም

1. የቀለማት መጠሪያ ለምሳሌ፦ ቀይ፣ ቢጫ፣ ሰማያዊ፣ አረንጓዴ.... ወዘተ
2. የቀለማት ንጽህናና መቆሸሸ፦ የቀለማት ንጽህናና መቆሸሸ የሚወሰነው ከሌሎች ቀለማት ጋር በሚያደርጉት ውህደት ሲሆን ቀለማት ከተቃራኒያቸው ጋር ውህደት ሲያደርጉ ቀለማት ንጽህናቸውን እያጡ ይሄዳሉ።
3. ፍካት፡ የቀለማት የጥቁረትና የንጣት ደረጃን የሚያሳይ ሲሆን በአንድ ቀለም ላይ ጥቁርንና ነጭ ቀለምን በመጨመር የሚፈጠር ነው። በቀለሙ ላይ ነጭ ሲጨመር ቀለሙ የሚነጣ ሲሆን ጥቁር ሲጨመር ደግሞ እየጠቆረ ይሄዳል።

በቀለም ቅብ ትምህርት ውስጥ ስለቀለም መረዳት ያለብን ነገሮች በመጀመሪያ ስለቀለማት ቻርት ስለቀለማት የፍካት ደረጃዎች እና ስለቀለማት ስምምነት ነው።

## 1.1.2 የቀለማት ቻርት (ቀለበታዊ ቀለማት)

የቀለም ቻርት የቀለም ቅብ ስራን ለመስራት ስለ ቀለማት ባህርያት የምናጠናበት ሲሆን በውስጡም ሞቃትና ቀዝቃዛ ቀለማትን፣ የቀለማት ድብልቅ ውጤቶችን እና ተጻራሪ (ተቃራኒ ) ቀለማትን የያዘ ነው።

የቀለማት ቻርት ክባማ በሆነ ቀለበት በአስራ ሁለት ክፍሎች የተከፋፈለ ሲሆን ቀለማቱም መስራች፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ደረጃ የሚባሉ ቀለማትን የያዘ ነው።

**የመጀመሪያ ደረጃ ቀለማት (መሰረታዊ ቀለማት)**፦ የሚባሉት በቀለም ቻርት ውስጥ ቀይ፣ ቢጫና ሰማያዊ ናቸው። እነዚህ ቀለማት በቀለሙ ቻርት ላይ በእኩል ርቀት የሚገኙ ሲሆን ለቀለማት ቻርት መሰረታዊ መዋቀር ናቸው። ቀይ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ ቀለማት ርስበርስ ሲዋሀዱ ሌሎች ቀለማትን ይፈጥራሉ።

**ሁለተኛ ደረጃ ቀለማት**፦ ብርቱካናማ፣ አረንጓዴ እና ወይነጠጅ ቀለማት ሲሆኑ እነዚህ ቀለማትም የሚፈጠሩት መስራች ቀለማትን ርስበርስ እኩል በሆነ መጠን ሲቀላቀሉ ነው። ይሄውም

ቀይ ቀለም ከቢጫ ጋር እኩል በሆነ መጠን ሲዋሃዱ ብርቱካናማ ቀለምን፣ ቢጫ ቀለም ከሰማያዊ ጋር ሲቀላቀሉ አረንጓዴን እና ሰማያዊ ከቀይ ጋር ሲቀላቀል ወይነጠጅ ቀለምን ይፈጥራሉ።

**ሦስተኛ ደረጃ ቀለማት፡-** እነዚህ ቀለማት ሀምራዊ (ቀላያለ ወይነጠጅ)፣ ቀላያለ ብርቱካናማ፣ ሰማያዊ አረንጓዴ፣ ሰማያዊ ወይነጠጅ፣ ቢጫማ አረንጓዴ ቢጫማ ብርቱካናማ ሲሆኑ በቁጥርም በቀለማት ቻርት ውስጥ 6 ናቸው። ቀለማቱ የሚፈጠሩት መስራች ቀለማትን ከሁለተኛ ደረጃ ቀለማት ጋር እኩል በሆነ መጠን ርስበርስ በማዋሃድ (በመቀላቀል) ነው።

ምሳሌ፡-

ቀይ + ብርቱካናማ = ቀላያለ ብርቱካናማ

ቀይ + ወይንጠጅ = ሀምራዊ (ቀላያለ ወይነጠጅ)


ቢጫ + ብርቱካናማ = ቢጫማ ብርቱካናማ

ሰማያዊ + ወይንጠጅ = ሰማያዊ ወይንጠጅ

ሰማያዊ + አረንጓዴ = ሰማያዊ አረንጓዴ

ቢጫ + አረንጓዴ = ቢጫማ አረንጓዴ

**ማሳሰቢያ፡-** እነዚህ ቀለማት በሚቀላቀሉበት ወቅት በእኩል መጠን መሆን ይኖርባቸዋል።





ስዕል 7 የቀለማትን ቻርት የሚያሳይ ዲያግራም


## መልመጃ 3

1. የተለያዩ ቀለማትን በማዋሀድ የቀለም ቻርትን በወፍራም ወረቀት ሰርታችሁ ለመምራችሁ አሳዩ።

### 1. የቀለማት ጥቁረትና ንጣት (ቫሊዩ)፡-

ቀለማት የራሳቸው የሆነ የጥቁረትና የንጣት ደረጃ ያላቸው ሲሆን የእነዚህ ደረጃም ፍካት ተብሎ ይጠራል። በሰማያዊ ቀለም ላይ ነጭ እየተጨመረበት ሲሄድ ቀለሙ እየነጣ ጥቁር ሲጨመርበት ደግሞ ቀለሙ እየጠቆረ ይሄዳል። ይህ ሂደትም የቀለማት ንጣትና ጥቁረት ተብሎ ይጠራል።





ስዕል 8 የቀለማት የንጣትና ጥቁረት ደረጃን የሚያሳይ ስንጠረጅ

## 2. ሞቃትና ቀዝቃዛ ቀለማት፡

የቀለማት ሞቃትና ቀዝቃዛነት የሚወሰነው ቀለማቱን ስንመለከት አይናችን ላይ በሚፈጠረው ስሜት ነው። ቀለማቱን ስንመለከታቸው ከፀሀይና ከእሳት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ቀለማት የሞቃት ስሜት ሲፈጥሩ። ውሃና አየርን የሚመስሉት ደግሞ የመቀዝቀዝ ስሜት ይፈጥራሉ። በቀለም ቻርት ውስጥ ቢጫ፣ ቢጫ ብርቱካናማ፣ ብርቱካናማ፣ ቀላያለ ብርቱካናማ፣ ቀይና ቀላ ያለ ወይነጠጅ (ሀምራዊ) ሞቃት ቀለማት ሲሆኑ ወይነጠጅ፣ ሰማያዊ ወይነጠጅ፣ ሰማያዊ፣ ሰማያዊ አረንጓዴ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫማ አረንጓዴ ደግሞ ቀዝቃዛ ቀለማት ተብለው ይጠራሉ።

## 3. ገለልተኛ ቀለማት

ገለልተኛ ቀለማት የሚባሉት በቀለም ቻርት ውስጥ የማይገኙ ሞቃትም ቀዝቃዛም ያልሆኑ ቀለማት ሲሆኑ በስዕል ውስጥ ጥላና ብርሀን ለመፍጠር የምንጠቀምባቸው ናቸው። ነጭና ጥቁር ቀለማት ገለልተኛ ቀለማት ተብለው ይጠራሉ።


## 4. የቀለማት ስምምነት

የቀለማት ስምምነት በቀለማት ቻርት ውስጥ የቀለማት ግንኙነት እና ዝምድና ነው። በዚህ የክፍል ደረጃ ላይ ተጻራሪ (ተቃራኒ) ቀለማትን ታያላችሁ።

ተጻራሪ ቀለማት የሚባሉት በቀለም ቻርት ውስጥ አንድ ቀለም ከሚገኝበት ቦታ በትይዩ ርቀት ላይ የሚገኘውን ቀለም ነው። እነዚህ ሁለት ቀለማት ተጻራሪ (ተቃራኒ) ቀለማት ተብለው ይጠራሉ።

ለምሳሌ፦ በቀለም ቻርት ላይ በቢጫ ትይዩ መስመር ብናሰምር የሚገኘው ቀለም ወይነጠጅ ነው ስለዚህ የቢጫ ተጻራሪ ቀለም ወይነጠጅ ነው ማለት ነው።

በቀለም ቻርት የሚገኙ ቀለማትና ተንጻራሪያቸው



ቀይና አረንጓዴ

ቢጫና ወይነጠጅ

ሰማያዊና ብርቱካናማ

ቢጫማ አረንጓዴና ቀላ ያለ ወይነጠጅ

ቀላያለ ብርቱካናማና ሰማያዊ አረንጓዴ ተጻራሪ ቀለማቶች ናቸው።

ስዕል 9 በቀለም ቻርት የሚገኙ ቀለማት ና ተንጻራሪያቸው


## 1.1.3 በእይታ ጥበብ አለባዊያን የንድፍ ስዕሎችን መስራት

የንድፍ ጥበብን ለመስራት መሰረታዊ የሚባሉ የስዕል መሳሪያዎች የሚያስፈልጉ ሲሆን ከነዚህም መካከል እርሳስ፣ የከሰል እርሳስ (ቻርኮል)፣ ወረቀት፣ የንድፍ ደብተርና ላጲስ ተጠቃሽ ናቸው።

እርሳሶች ለተለያዩ የንድፍ ተግባራት በሚመች ሁኔታ በተለያዩ የአሰራር ደረጃዎች የተዘጋጁ ሲሆኑ የተለያየ የጥንካሬና የልስላሴ ደረጃዎች አሏቸው። እነዚህም የእርሳስ ዓይነቶች እንደ ጥንካሬያቸውና ልስላሴቸው የሚያስቀምጡት መስመር ይለያያሉ።

ጠንካራ የእርሳስ ዓይነቶች ቀጠን ያሉና ግልፅ የሆኑ መስመሮችን የሚያስቀምጡ ሲሆን ለህንፃ ዲዛይንና ለሌሎች መሠረታዊ የዲዛይን ስራዎች ያገለግላሉ። በተቃራኒው ለስላሳ እርሳሶች ጠቆርና ለስለስ ያሉ መስመሮችን የሚያስቀምጡ ሲሆን ለንድፍ ስራ አመች ናቸው።

በአንድ አካል ላይ ብርሃን በሚያርፍበት ጊዜ በተቃራኒው ጥላ የሚፈጠር ሲሆን ይህንን ሁኔታ በደንብ ማስተዋልና ጥላውን ክፍል በእርሳስ ጠቆር ማድረግና ብርሃናማውን ደግሞ ነጣ በማድረግ መስራት ያስፈልጋል።



ስዕል 10 የቁሳቁሶች ንድፍ

### መልመጃ 4

1. የእይታዊ ጥበብ አለባውያንን ተጠቅማችሁ የሚያስደስታችሁን የተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ምስሎችን በስዕል ደብተራችሁ ሰርታችሁ ለመምራችሁ አሳዩ።

ስዕሎቻችሁን ለመምህራችሁ አቅርባችሁ በምታሳዩበት ወቅት ስለ ስራችሁ የሚሰጡ አስተያየቶችን መቀበል ለሚቀጥለው ስራችሁ መስተካከልና መሻሻል እገዛ የሚያደርግላችሁ መሆኑን በመረዳት አስተያየት የመቀበል ልምዳችሁን ማዳበር ጠቃሚ ነው።

## 1.1.4 በቀለማት የተለያዩ ስዕሎችን መስራት

በአካባቢያችን የምናያቸው ነገሮች እንደ ተራራ፣ ወንዝ፣ ሸንተረር፣ ደን፣ እንስሳት፣ አእዋፋት በአጠቃላይ በምድር ላይ የሚገኙ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ የሆኑ ነገሮች በሙሉ በተለያዩ የቀለማት አይነቶች ያሸበረቁ ናቸው። በመሆኑም እናንተ ተፈጥሮን በስዕላችሁ ለማንጸባረቅ በምትፈልጉበት ጊዜ በትክክል የቀለማትን ባህሪ በቅድሚያ መረዳትና ማወቅ ይጠበቅባችኃል። በዚህ የክፍል ደረጃ በውኃ ቀለምና በዘይት ቀለም የተለያዩ ስዕሎችን ትሰራላችሁ።

### የውሃ ቀለም

የውኃ ቀለም በውሃ የሚበጠበጥና ከብርሃን ወደ ጥላ የአቀባብ ቴክኒክ የምንሰራው ሲሆን የሚቀባውም በስሱ ነው። የሚሰሩበት ብሩሾችም ውሃ መቋጠር የሚችሉና ለስላሳ የሆኑ ናቸው።




ስዕል 11 በውሃ ቀለም አሰራር ቴክኒክ የተሰራ ቀለም ቅብ

### የዘይት ቀለም

የዘይት ቀለም በዘይት ወይም በጋዝ የሚቀጥን የቀለም አይነት ሲሆን የአቀባብ ቴክኒኩም እንደፈለግን ከጥላ ወደ ብርሃን ወይም ከብርሃን ወደ ጥላ መሄድ የሚያስችለን ነው። ቀለሙም በወፍራሙ እየለጠፍንም ሆነ በስሱ ልንጠቀመው እንችላለን።



ስዕል 12 በዘይት ቀለም አሰራር ቴክኒክ የተሰራ ቀለም ቅብ

**መልመጃ 5**

1. የእይታዊ ጥበብ አለባውያንን ተጠቅማችሁ የሚያስደስታችሁን የተፈጥሯዊ ወይም ሰው ሰራሽ ምስሎችን በምታገኟቸው ቀለማት ቀለም ቅብ በመስራት ለመምራችሁ አሳዩ።

## 1.2 መሰረታዊ የሙዚቃ አለባዊያን

የሙዚቃ አለባዊያን የሚባሉት ምት፣ ዜማ፣ ህብረ ድምፅ፣ መዋቅር፣ ተለዋዋጭ ምልክቶች፣ የድምፅ ቀለም ወዘተ ናቸው። ይሁኑ እንጅ በዚህ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች እንድታውቋቸው የተፈለጉት ሙዚቃን ለመፃፍና ለማንበብ የሚያስችሉ የኖታና የእረፍት ምልክቶችን ጊዜ/ምት፣ ተለዋዋጭ ምልክት (ዳይናሚክስ)፣ የምት አካሄድ ሁኔታ (ቴምፖ)፣ የድምፅ ቃና (ፒች) እና ዜማ ናቸው። እነዚህም መሰረታዊ የሙዚቃ አለባውያን እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## ቅደመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄዎች

1. ከአሁን በፊት የምታውቁትን ኖታ በመዘርዘር ስንት ምት እንዳለው ተናገሩ።
2. ኖታዎች፣ እረፍት ምልክቶችና ተለዋዋጭ ምልክቶች በሙዚቃ ስራ ውስጥ ያላቸው ሚና ምንድን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?

### 1.2.1 የኖታዎችና የእረፍት ምልክቶች አጨዋወት

## መልመጃ 6


1. የኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶችን የምት አቀማጠር አስረዱ።

በሙዚቃ ጽሑፍ አጻጻፍ ስርዓት ውስጥ ማንኛውም እንቅስቃሴ ያለው ነገር ሁሉ ከምት ቁጥጥር ውጭ አይደለም። የተለያዩ የጊዜ ቆይታ ያላቸው ኖታዎችን ለማንበብ የምንወስደው ጊዜ ምት/ሪትም ይባላል። በሌላ መልኩ ምት የጊዜ ዋጋ ያለውና እንቅስቃሴ ለመፍጠር የሚያገለግል ስርዓት ያለው ተግባራዊ ክንዋኔ ነው።

ኖታዎች ድምፅ መስጠት የሚችሉ፣ ቃና ያላቸውና ሙዚቃን ጽፈን ለማንበብ የሚረዱ ምልክቶች ናቸው። ልክ እንደ ሙዚቃ ኖታዎች ሁሉ የራሳቸው የጊዜ ቆይታ ያላቸው ነገር ግን በዝምታ የሚነበቡ የሙዚቃ እረፍት ምልክቶች ተብለው ይጠራሉ። የሙዚቃ ኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶችን ረጅም ምት ከሚቆጠርለት በመጀመር እንደሚከተለው ትመለከታላችሁ።

### ሀ. ሙሉ ኖታን መጫወት

ሙሉ ኖታን ለመጫወት በቅድሚያ የጊዜ መጠኑን ወይም የምት ብዛቱንና እንዴት ማንበብ እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሚከተለውን ምስል በመመልከት ሙሉ ኖታን እንዴት መጫወት እንደሚቻል መለየት ትችላላችሁ።




### መልመጃ 7

1. ተማሪዎች፣ በቡድን በመሆን አራት ሙሉ ኖታዎችን ጽፋችሁ በአካባቢያችሁ በምታገኙት የምት የሙዚቃ መሳሪያ በማጀብ ተጫውታችሁ አሳዩ።

## ለ. ሙሉ ኖታንና የሙሉ የዕረፍትን ቀላቅሎ መጫዎት


### መልመጃ 8

1. ሙሉ ኖታንና የዕረፍት ምልክቱን በመቀላቀል ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመሆን በቅብብሎሽ ተጫዎቱ።



## ሐ. ግማሽ ኖታን መጫወት

ግማሽ ኖታን ለመጫወት በቅድሚያ የጊዜ መጠኑን ወይም የምት ብዛቱንና እንዴት ማንበብ እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሚከተለውን ምስል በመመልከት ግማሽ ኖታን እንዴት መጫወት እንደሚቻል መለየት ትችላላችሁ።




የግማሽ ኖታ አነባበብ ሁኔታ

## መልመጃ 9

1. ከዚህ በታች የተቀመጡ ግማሽ ኖታዎችንና ሙሉ እረፍቶችን ተጫውታችሁ አሳዩ።



### መ. የግማሽ ኖታንና ዕረፍትን በመቀላቀል መጫወት


## መልመጃ 10

1. ተማሪዎች፣ በቡድን በመሆን ከዚህ በታች የተቀመጡትን ኖታዎችና እረፍቶችን በአካባቢያችሁ በምታገኙት የምት የሙዚቃ መሳሪያ በማጀብ ተጫውታችሁ አሳዩ።



### ሠ. ሩብ ኖታን መጫወት

ሩብ ኖታን ለመጫወት በቅድሚያ የጊዜ መጠኑን ወይም የምት ብዛቱንና እንዴት ማንበብ እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሚከተለውን ምስል በመመልከት ሩብ ኖታን እንዴት መጫወት እንደሚቻል መለየት ትችላላችሁ።




## መልመጃ 11


1. ከዚህ በታች የተቀመጠውን ኖታ ምሳሌ በማድረግ በአካባቢያችሁ ከምታዩት እንቅስቃሴ ጋር በማመሳሰል እንቅስቃሴውን በኖታው ዋጋ መሰረት ተለማመዱ።



## ረ. ሩብ ኖታንና ዕረፍትን በመቀላቀል መጫወት


### መልመጃ 12

1. ከዚህ በላይ ያያችሁትን ኖታና የዕረፍት ምልክት አጨዋወት ምሳሌ በማድረግ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ኖታዎች ተጫዎቱ።




## ሸ. የአንድ ስምንተኛ ኖታን መጫወት

አንድ ስምንተኛ ኖታን ለመጫወት በቅድሚያ የጊዜ መጠኑን ወይም የምት ብዛቱንና እንዴት ማንበብ እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሚከተለውን ምስል በመመልከት አንድ ስምንተኛ ኖታን እንዴት መጫወት እንደሚቻል መለየት ትችላላችሁ።



## መልመጃ 13


1. ከዚህ በታች የቀመጡ ኖታዎችና የዕረፍት ምልክቶችን በመለማመድና ሌሎችንም በመጻፍ ተጫዎቱ።



### ቀ. አንድ ስምንተኛ ኖታንና የዕረፍትን በመቀላቀል መጫዎት

## መልመጃ 14

1. ከዚህ በታች የተቀመጠውን የአንድ ስምንተኛ ኖታንና የዕረፍት ምልክቱን በመለማመድ በራሳችሁ ሌላ ዕፋችሁ አንብቡ።




### ባለ ነጥብ ኖታ


## ቅደመ እውቀት መፈተሻ ጥያቄ


1. ነጥብ በሙዚቃ ኖታ ውስጥ የሚሰጠውን ጠቀሜታ በመዘርዘር ለመምህራችሁ ተናገሩ።

አንድ ኖታ የነበረውን ቅርፅ እንደያዘ በቀኙ በኩል ካለው የኖታው ጭንቅላት ስር ነጥብ ሲቀመጥለት ባለ ነጥብ ኖታ ይባላል። ነጥብ የተቀመጠለት ኖታ ደግሞ የነበረውን የምት መጠን በግማሽ የሚጨምርለት ሲሆን የባለነጥቡ ኖታ ዋጋ ማለት የነበረው የኖታ ዋጋ ሲደመር የነበረው የኖታ ዋጋ ግማሽ ይሆናል።

የሚከተሉትን ምሳሌዎች በጥሞና ተመልከቷቸው።

1.  = 4 

2.  = 2 

3.  = 1 


 4 + 2 = 6

 2 + 1 = 3

 1 + ½ = 1½

ከዚህ ቀጥሎ የተቀመጡትን ኖታዎች ነጥብ ሲቀመጥባቸው ስንት ምት እንደሚኖራቸው ደምሩ።

1. 

2. 

3. 

**መልመጃ 15**

1. የተለያዩ የባለ ነጥብ ኖታዎችን በመፃፍ መልሳችሁ በተግባር ተጫወቷቸው።

## 1.2.2 ተለዋዋጭ ምልክቶች

### የድምጽ መጠን መለዋወጫ ምልክቶች

የተለያዩ ዜማዎች ወይም ሙዚቃዎች ውበትና ለዛ እንዲኖራችው ለማድረግ የድምፅ መለዋወጫ ምልክቶች የድምፁን ውፍረትና ቅጥነት፣ የድምፁን መጨመርና መቀነስን የሚያዝዙ ምልክቶች ናቸው። እነዚህን ምልክቶችና ትዕዛዞች በሚከተለው ሰንጠረዥ ተቀምጠዋል።

| የድምፅ መጠን ምልክት | መጠሪያ ስም | ትዕዛዝ |
|---|---|---|
| P | ፒያኖ | ዝቅተኛ የድምፅ መጠን |
| PP | ፒያኖ ሲሞ | በጣም ዝቅተኛ የድምፅ መጠን |
| F | ፎርቴ | ከፍተኛ የድምፅ መጠን |
| FF | ፎረቴ ሲሞ | በጣም ከፍተኛ የድምፅ መጠን |
| < | ክሬሼንዶ | ከዝቅተኛ ድምፅ ተነስቶ ቀስ በቀስ ወደ ከፍተኛ ድምፅ ማስኬድ |
| > | ዲ-ክሬሼንዶ | ከከፍተኛ ድምፅ ተነስቶ ቀስ በቀስ ወደ ዝቅተኛ ድምፅ ማስኬድ |

**መልመጃ 16**

1. አንድ የሚታወቅ መዝሙር/ሙዚቃ በመጠቀም ከላይ ያያችሁትን የተለዋዋጭ ምልክት በመጠቀም ዘምሩ።

### የምት አካሄድ መጠን ትዕዛዝ

መዝሙር ወይም ሙዚቃ በምንጫወትበት ጊዜ የምት አካሄዱን ፍጥነትና እርጋታን የሚለካ ዓለም አቀፍ መመሪያ ወይም ህግ ነው። ይህ የምት የአካሄድ ፍጥነት በ1815 ዓ.ም በተሰራ ሜትሮኖም በተባለ መሳሪያ ይለካል። መጠሪያውንና ትዕዛዙን በሰንጠረዥ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

| ስም/መጠሪያ | የትዕዛዙ ትርጉም |
|---|---|
| አንዳንቴ | ረጋ ያለ የምት አካሄድ |
| ሞደራቶ | መካከለኛ ፍጥነት አካሄድ |
| አሌግሮ | ፈጣን አካሄድ |
| አሌግራቶ | በጣም ፈጣን አካሄድ |

## መልመጃ አስራ 17

1. ከላይ የተቀመጡትን የምት አካሄድ መጠኖች መምህራችሁ አስምተው ከሚያዘምሯችሁ መዝሙር ላይ ፍጥነቱንና መዘግየቱን በማዳመጥ ገምግሙ።

### 1.2.3. የሙዚቃ ድምጽ ቃና

የሙዚቃ ቃና የሰውን ልጅ የማድመጥ ስሜትን መማረክ የሚችል የድምጽ ቅንብር ውጤት ነው። ሁሉንም የምንሰማቸውን ድምፆች ሙዚቃ ናቸው ልንል አንችልም። ሙዚቃ የሚባለው ድምጾች ማራኪ እንዲሆኑ በህግና በሥርዓት የመደርደር የማቀናጀት ጥበብ ውጤት ነው። ይህንን መነሻ በማድረግ የምንሰማውን ድምፅ በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን።

**ሁካታ ድምፅ፡-** የድምፅ ፍጥነቱ ለመለካት የሚያስቸግር የሚረብሽ አይነት ድምፅ ነው። ምሳሌ መስተዋት ወድቆ ሲሰበር፣ ቆርቆሮ በእንጨት ሲመታ፣ የመብረቅ ድምፅ ወ.ዘ.ተ ይገኙበታል።

**ሙዚቃዊ ድምፅ፡-** ድምፁ ሊለካና ልንረዳው የሚችል ስሜት የሚሰጥና ቃና ያለው ነው። ምሳሌ የሰዎች ድምፅ፣ የሙዚቃ መሳሪያዎች ድምፅ ወ.ዘ.ተ መጥቀስ ይቻላል።

## መልመጃ አስራ 18

1. በአካባቢያችሁ ሰምታችኋቸው የምታውቋቸውን የሁካታና ሙዚቃዊ ድምጾችን እያነሳችሁ ከመምህራችሁና የክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩባቸው።


## 1.2.4 የድምፆች ስያሜ

የሙዚቃ መሰረታዊ ድምፆች ሰባት ናቸው። እነዚህን ድምፆች ለመሰየም ከA-G ያሉ ሰባት የእንግሊዘኛ ፊደላትን በቅደም ተከተል በመጠቀምና በጣሊያንኛ (በሶል-ፋ ስያሜ) የሚጠሩ ናቸው። እነዚህ ድምጾችም እንደሚከተለው ቀርበዋል።


| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በእንግሊዘኛ ---------- | C | D | E | F | G | A | B | |
| የጣሊያንኛ ወይም የሶል-ፋ ስያሜዎች | DO | Re | Mi | Fa | Sol | La | Si | |

የሙዚቃ ድምፆች ስያሜ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ሲደረደሩ የሚያሳይ።




ከዚህ በላይ በስታፍ ላይ የተቀመጡት ኖታዎች ስያሜያቸው ከA- G ያሉት ፊደላት ቢሆኑም በሙዚቃ መጻፊያ ላይ የተደረደሩት ግን የዶን ድምጽ እንደመነሻ በመጠቀም መሆኑን ከግንዛቤ ውስጥ እንድታስገቡ ይፈለጋል። የሚከተሉት ደግሞ የተለያዩ ድምጾችን እንደ መነሻነት በመጠቀም የተጻፉ ናቸው። ኖታዎች የተቀመጡበትን ቦታ በመመልከት ስያሜያቸውን ከኖታዎች ስር አስቀምጡባቸው።



## 1.3 የቴያትር መሰረታዊ አለባዊያን

ቴያትር ጥበባዊ ቃል ሲሆን በውስጡ በተዋንያን የሚተወኑ ግጭቶችን፣ ድርጊቶችንና፣ የሚፈጠሩ ድባቦችን የያዘ ሲሆን በመድረክ ላይ ከተመልካቾች ፊት የሚተወን ነው። የቴያትር ጥበብ የሰው ልጆች ሕይወት በመድረክ ላይ የሚገለፅበትና የሚተረጎምበት አንዱ የኪነ-ጥበብ ዘርፍ ነው።

የቴያትር መሰረት ሆነው የሚያገለግሉት የቴያትር አለባዊያን ቁጥር እንደ ባለሙያዎች ቢለያይም፣ በዚህ የትምህርት ርዕስ የምንመለከታቸው መቼት፣ ገፀ ባህሪያት፣ ሴራ፣ የቴያትር ጸሐፍና ጭብጥ ናቸው።

### ሀ. መቼት

መቼት የቴያትር ዋነኛ አለባውያን ነው። መቼት የሚከተሉትን ሁለት መሰረታዊ ሀሳቦች በውስጡ የሚያቅፍ ሲሆን እነሱም፡

1. ቴያትሩ የሚከናወንበት ቦታ
2. ቴያትሩ የሚከናወንበት ጊዜ ናቸው።

በተራ ቁጥር 1 የተጠቀሰው ቴያትሩ የሚከናወንበት ቦታ የሚያመለክተው ፀሀፊ ተውኔቱ የተውኔቱ ታሪክ ተጽፎበታል ብለን ያሰፈርነውን የታሪኩን የክንውን ቦታ ነው።

ቴያትሩ በሚከናወንበት ጊዜ ሌላው የመቼት አንዱ አካል ሲሆን፣ የቴያትሩ ታሪክ የሚከናወንበት ጊዜ የሚያመለክት ነው። የቴያትሩ ታሪክ በየትኛውም ዘመን፣ በየትኛው ሰዓትና ደቂቃ እየተፈፀመ እንደሆነ በሚያመለክተው በዚህ ክፍል ፀሀፊ ተውኔቱ ጊዜውን ፊት ለፊት ወይም ከገፀ ባህሪያቱ አጠቃላይ ሁኔታ ተነስተን እንድንገምት ያደርጋል።

## ለ. ገፀ ባህሪ

ገፀ ባህሪ ከቴያትር አለባዊያን አንዱና ዋነኛው ነው። ማንኛውም የስነ-ጽሁፍ ውጤት ካለ ገፀ ባህሪያት እውን እንደማይሆን ሁሉ ቴያትርም ያለ ገፀባህሪያት የሚታሰብ ጉዳይ አይሆንም።

ገጸ ባህሪያት የሚባሉት በፈጠራው ዓለም ውስጥ በጸሃፊ-ቴያትር የሚፈጠሩ ፍጡራን ናቸው። የምናቡ ዓለም ፈጠራን በዋናነት በሦስት የሚከፍል ሲሆን እነዚህም ሰዎች (ሰለሞን፣ ከድር፣ ሰላማዊት ወዘተ እንስሳት (በግ፣ ፍየል፣ ቀበሮ፣ አንበሳ ወዘተ)ና ረቂቅ ሀሳቦች (ደግነት፣ ተንኮል፣ መልካም ስራ ወዘተ) ናቸው።

የቴያትሩ ገፀ ባህሪያት ማለት በእውኑ ዓለም ያሉ ሰዎችን የሚወክሉ የምናብ ዓለም ወይም ታሪክን መሰረት ያደረጉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ገፀባህሪያት እንደሰው የሚናገሩ፣ የሚያዳምጡ፣ የሚበሉ፣ የሚጠጡ፣ በአጠቃላይ ሰውነትን የሚላበሱ ባህሪያት ናቸዉ።

አንድ ተዋናይ ወክሎ የሚጫዎተውን ገጸ ባህሪ ምንነት ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል። የተሰጠውን ገጸ ባህሪ ሰው ይሁን እንስሳ ወይም ደግሞ ረቂቅ ሀሳብ እንደ አፈጣጠሩ በትክክል አውቆና ተረድቶ መጫዎት ይገባዋል። ለዚህም ይረዳው ዘንድ ገጸ ባህሪን መተንተን እጅግ በጣም አስፈላጊና ቀዳሚ ተግባሩ ነው።

## ሐ. ሴራ

ሴራ ታሪኩን፣ ግጭትን፣ ምክንያትና ውጤትን ጭምር በውስጡ ይዞ የሚገኝ የቴያትር አላባ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ በድርጊቶች መካከል ያለ የቅደም ተከተል ቁርኝት፣ የቁርኝቶች ተአማኒነት እና የሚያስከትሉት ውጤት፣ የውጤታቸው ምክንያት ተገቢነት እና ይሁንታን ሴራ ብለን ልንጠራው እንችላለን።

የሴራ ተግባር ቅደም ተከተል ሳያዛባ አንዱን አስቀድሞ አንዱን ሳያዘገይ በምክኒያትና ውጤት ተመርኩዞ መተረክ ነው።

**ለምሳሌ**፦ ‹‹ወታደሩ በጠላት ጥይት ቆስለው ከሞቱ በኋላ ሚስታቸው ወይዘሮ ቃልኪዳን በሀዘን ብዛት ሞቱ።›› የሚለው ሴራ ነው። ግጭትን ምክንያትና ውጤት ሳይቀር በውስጡ ይዞ እናገኘዋለን። ይህንን ታሪክ በመድረክ ስናቀርበው ለልብ ሰቀላ ሲባል ወይም የሚመስጥ አተራረክ እንዲኖረው ለማድረግ የጊዜ ቅደም ተከተል ይጨመርበታል። ወይዘሮይቱ ታመው ባልጋ ላይ እንዳሉ (የወታደሩን አማሟት ሳናሳይ ማለት ነው) የቴያትሩን ታሪክ መጀመር እንችላለን። ከዚያም የባላቸውን ወታደር በምልሰት ቴክኒክ ጣልቃ እናስገባና እንተርካለን። በመጨረሻም ወይዘሮይቱ ሀዘናቸውና ህመማቸው ጠንቶባቸው ሲሞቱ በማሳየት እንደመድማለን።

## መ. የቴያትር ጽሁፍ

የአንድ ቴያትር አንኳር ነጥብና የሌሎች ቴያትር አለባዊያን መገለጫ ሲሆን የቴያትሩን ታሪክ አጠቃላይ ዝርዝር ሁኔታ የሚገልጽ ነው። በመሆኑም ሲፃፍ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል።

የቴያትር ጽሁፍ በሚጻፍበት ጊዜ የሚከተሉትን ባህሪያት የተላበሱ ሊሆን ይገባል።

1. ቁጥብነት ያለው ሊሆን ይገባል። በአንድ ቴያትር ውስጥ የሚጻፍ ታሪክ በጥቂት ቃላት ብዙ የመግለጽ አቅም ሊኖረው ይገባል። በዚህም የተንዛዛ የቋንቋ አጠቃቀምን መጠቀም፣ አላስፈላጊ ሀሳቦችን ማጨቅ የለበትም።
2. ግልጽነት ሊኖረው ይገባል። የቴያትሩ ታሪክ ግልጽና ቀላል መሆን ይኖርበታል። የታሪኩ አንባቢ ወይም ሲመደረክ የሚያይ ተመልካች ሊረዳው በሚችል መልኩ ታሪኩ መጻፍና ማቅረብ።
3. በተቻለ መጠን አረፍተ ነገሮቹ አጫጭር መሆን አለባቸው።
4. ከገፀ ባህሪያቱ ስብዕና ጋር የሚዋሀዱ የቋንቋ አጠቃቀም ሊኖረው ይገባል።
5. አጽንኦት የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች በተገቢው ቦታ ማድረግ ወዘተ...

### ሠ. ጭብጥ

ጭብጥ አካባቢያዊ እና ሁለንተናዊ ተብሎ የሚከፈል ሲሆን አካባቢያዊ ጭብጥ ወቅታዊ ሁኔታን መሠረት አድርጎ የሚጻፍ ሲሆን በአንድ ዘመን እና አካባቢ የተፈጠረን ነገር መነሻ በማድረግ የሚጻፍ ነው፡ ሁለንተናዊ ጭብጥ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ነው።

ሁለንተናዊ ጭብጥ የአለም አቀፋዊነት ባህሪ አለው። በየዘመኑ የተፈጠሩ ክስተቶች፣ ባህል፣ ጊዜ እና ቦታ ሳያግደው የሚታይ የቴያትር ጭብጥ ሁለንተናዊ ጭብጥ ተብሎ ይጠራል። ሁለንተናዊ ጭብጥ ባለበት ቴያትር የሚነሱ ርዕሰ ጉዳዮች አብዛኛውን የአለም ህዝብ በየትኛውም ቦታና ዘመን የሚያሳስቡ እና የሚያወያዩ ጉዳዩች ናቸው። እንደ ፍቅር፣ ጥላቻ፣ ክብር፣ ዝና ወዘተ የመሳሰሉ ጉዳዮች የዚህ የሁለንታናዊ ጭብጥ ማጠንጠኛዎች ናቸው።

**መልመጃ 19**

1. መምህራችሁ በሚያሳያችሁ የቴያትር ቪዲዩ መቼት፣ ገጸ-ባህሪያት፣ ሴራና ጭብጡን ለይታችሁ በመጻፍ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻቹህ ግለጹ።

## 1.3.1 የቴያትር ጥበብ ዋና ዋና አካላት

### ሀ. ተዋንያን



ስዕል 13 የቴያትር ተዋንያን

ተዋንያን የምንላቸው በምናብ አለም ያሉ ሰዎች ሳይሆኑ በእውኑ አለም ያሉ ሰዎች ናቸው። እነዚህም የቴያትሩን ታሪክ በመገንዘብ በመድረክ ላይ የራሳቸውን ባህሪ በመተው የታሪኩን ገፀ ባህሪ ተላብሰው የሚጫዎቱ ሰዎች ናቸው።

**በቴያትር ጥበብ ውስጥ ከተዋንያን የሚጠበቁ ነገሮች**

- ☞ የተለያዩ መዝሙሮችን፣ ዳንሶችን፣ እንቅስቃሴዎችን ወዘተ መማር።
- ☞ በመለማመጃ ክፍል የልምምድ ፕሮግራም ላይ መገኘትና አቅምን ማሳድግ።
- ☞ ከዳይሩክተሩ የሚሰጡ አጠቃላይ አቅጣጫዎችን ማዳመጥና ወደ ተግባር መለወጥ።
- ☞ ከሌሎች ተዋኒያን ጋር በጋራ የመስራት ልምድን ማሳደግ።

ተዋንያን ለመሆን ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ያስፈልጋሉ። እነዚህም

### 1) አካል (ተክለ ሰውነት)

ተዋንያን (በተለይም የቴያትር) ሰውነታቸው ለሁሉም አይነት እንቅስቃሴ ምቾት ያለው መሆን ይገባዋል። ከዚህ በተጨማሪም ቴያትር ብዙ ትንፋሽ ይፈልጋል። ለዚህም የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ማድረግ ያስፈልጋል።

### 2) ድምፅ

ድምፅን ለተመልካች (ለአድማጭ) ድምፅ እንዲሰማ አድርጎ ከማውጣት በተጨማሪ ቃላቱና ፊደላቱ ሳይደራረቡ አድማጮች ጋር ከነሙሉ ይዘቱ እንዲደርስ ስርዓታዊ በሆነ መንገድ መናገር መቻል ነው።

### 3) አዕምሮ

ተዋናዩ ከሁሉም አካላቱ በላይ አዕምሮውን ይጠቀማልና ንቁ መሆን አለበት።

አዕምሮውንም የሚጠቀምባቸው ዋና ዋና ነገሮች

ሀ. ገፀ ባህሪውን ተላብሶ ለመጫወት ገፀ ባህሪውን በአዕምሮው መሳል።

ለ. ስሜት እና

ሐ. አትኩሮት ናቸው።


## ለ. የቴያትር ቦታ (መድረክ)፡

የቴያትር ቦታ (መድረክ) ቴያትሩ በሚገባ ከተዘጋጀ በኋላ ለተመልካች የሚቀርብበት ቦታ ነው። ቴያትር ለተመልካች በተለያዩ መድረኮች ይቀርባል። በዚህ ክፍል የምናየው የቴያትር ማቅረቢያ መድረኮች ከተመልካች ጋር ባላቸው ርቀት በሁለት ከፍለን ነው። እነዚህ ሁለት መድረኮችም የፊት ለፊት መድረክ እና ክብ መድረክ በመባል ይጠራሉ።

**የፊት መድረክ**፡ ቴያትሩ የሚቀርብበት ቦታ ከተመልካች ፊትለፊት የሚሆንበት የመድረክ አይነት ነው።

ይህ መድረክ በሀገራችን ባሉ ቴያትረ ቤቶች ውስጥ ይገኛል። ተዋንያን እና ተመልካቹ በፊት ለፊት አቅጣጫ ይሆናሉ። ከመድረክ በስተጀርባ የተዋንያን አልባሳት መቀየሪያ፣ የመዋቢያና የመጋረጃ ክፍሎች ይኖሩታል። በመድረክ ተዋንያኑ በሚተወኑበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ ወይም በግማሽ ፊታቸውን ወደ ተመልካቹ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ተዋንያኑ ጀርባቸውን ሙሉ ለሙሉ ለታዳሚያን መስጠት የለባቸውም።


የፊት ለፊት መድረክ ከተመልካቹ መቀመጫ ከፍ ብሎ የሚገነባ ነው። ይህ ዓይነቱ መድረክ በታዳሚያንና በተዋንያን መካከል ርቀት የሚፈጥር ከመሆኑም ባሻገር ተዋንያን ገዝፈው እንዲታዩ ምክንያት ይሆናል።



ስዕል 13 የፊት ለፊት ቴያትር መድረክ

**ክብ መድረክ**፦ ቴያትሩ የሚቀርብበት መድረክ ተመልካቹ በሚያዩበት አዳራሽ መሀል ላይ ሲገነባ ክብ መድረክ ይባላል። የቴያትሩ ታዳሚያን በመድረኩ ዙሪያ ይቀመጣሉ። የወንበር አደራደሮች ልክ እንደ ቅርጫት ኳስ ወይም እግር ኳስ ያሉ ናቸው። ተዋናያኑና ተመልካቹ የሚቀራረቡበት የመድረክ አይነትም ነው። ከፊት ለፊት መድረክ በበለጠ መልኩ ታዳሚው ተዋንያንን ከነድርጊታቸው በቅርብ ይመለከቷቸዋል።


## የክብ መድረክ



ስዕል 14 ክብ መድረክን የሚያሳይ

### ሐ. ታዳሚያን፡

የቴያትር ጥበብ የሚከናወነው በተዋንያንና በታዳሚው መካከል መስተጋብር ሲኖር ነው። ስለሆነም ታዳሚያን የምንላቸው የቴያትሩን ታሪክ ገጸ ባህሪ ተላብሰው የሚተውኑትን ተዋንያን የሚመለከቱ ህጻናት፣ አዋቂዎች፣ ሽማግሌዎች ወዘተ ናቸው።



ስዕል 15 ታዳሚያን

## መ. ዳይሬክተር

አጠቃላይ የቴያትሩን የክንውን ሂደት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ድረስ የሚመራና የሚቆጣጠር ባለሙያ ነው።

በቴያትር ጥበብ ውስጥ በዳይሬክተሩ የሚከወኑ ተግባራቶች

ቴያትርን ለማዘጋጀት አዘጋጁ በቅድሚያ መድረኩን ከግምት ውስጥ ማስገባትና የትኛውን ክንውን የትኛው የመድረክ ክፍል ላይ መካሄድ እንዳለበት ይወስናል።

ለየገፀ ባህሪያቱ የተመረጡትን ከዋኞች (casts) የተሰጣቸውን ገፀ-ባህሪ ተላብሰው እንዲተውኑ ከአቅርቦተ ተውኔት (production) በፊት የሚደረጉ የልምምድ ሂደቶችን ያካሂዳል፣ ይከታተላል።

ቴያትሩ በሚሰራበት ወቅት ተዋኒያን የሚለብሱትን አልባሳቶች፣ የመድረክ ዲዛይኑን እና የመብራት ሁኔታውን ያደራጃሉ።

ተዋኒያን የሚያደርጉትን የእንቅስቃሴውን (አካሄድ፣ አዟዟር፣ አቀማመጥ...) ተገቢነትና ትክክለኛነት እንዲሁም ከመልእክቱ ጋር ያለውን ተዛማጅነት ይቆጣጠራል።

## ሠ. የቴያትሩ ዲዛይን ገጽታዎች

የመድረክ ገጽ ግንባታ፣ አልባሳትን፣ የድምፅ ግብአት፣ መብራትን፣ ለቴያትሩ መስሪያ የሚሆኑ ተንቀሳቃሽ ቁሳቁሶች ወዘተ የሚያካትት ነው።

## ሀ. የመድረክ ገፅ ግንባታ

ይህ ማለት መድረካችንን ከተውኔቱ መቼት ጋር በተቀራረበ መንገድ ማዛመድ ነው።ሁለት አይነት የመድረክ ገጽ ግናባታ ያለ ሲሆን እነሱም።

### 1. በቀለም ቅብ አማካኝነት የሚሰራ የመድረክ ገጽ ግንባታ

የመድረካችንን የጀርባ ገፅ በስዕል፣ በመጋረጃ ወይም በተለያዩ መንገዶች የትዕይንቱን ስፍራ ማስመሰል ነው።

ለምሳሌ መቼቱ ውሃ ዳር አካባቢ ከሆነ ያለን አማራጭ የመድረኩን የጀርባ ገፅ ከዚህ ጋር በተቀራረበ ምስል መሸፈን ነው።

### 2. የፈጠራ መድረክ ገጽታ

ይሄኛው ደግሞ የተለያዩ ቁሶችን በመጠቀም መድረኩን ከመቼቱ ጋር ማቀራረብ ነው።

ለምሳሌ ካርቶን፣ እንጨት፣ ብረት የመሳሰሉትን ተጠቅመን ቤት መስራት እንችላለን።

## ለ. አልባሳት

በተውኔቱ ውስጥ ለሚገኙ ለእያንዳንዱ ገፀ ባህሪያት ከአውዱና ከመቼቱ ጋር የተጣጣመ አልባሳት ያስፈልጋል። አልባሳት ለተመልካች ምስልን ከመከሰት ባለፈ ተዋንያኖች ገፀ ባህሪውን በትክክለኛው ስሜት እንዲጫዎቱ አቅምን ይጨምርላቸዋል። ስለዚህ አዘጋጁ በአልባሳት ጉዳይ ላይ የሚሰራ ቡድን ማዘጋጀት ይገባዋል።

## ሐ. የድምፅ ግብአት (Sound)

በተውኔቱ ውስጥ ላሉ ለእያንዳንዱ ትዕይንቶች የሚያስፈልገውን የድምጽ ሁኔታ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

የድምፅ ግብዓት የሚታየው ትዕይንት ለተመልካቹ ስሜት ያለውን ቅርበት እንዲጨምር አቅም ይሆነዋል። ለምሳሌ አሳዛኝ ዘውግ ያለውን አንድ የምታውቁትን ፊልም፣ ድራም ወይም ቴያትር አስቡ... ያንን ፊልም ወይም ድራማ ያለ ድምጽ መሳሪያዎች ለመሳል ሞክሩ ወይም ደግሞ ከቻላችሁ እዩት... ስሜት አይሰጥም። ቢሰጥ እንኳን የቀድሞውን ያህል አይሆንም። ስለዚህ ድምጽ በጣም ወሳኝ ነገር ነው።

### መ. መብራት

ተውኔት በሚቀርብበት ጊዜ የመብራት ግብአት መኖሩ ተውኔቱን የበለጠ ሳቢና የተሟላ ያደርገዋል። ለምሳሌ ልብ አንጠልጣይና የህልም ትዕይንቶች ካሉን ደብዘዝ ያለ ጭል ጭል የሚል መብራት መጠቀም የበለጠ ወደ ተመልካች ልብ ሁነቱን ያቀርበዋል።

### ሠ. ቁሳቁስ

በተውኔቱ ውስጥ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ሲሆኑ ሁለት አይነት ቁሳቁሶች አሉ።

የመጀመሪያው በእጅ የሚያዙና የሚንቀሳቀሱ ቁሳቁሶች ናቸው። ለምሳሌ ከዘራ፣ ጎንጥላ...

ሁለተኛው ደግሞ አንድ ቦታ ይዘው የሚቀመጡ ቋሚ የሆኑ ቁሶች ሲሆኑ ለምሳሌ ብፌ፣ ቁም ሳጥን... ይጠቀሳሉ።

### ረ. ጽሑፍ (ስክሪፕት)

ተዋኒያን እንዲተውኑት የሚፈለገውን ነገር በዝርዝር የሚያሳይ በወረቀት ላይ በደራሲው የተደረሰው ጽሁፍ ነው።

## 1.3.2 ለቴያትር ድርሰት ሀሳብ የሚገኝበት መንገድ

ለቴያትር የሚሆን ድርሰት ስንጽፍ የተለያዩ ሃሳቦችን የምናገኝባቸው መንገዶች ያሉ ሲሆን የሚከተሉትን በዋናነት መጥቀስ እንችላለን።

1. **የግል ገጠመኝ**፦ የቴያትር ድርሰት የሚሆኑ ሀሳቦች ከምናገኝባቸው ምንጮች መካከል አንዱ የግል ገጠመኝ ነው። ማንኛውም ሰው ከልጅነት እስከ ሽምግልና ባለው የህይወት ጉዞ የተለያዩ መጥፎም ይሁን ጥሩ ገጠመኞች ይኖሩታል። ለምሳሌ

- ☞ በልጅነት ዘመኑ ከቤተሰብ፣ ከጎረቤትና ከአካባቢ ሰዎች ጋር ገብተውባቸው የነበሩ ግጭቶች
- ☞ በትምህርት ቤት ቆይታው ከጓደኞቹና ከመምህራን ጋር የነበረው አለመግባባት፣ ያጋጠሙት መሰናክሎች ወዘተ...እነዚህ ገጠመኞች ለአንድ ጸሀፊ-ቴያትር ሀሳብ ሊሆኑ ይችላሉ።

2. **ጋዜጠኞችና መጽሄቶች፡-** የተለያዩ ጋዜቶችን መጽሄቶችን በምናነብበት ጊዜ በውስጡ የተለያዩ ጽሑፎች ልናገኝ እንችላለን። ለምሳሌ የጦርነት ታሪኮች፣ የንቅናቄ ታሪኮች፣ የታዋቂ ሰዎች ታሪክ፣ ወንጀል ነክ ታሪኮች፣ የፍርድ ቤት ጉዳይ ታሪኮች ወዘተ የቴያትር ድረሰት ለመጻፍ እጅግ በጣም ጠቀሚታ አላቸው።

3. **የሌሎች ሰዎች ገጠመኝ፡-** የጓደኞቻችን፣ የዘመዶቻችንና የመሳሰሉት ሰዎች ገጠመኞቻቸውና ታሪኮቻቸው ድርሰት ለመጻፍ ምንጮች ይሆናሉ።

## 1.4 ቀላል የቪዲዮ ቀረጻ



ስዕል 16

### 1.4.1 የቪዲዮ ምንነት

ቪዲዮ ማለት በሁኔታዎች ላይ ተመስርቶ የራሱ የሆነ የጊዜ ቆይታ ያለው በድምጽ ወይም ያለ ድምጽ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ ተንቀሳቃሽ ምስል ነው።

ተንቀሳቃሽ ምስሎችን በቪዲዮ ካሜራ አማካኝነት ተቀርጸው በሞባይል፣ በኮምፒውተርና በቴሌቪዥን አማካኝነት የምንመለከታቸው ሲሆኑ ለምሳሌ፦

ሙዚቃዎች፣ ፊልሞች፣ ድራማዎች፣ የኳስ ጨዋታዎች ወዘተ መጥቅስ እንችላለን።

### 1.4.2 ቪዲዮ በምንቀርጽበት ወቅት ልብ ልንላቸው የሚገቡ ነገሮች

ቪዲዮ በምንቀርጽበት ወቅት ልብ የምንላቸው ጠቃሚ ነገሮች እንዲመከተለው ተቀምጠዋል።

ሀ. ቪዲዮ ለመቅረጽ የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን በአግባቡ ማሰባሰብና ማዘጋጀት። ለምሳሌ የሞባይል ስልክ

ለ. ስለምን እንደምንቀርጽ እና ከምን ጀምረን አስከ የት መጨረስ እንዳለብን ማሰብና ማቀድ ለምሳሌ የሰርግ ፕሮግራም ከሆነ ሁሉንም ሁነት መቅረጽ ስለማይቻል ጠቃሚና ወሳኝ የሚባሉትን ነገሮች መለየትና ማዘጋጀት ይኖርብናል።

ሐ. የብርሀን መጠኑን መቆጣጠር ያስፈልጋል። ይህም ቪዲዮው የተሻለና ጥራት እንዲኖረው ያስችላል።

መ. ከምስሎች በስተጀርባ ያለውን ነገር የቪዲዮውን ጥራት ስለሚወስኑት ቀድሞ ማሰብ ያስፈልጋል። ለምሳሌ የቀለም ሁኔታው

ሠ. የምስሎችን ድርሰት የማደራጀት አቅምን ማሳደግ። ይህም በምንቀርጽበት ወቅት በካሜራ እይታ ውስጥ መግባት ያለባቸውን ነገሮች መስተጋብራቸው ያማረ እንዲሆን ያስችላል።

ረ. መቅረጽ የምንፈልገውን ነገር በትክክል በካሜራችን ውስጥ መግባቱን ማረጋገጥ። የመቅረብና የመራቅ ሁኔታ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ናቸው።

**መልመጃ 20**

1. ልታገኙ በምትቹለባቸው የቪዲዎ መቅረጽ መሳሪያዎች ደስ የሚላችሁን ነገሮች ቀርጻቹሁ ከጓደኞቻቹህ ጋር በመመልከት የምስል ጥራቱን ና አደረጃጀታቸውን አስተያየት ተሰጣጡባቸው።

# የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ አንድ ትምህርት የተጠናቀቀ ሲሆን በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጣችሁን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦላችኃል።

የተነሳውን ነጥብ የምታውቁት ከሆነ የራይት ምልክት ነጥቡን የማታውቁት ከሆነ ኤክስ ምልክት ማድረግና እንደገና ተመልሳችሁ ትምህርቱን ከልሱ።

| ተ.ቁ | ነጥቦች | አሳክቻለሁ | አላሳካሁም |
|---|---|---|---|
| 1 | የዕይታዊ ጥበባት ጽንስ ሀሳብን ተረድቻለሁ። | | |
| 2 | የዕይታዊ ጥበብ ክፍሎችንና አለባውያንን አውቃለሁ። | | |
| 3 | መስመርን በማቀናጀት ምስል መፍጠር እችላለሁ። | | |
| 4 | መሰረታዊ ፎርሞችን ተገንዝቢለሁ። | | |
| 5 | የቴክስቸር አይነቶችን በእርሳስ መፍጠር እችላለሁ። | | |
| 6 | መሰረታዊ የሙዚቃ አለባውያን በውስጡ የሚይዛቸውን አለባውያን አውቃለሁ። | | |
| 7 | ከሙሉ ኖታ እስከ አንድ ስምንተኛ ኖታ ድረስ የጊዜ ቆይታቸውን አውቂአለሁ። | | |
| 8 | ከሙሉ ኖታ እስከ አንድ ስምንተኛ ኖታ ድረስ ያሉ ኖታዎችንና የእረፍት ምልክቶቻቸውን አጨዋወት ተረድቻለሁ። | | |
| 9 | ባለ ነጥብ ኖታ በኖታዎች ፊት ለፊት በመቀመጥ የኖታውን ምት በግማሽ በመጨመር ድምፅ በማያያዝ እንደ ምንጫዎት ተረድቻለሁ። | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 10 | ተለዋዋጭ ምልክቶች ሙዚቃ ስንጫዎት ድምፁን ከፍ ወይም ዝቅ በማወፈር ወይም በማቅጠን ድምፁን ለዛ የሚቀያይር መሆኑን አውቃለሁ። | | |
| 11 | የምት አካሄድ መጠን ትዕዛዝ የሙዚቃውን የምት ፍጥነት ለማፍጠንና ለማዘግየት እንደሚጠቅም አውቃለሁ። | | |
| 12 | የሙዚቃ የድምፅ ቃና ሁካታዊና የሙዚቃዊ ለዛ ያለው ተብሎ በሁለት እንደሚከፈል አውቃለሁ። | | |
| 13 | የሙዚቃ ድምፆች ስያሜ ሰባቱ የሙዚቃ ድምፆች በእንግሊዘኛና በጣሊያንኛ የራሳቸው የሆነ አጠራር እንዳላቸው ተረድቻለሁ። | | |
| 14 | የቴያትር ምንነትን ተረድቻለሁ። | | |
| 15 | የቴያትር አለባውያንን መዘርዘር እችላለሁ። | | |
| 16 | ተዋንያን፣ የታዳሚያ፣ ዳይሬክተር በቴያትር ጥበብ ውስጥ የሚኖራቸውን ተግባራቶችን መዘርዘር እችላለሁ። | | |
| 17 | የቪዲዮ ምንነትን መግለጽ እችላለሁ። | | |
| 18 | ቪዲዮ በተለያዩ መሳሪያዎች በመጠቀም መቅረጽ እንደሚቻል ተረድቻለሁ። | | |

## ማጠቃለያ

☞ የሰው ልጅ ሀሳቡን፣ ስሜቱንና ፍላጎቱን ከሚገልጽባቸው የጥበብ ዘርች መካከል ስዕል፣ ሙዚቃ፣ ቴያትር፣ ፊልም ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። ስዕል በዋናነት መስመራትን በመጠቀም በእርሳስ፣ በክራዮን፣ በከሰል፣ በቀለምና በመሳሰሉት መስሪያዎች በወረቀት፣ በግድግዳ፣ በሸራ ወዘተ የሚገለጽ ሲሆን የራሱ የሆነ መሰረታዊ አለባዊያንም አሉት። አለባዊያን ሲባል የስዕሉን መልዕክት የሚሸከሙ ሰዓሊው የሚጠቀማቸውና የሰዓሊውን ሀሳብ የሚገልጹ ናቸው። ማንኛውም የስዕል ዘርፍ ቀለም ቅብ፣ ንድፍ፣ ህትመት፣ ኪነ ቅርጽ ወዘተ ስራዎችን

ብንመለከት እንዚህን አለባዊያን እናያቸዋለን ማለት ነው።

- ሙዚቃ የሰው ልጆች የተለያየ ስሜትን የሚገልፁበት የጥበብ አንድ ክፍል ነው። ሰዎች ሙዚቃ በሚያዳምጡበት ጊዜ የመከፋትም ሆነ የመደሰት ስሜት ሊፈጠርባቸው ይችላል። ይህን ስሜት የሚሰጥ ሙዚቃ ለማዘጋጀት የተለያዩ የሙዚቃ አለባዊያን መጠቀም ያስፈልጋል።

- ሙዚቃን ለመፃፍና ለማንበብ የምንጠቀማቸው ኖታዎች የድምፅ ቃና ያላቸው ሲሆን የዕረፍት ምልክቶች ደግሞ ድምፅ የማይሰማባቸው ነገር ግን ምት የሚቆጠርላቸው ናቸው። የተለያዩ የጊዜ ቆይታ ያላቸው የኖታዎች ቅንጅት ውጤት ምት ይባላሉ። ምት የሚባለው የጊዜ ዋጋ ያለው፣ እንቅስቃሴ ለመፍጠርና ለመስራት የሚያገለግል ተግባራዊ ክንዋኔ ነው።

- ተለዋዋጭ ምልክቶች የሙዚቃውን ድምፅ ከፍ ወይም ዝቅ በማድረግ የሙዚቃው ቃና ወይም ለዛ ለጆሮ ተስማሚና ስሜት የሚሰጥ እንዲሆን የሚያደርጉ ወሳኝ ምልክቶች ናቸው።

- በጆሮ የምንሰማቸው ድምፆች ሁካታዊና ሙዚቃዊ ድምፆች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። በሙዚቃ ስርዓት ውስጥ ሰባት መሰረታዊ ድምጾች ያሉ ሲሆን እነዚህ ድምጾችም ከእንግሊዝኛ ፊዳላት ከA-G ያሉትን በመውሰድ የምንጠቀምባቸው ናቸው። እነዚህን የእግሊዚኛ ፊደላት የጣሊያንኛ ስያሜዎችን ማለትም ሶል-ፋን በመጠቀም ልንጠራቸው እንችላልን። እንደ አጠቃላይ ሙዚቃ ስሜትን የሚገልጽ፣ ሊጻፍና ሊነበብ የሚችል ዓለማቀፋዊ የመግባቢያ ቋንቋ ሆኖ እንደሚያገለግል በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል።

- ቴያትር በመድረክ ላይ ተዋኒያን ገጸ ባህሪያትን ተላብሰው ለታዳሚዎች በመድረክ ላይ የሚቀርብ ሲሆን የራሱ አለባውያን ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካካል

- **ተዋኒያን**፡- የቴያትሩን ታሪክ በመረዳት በመድረክ ላይ ለታዳሚያን የሚያቀርቡ ሰዎች ናቸው።

- **ታዳሚያን**፡- በተዋኒያን የሚቀርበውን ቴያትር የሚመለከቱ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው።

☞ **መድረክ፦** ቴያትሩ የሚቀርብበት ቦታ ነው።

☞ **ዳይሬክተር፦** የቴያትሩን አጠቃላይ ሂደት የሚመራ ባለሙያ ነው።

☞ **ቪዲዮ፦** በቀጥታ አለያም በቪዲዮ ካሜራ አማካኝነት ተቀርጾ በሞባይል፣ በኮምፒዩተር፣ በቴሌቪዥን ወዘተ የምንመለከተው ተንቀሳቃስ ምስል ነው።

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

በምዕራፍ አንድ የቀረበውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በመጽሀፉ ውስጥ የቀረበውን ጹሁፍ ሳትመለከቱ ጥያቄዎቹን መልሱ። ጥያቄዎቹን ሠርታችሁ ከጨረሳችኩ በኋላ ከመምራችሁ ጋር መልሶቻችሁን አመሳክሩ።

**መመሪያ አንድ፦** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል "እውነት" ስህተት የሆነ ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሽ።

----1. መስመሮች ቴክስቸርን መፍጠር ይችላሉ።

----2. ባለ ሁለት መጠን አውታር የሆነ በመስመር የተከበበ ቦታ ፎርም ነው።

----3. ጎባጣ መስመር የሥያፍ መስመሮች ስሪት ሲሆን በባህሪው ቁጣን፣ ድርቅናን፣ ውጣውረድን ያሳያል።

----4. በስዕል ትምህርት ሲሊንደር፣ ኩብና ሬክታንግል ለፎርም ምሳሌዎች ናቸው።

----5. የሩብ ኖታ ምልክት አንድ ምት በሁለት ድምፅ ይቆጠርለታል።

----6. ሙዚቃ ስናዳምጥ የደስታ ስሜት ብቻ እንጂ የሀዘን ስሜት አይሰማንም።

----7. አንዳንቴ ከምት ምጣኔ አካሄድ ምልክቶች ውስጥ ረጋ ያለ የምት አካሄድ አለው።

----8. ከምት መጠን አካሄድ ምልክቶች ውስጥ ሞደሬቶ መካከለኛ የምት አካሔድ ፍጥነት አለው።

----9. በቴያትር ጥበብ ውስጥ አጠቃላይ የቴያትሩን የክንውን ሂደት ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻ ድረስ የሚመራና የሚቆጣጠር ታዳሚው ነው።

**መመሪያ ሁለት፡-** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ።

---1. በባህሪው የሚፈጥራቸው ስሜቶች የተቀላቀሉ ሲሆን በአንድ በኩል፣ ፍጥነትን፣ እንቅስቃሴን፣ የሚወክል ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ መውደቅን ወይም እየወደቁ መሆንን ያሳያል።

ሀ. ዚግዛግ ሐ. ሰያፍ

ለ.ማዕበላዊ መ. አግዳሚ

---2. ከሚከተሉት ውስጥ ባለ ሁለት አውታር መጠን የሆነው የቱነው?

ሀ. ኩብ ሐ. ሬክታንግል

ለ. ኮን መ. ሲሊንደር

---3. መስራች ቀለማቶች ውስጥ የማይመደበው የትኛው ነው?

ሀ. ቀይ ሐ. አረንጓዴ

ለ. ቢጫ መ. ሰማያዊ

**መመሪያ መመሪያ ሦስት፡** ከዚህ በታች በ(ሀ) ረድፍ የተቀመጡ ጥያቄዎችን በትክክል ካነበባችሁ በኃላ በ (ለ) ረድፍ ከተቀመጡ አማራጮች ጋር አዛምዱ።

| (ሀ) | (ለ) |
|---|---|
| 1. በጣም ከፍተኛ የሆነ የድምፅ መጠን ያመላክታል | ሀ. ክሬሼንዶ |
| 2. ከዝቅተኛ ድምፅ ተነስቶ ወደ ከፍተኛ ድምፅ የሚሄድ | ለ. ፎርቶሲሞ |
| 3. ከፍተኛ የሆነ የድምፅ መጠን | ሐ. ፒያኖ |
| 4. በጣም ለስላሳና በጣም ዝቅተኛ ድምፅ | መ. ፎርቴ |
| 5. ድምፁን ለስለስ በማድረግና ቀስ አድርገን በማውጣት መጫወት | ሠ.ፒያኖሲሞ |

**መመሪያ አራት፡-** የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጭር መልስ በመስጠት መልሱ።

1. የቴያትር ጣራና ግድግዳ ሆነው የሚያገለግሉት የቴያትር አለባዊያንን ዘርዝሩ።
2. በቴያትር ጥበብ ውስጥ የመድረክ አይነቶችን በመጥቀስ ምንነታቸውን ግለጹ።
3. የምታውቋቸውን የሙዚቃ ኖታዎች ዘርዝሩና አጨዋወቱን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞችሁ ተናገሩ

4. የተለዋዋጭ ምልክቶችን ጠቀሜታ ከዘረዘራችሁ በኋላ በተግባር አሳዩ።
5. የሙዚቃ ድምፆች የእንግሊዘኛ ፊደል ውክል B በሶል-ፋ ውክል ማንን ይወክላል።
6. ሙዚቃዊ ድምፅና ከሁካታዊ ድምፅ ስታዳምጡ የሚሰማችሁን የስሜት ልዩነት ተናገሩ።
7. በሙሉ ኖታ፣ በግማሽ ኖታ፣ በሩብ ኖታ፣ በአንድ ስምንተኛ ኖታ አጨዋወት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነቱን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በመናገር ተጫውታችሁ አሳዩ።
8. ቪዲዮ ማለት ምን ማለት ነው?
9. በቴያትር ጥበብ ውስጥ የዳይሬክተሩ ተግባራትን ጻፉ?

# ምዕራፍ 2 የፈጠራ ችሎታን መግለጽ

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ስለ ሙዚቃ ኖታዎች ምንነትና አጨዋወት፣ የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመት አሰራር፣ የወረቀት ሞዛይክ ምንነትና አሰራር፣ የጭቃ ሞዴሊንግ አሰራር ጥበብንና ቀላል የቴያትር ድርሰት አጻጻፍና ትወና ጥበብ የምትመለከቱ ይሆናል።

በምዕራፍ አንድ ላይ የተገነዘባችኋቸው ነገሮች በዚህ ምዕራፍ ላይ መሰረታዊ ሲሆኑ እናንተም የተለያዩ የሙዚቃ፣ የስዕልና የቴያትር መስሪያና መሳሪያዎች በመጠቀም የፈጠራ ችሎታችሁን የምታሳዩበትና አስተያየት በመቀበልና በመስጠት ልምዳችሁን የምታዳብሩበት ነው። በመሆኑም በትምህርት ቤት ብቻ ሳይሆን በቤታችሁም ተጨማሪ ተግባራትን በመስራት የፈጠራ ችሎታችሁን ማሳደግ ይጠበቅባችኋል።

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች፡

### ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፦

- የሙዚቃ ኖታዎችን ትለያላችሁ።
- የሙዚቃ ኖታዎች ምልክቶችን ሰርታችሁ ታሳያላችሁ።
- የተጻፉ የሙዚቃ ኖታዎችን ታነባላችሁ።
- የኪነ ፅሀፊት ምንነትን ትለያላችሁ።
- ፊደላትን ከመሠረታዊ አፃፃፍ ጋር በማገናዘብ ፅፋችሁ ታሳያላችሁ።
- የኪነ ፅሀፊት መሳሪያዎችን አጠቃቀማቸውን ትለያላችሁ፤ በአይነታቸው ለይታችሁ ታሳያላችሁ።
- የሞዛይክ ምንነትን እና አሰራርን ትረዳላችሁ።
- የወረቀት ሞዛይክ ስራዎችን ትሰራላችሁ።

- የህትመት ምንነትን ትረዳላችሁ።
- የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመት ምንነትንና አሰራርን ትገነዘባላችሁ።
- የብሎክ ህትመትን በተግባር ትሰራላችሁ።
- የሞዴሊንግ ምንነትን ትረዳላችሁ።
- በሞዴሊንግ የቅርጽ አሰራር ዘዴ የተሰሩ ኪነ-ቅርጾችን ታደንቃላችሁ።
- የሞዲሊንግ ቅርጽ በተግባር ትሰራላችሁ።
- ከዚህ በፊት የተሰሩ የህጻናት ቴያትሮችን ታደንቃላችሁ።
- ቀለል ያሉ ቴያትሮችን በተግባር ትስራላችሁ።

## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መጻፍና ማንበብ

2.2 ኪነ-ጽህፈት

2.3 የወረቀት ሞዛይክ እና የብሎክ/ሪሊፍ/ ህትመት

2.4 ሞዴሊንግ (በሥዕቃ)

2.5 ተገቢውን ዝግጅትና ልምምድ በማድረግ ቴያትር የመስራት ችሎታን ማሳየት


## 2.1 የሙዚቃ ኖታዎችን መፃፍና ማንበብ

ሙዚቃን ለመፃፍና ለማንበብ ምዕራፍ አንድ ላይ ካያችሁት የሙዚቃ መሰረታዊያን በተጨማሪ የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ፣ የሙዚቃ ቁልፎች፣ የጊዜ አመልካች ምልክቶች፣ የሙዚቃ ድምፆች አስፈላጊ ናቸው። በዚህ ምዕራፍ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የተፃፉ ኖታዎችን ዜማዎችን ታነባላችሁ።

### የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ

የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ የሙዚቃ ኖታዎችን በመጻፊያ ሰሌዳ /ስታፍ በዜማ ለመፃፍና ለማንበብ ይረዱናል። የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ በአምስት መስመሮችና በአራት ክፍት ቦታዎች የሚዋቀርና ሙዚቃን በዜማ ማንበብ የሚያስችል የሙዚቃ አንዱ ክፍል ነው።

የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ መስመሮችም ሆኑ ክፍት ቦታዎች ከታች በመነሳት ወደ ላይ ይቆጠራሉ። የመስመርና ክፈት ቦታዎችን አቆጣጠር እንደሚከተለው እናያለን።





ኖታዎችን የጊዜ አመልካች ምልክቶችን በመጠቀም በምንጽፍበት ወቅት ኖታዎችን በምድብ ለመከፋፈልና ሙዚቃው መጠናቀቁን ለማመላከት የምንጠቀምባቸው የመክፈያ መስመርና የመዝጊያ መስመር የሚባሉ አሉ። እነሱም፦

ሀ. **መክፈያ መስመር** /bar line/፦ እኩል ምት ያላቸውን ኖታዎች ለመከፋፈል የሚረዳ ነጠላ ቋሚ መስመር ነው።

ለ. **ምድብ** /Bar/፦ እኩል ምት ያላቸው ኖታዎች ተከፋፍለው የሚቀመጡበት ወይም በሁለት የመክፈያ መስመሮች መካከል የሚገኝ ቦታ ነው።

ሐ. **መዝጊያ መስመሮች** /Duble bar lines/፦ አንድ ዓረፍተ ነገር ተጽፎ ማለቁን በአራት ነጥብ እንደሚዘጋ ሁሉ የመዝጊያ መስመሮችም አንድ ሙዚቃ ተጽፎ መጠናቀቁን የሚያሳየን ምልክት ነው።



## መልመጃ 1

1. የመክፈያ መስመር፣ ባርና የመዝጊያ መስመሮችን በመጠቀም ኖታዎችን የያዙ ስምንት ባሮችን ጽፋችሁ ለመምራችሁ አሳዩ።

## ድንገተኛ ምልክቶች

## መልመጃ 2

1. ድንገተኛ ምልክቶች ሲባል ከስማቸው በመነሳት ምን እንደገመታችሁ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ። ለግምታችሁ መነሻ የሆኗችሁ ምክንያቶች ምን እንደሆኑም አብራሩ።
2. የሙዚቃ መክፈቻ ቁልፎች የድምጾችን ስያሜ እንዴት እንደሚወስኑ አሰላስላችሁ ለመምህራችሁ ተናገሩ።

በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ በሙዚቃ መክፈቻ ቁልፎች አማካኝነት የሚሰየሙት የሙዚቃ ድምፆች የቁልፉና የቦታዎች መለያየት ድምጾች የተለያየ ቃና እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። የተሰየሙት የድምጽ ርቀቶች የሙሉና የግማሽ ድምፅ ርቀት አሏቸው። በሙዚቃ ሳይንስ እውቅና ያገኙት የድመፅ ርቀቶች የግማሽ ድምጽ ርቀት (Semitone) እና የሙሉ ድምጽ (whole tone) ርቀት በመባል ይታወቃሉ። በሙዚቃ ትንሹ የድምጽ ርቀት የግማሽ ድምጽ ርቀት (Semitone) ነው። በሙዚቃ ቅንብር ሂደት ደራሲው ድምፆችን መጨመር፣ መቀነስና ወደነበሩበት መመለስ ይፈልጋል። ለዚሁ ተግባር ጥቅም ላይ የሚውሉት የድምጽ መጨመርንና መቀነስን እንዲሁም ወደነበሩበት መመለስን የሚናገሩ ምልክቶች ድንገተኛ ምልክቶች ይባላሉ። ስለዚህ ድንገተኛ ምልክቶች በግማሽ ወይም በሙሉ ድምጽ የሚጨምሩ፣ የሚቀንሱና ወደነበረበት ቦታ የሚመልሱ ምልክቶች ናቸው።


ይህንን በሰንጠረዥ እንደሚከተለው እናያለን።

| ድንገተኛ ምልክቶች | ስያሜ | ተግባር |
|---|---|---|
| # | ሻርፕ | ማንኛውንም ድምጽ በግማሽ እንዲጨምር ያደርጋል። |
| ♭ | ፍላት | ማንኛውንም ድምጽ በግማሽ እንዲቀንስ ያደርጋል። |
| X | ደብል ሻርፕ | ማንኛውንም ድምጽ ሙሉ ድምጽ እንዲጨምር ያደርጋል። |
| ♭♭ | ደብል ፍላት | ማንኛውንም ድምጽ ሙሉ ድምጽ እንዲቀንስ ያደርጋል። |
| ♮ | ናቹራል | ጨምሮ ወይም ቀንሶ የነበረውን ድምጽ ወደ ነበረበጽ ድምጽ የሚመልስ ምልክት ነው። |

## የሙዚቃ መክፈቻ ቁልፎች


የሙዚቃ መክፈቻ ቁልፎች ከስታፍ በስተግራ መጀመሪያ ላይ የሚቀመጡ ናቸው። አገልግሎታቸው የሙዚቃ ድምጾች ስያሜ እንዲያገኙ፣ መፃፍና መነበብ እንዲችሉ ማድረግ ነው። በዋነኛነት የሚታወቁት የጅ እና የኤፍ ቁልፎች ሲሆኑ ስያሜያቸውን ያገኙትም ቁልፎቹ የሚነሱበትን ቦታ መነሻ ተደርጎ ነው። ምሳሌ ጅ ቁልፍ መነሻው ከሁለተኛው መስመር G (Sol) ሲሆን የኤፍ ቁልፍ መነሻ ደግሞ ከአራተኛው መስመር F (Fa) ስለሆነ ነው። ጅ ቁልፍ ከመካከለኛ ድምጽ እስከ ቀጭን ድምጽ ለመጻፍና ለማንበብ የሚያገለግል ሲሆን የኤፍ ቁልፍ ደግሞ ከዚህ በተቃራኒው ከመካከለኛ እስከ ወፍራም ድምጽ ለመጻፍ የምንጠቀምበት የቁልፍ አይነት ነው።







የጅ ቁልፍ አመልካች ምልክት ቅርጽና አቀማመጥ

የጅ ቁልፍ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ሲቀመጥ ምን እንደሚመስል ከዚህ በላይ ያለውን ምስል መመልከት የሚቻል ሲሆን የክፍት ቦታዎችና መስመሮች ስያሜ ደግሞ እንደሚከተለው ቀርቧል።












የጂ ወይም የትሬብል ቁልፍ የመስመርና ክፍት ቦታ ስያሜ

የኤፍ ባዝ ቁልፍ ምልክትና አቀማመጥ









## መልመጃ 3


1. የጂ ቁልፍና የኤፍ ቁልፍ የመስመሮችንና የክፍት ቦታዎችን የድምጽ ስያሜዎችን ዘርዝሩና ዘምሯቸው።
2. እነዚህን ከላይ በምስሉ የተቀመጡትን የመስመርና ክፍት ቦታ በቀላሉ ልታስታውሱበት የምትችሉበት መንገድ ፈልጋችሁ ተናገሩ።

## ረዳት መስመሮች


ከስታፍ በላይና በታች የወጡና የወረዱ ድምፆችን ለመፃፍ የሚያገለግሉ መስመሮች ናቸው። ረዳት መስመሮች በሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ውስጥ መካተት ያለቻሉ ወፍራምና ቀጭን ድምጾችን ለመጻፍ የሚያገለግሉ አጫጭር መስመሮች ናቸው።





በ 'ጅ' ቁልፍ የረዳት መስመሮች ከስታፍ በላይ አቀማመጥ





በ ‘ድ’ ቁልፍ የረዳት መስመሮች ከስታፍ በታች አቀማመጥ




በኤፍ ቁልፍ የረዳት መስመሮች ከስታፍ በላይ ሲቀመጡ




በኤፍ ቁልፍ ላይ የረዳት መስመሮች ከስታፍ በታች ሲቀመጡ




## መልመጃ 4

1. ከዚህ በላይ ከተሰጧችሁ በተጨማሪ ከሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ በላይና በታች በረዳት መስመሮች አማካኝነት የተጻፉ ኖታወችን ተለማመዱ። ስትለማመዱ እግረ መንገዳችሁን የጊዜ አመልካች ምልክት የሚባሉትን ለመጠቀም ሞክሩ።
2. የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳን በመጠቀም ኖታዎችን ዜማ መፍጠር እንዲችሉ በማድረግ ጽፋችሁ በማንበብ ተለማመዱ።

## የጊዜ አመልካች ምልክቶች

አንድን የተፃፈ ዜማ ለመጫዎትና የጊዜውን ሂደት ለመወሰን የሚያስችሉ በሁለት ፍራክሽን መሰል ቁጥሮች የሚፃፉ ምልክቶች ናቸው። ቁጥሮችም የላይኛውና የታችኛው ተብለው የሚከፈሉ ሲሆን የላይኛው ቁጥር የሚያመለክተው በአንድ ምድብ ስንት ምት እንዳለ የሚጠቁም ሲሆን የታችኛው ቁጥር ደግሞ የኖታውን ዝርያ የሚያመለክት ነው።

| | |
|---|---|
| 4<br>4 | የላይኛው ቁጥር በአንድ ባር ውስጥ አራት ምት እንዳለ ያመለክታል። |
| | የታችኛው 4 ቁጥር በሩብ ኖታ የሚመነዘር የሙሉ ኖታ ዝርያ መሆኑን ያሳያል። |
| 3<br>4 | የላይኛው ቁጥር በአንድ ባር ውስጥ ሦስት ምት እንዳለን ያሳየናል። |
| | የታችኛው 4 ቁጥር በሩብ ኖታ የሚመነዘር የሙሉ ኖታ ዝርያ መሆኑን ያሳያል። |
| 2<br>4 | የላይኛው ቁጥር በአንድ ባር ውስጥ ሁለት ምት እንዳለን ያሳየናል። |
| | የታችኛው 4 ቁጥር በሩብ ኖታ የሚመነዘር የሙሉ ኖታ ዝርያ መሆኑን ያሳያል። |

**ምሳሌ**



ከዚህ በታች የቀረቡትን ኖታዎች የጊዜ አመልካች ምልክቱን መሰረት በማድረግ ክፍት ቦታውን ሙሉ።



## መልመጃ 5

1. የጊዜ አመልካች ምልክቶችን በመጠቀም የተለያዩ ኖታዎችን ጽፋችሁ በማንበብ የተሰማችሁን ስሜት ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. መምህራችሁ በስታፍ ላይ የተጻፉ ድምጾችን በሙዚቃ መሳሪያ ሲጫወቱላችሁ አብራችሁ ዘምሩ።

### 2.1.1 ዜማን ማንበብ


ኖታዎች በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ሲቀመጡ የራሳቸው የሆነ ህግና ስርዓት አላቸው። ይኸውም ዘንግ ያላቸው ኖታዎች በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ ሲቀመጡ የኖታዎች ራስ ከሦስተኛው መስመር በላይ ሲሆኑ ዘንጋቸው ወደ

ታችና ከሦስተኛው መስመር በታች ከሆኑ ደግሞ ዘንጋቸው ወደ ላይ በማድረግ ይጻፋሉ። ነገር ግን ሦስተኛው መስመር ላይ ከሆኑ ወደ ሁለቱም አቅጣጫ ሊጻፉ ይችላሉ።


ሀ.  ለ.  ሐ. 

ሌላው ደግሞ ኖታዎች በስታፍ ላይ ሲቀመጡ ክፍት ቦታ ላይ ከሆነ የሚቀመጡት ራሳቸው ከመስመርና ከመስመር መካከል መሆን አለባቸው። መስመር ላይ ከሆነ የሚቀመጡት የኖታዎች የራሳቸው ክፍል መስመሩ እኩል ሊከፍላቸው ይገባል።

ክፍት ቦታ ላይ ሲቀመጡ




መስመር ላይ ሲቀመጡ



ከዚህ በታች የቀረቡ በስታፍ ላይ የተፃፉ ኖታዎች በአካባቢያችሁ በምታገኙት የሙዚቃ መሳሪያ አጅባችሁ ዘምሩ።






## 2.2 ኪነ-ጽሀፈት

### 2.2.1 የኪነ-ጽሀፈት ምንነትና የእጅ ማፍታቻ መስመሮች ጥናት

ኪነ-ፅሕፈት ፊደላትን በብራና፣ በወረቀት ወይም በሌላ ነገር ላይ በፊደል ምልክትነት በመወከል ውብ አድርጎ የመቅረጽ ወይም የመጻፍ ጥበብ ነው። ይህም ተግባራዊ የሚሆነው በነጠላ፣ በድርብ፣ በጥላና ብርሃን፣ እንዲሁም በጌጥ የአሰራር ዘዴ አማካኝነት ነው።

በግራፊክስ ጥበብ ውስጥ ኪነ-ጽህፈት ከፍተኛ ቦታ ያለው ሲሆን ለማስታወቂያና ለፖስተር ሥራዎች የመግለጫና የአርዕስት ጽሑፎችን በልዩ ልዩ የአጻጻፍ ዘዴ አጉልቶ ለማቅረብ አስፈላጊ ነው።

የኪነ-ጽህፈት ችሎታን ለማግኘት መሰረታዊ የሆኑ የእለካክና የፊደል መጻፊያ መሳሪያዎችን ትክክለኛ አያያዝና አጠቃቀም ቴክኒክን በቅድሚያ በልምምድ ማግኘት ያስፈልጋል። ይህ ጥበብ የአእምሮንና የእጅን የተቀናጀ እንቅስቃሴ የሚጠይቅ በመሆኑ በመጀመሪያና የእጅ ጡንቻዎችን እንደ ልብ ለማዘዝ እንዲቻል ልዩ ልዩ መስመሮችን ነጻ በሆነ መንገድ ያለ ማስመሪያ እየሰሩ መለማመድ ያስፈልጋል።

ፊደላትንና ቁጥሮችን ለመጻፍ በመጀመሪያ የፊደላቱንና የቁጥሮቹን ቅርጽ እና መጠን በደንብ መረዳት የሚጠይቅ ሲሆን ከዚህ በፊት ግን የተለያዩ መስመራትን በተለያየ አቅጣጫ በማስመር ተደጋጋሚ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል።

## በልምምድ ጊዜ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

ለእጅ የመስመር ነጻነትን መስጠትና እርሳሱን ወይም ብዕሩን ረዘም አድርጎ መያዝና መስመሮቹን/ቋሚ፣ አግድም፣ ሰያፍ፣ ከርቭ፣ ሩብ ክብ፣ ግማሽ ክብና ሙሉ ክብን ደጋግሞ መስራት ለዚህም ተግባር ማስመሪያ መጠቀም የለባችሁም። የመስመሮቹን ሁኔታ ማቅጠን፣ ማወፈር፣ ማጠጋጋትና ማራራቅን ወዘተ መጠቀም ያስፈልጋል።

### 2.2.2 የነጠላ ፊደላትና የቁጥሮች አጻጻፍ ልምምድ

እንደሚታወቀው ኪነ-ጽህፈት ፊደላትን በልዩ ልዩ ዲዛይን እያስጌጡ ለተመልካች በሚማርክ ሁኔታ የሚቀርብበት ጥበብ ነው። ስለሆነም ይህንን ማድረግ እንዲቻል በመጀመሪያ የፊደላትን ቅርጽ አቋምና የአጻጻፍ ዘዴን በሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል። ትክክለኛ የአጻጻፍ እውቀትን ለማግኘት ደግሞ ግልጽ የሆነ ያለካክና የፊደላት መጻፊያ መሳሪያዎችን ትክክለኛ አያያዝና አጠቃቀም በቅድሚያ በልምምድ ማግኘት አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ነጠላ ፊደላትን እና ቁጥሮችን ለመጻፍ ተጓዳኝ መስመሮችን አስምሮ መጠቀም ስራውን እድንለምደው ከማስቻሉም በላይ ፊደላትም ሆነ ቁጥሮች እኩል ቁመትና የተስተካከለ ውፍረት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

## ነጠላ የአማርኛ ፊደላት ልምምድ

የአማርኛ ፊደላት የራሳቸው የሆነ ቅርጽ፣ መጠንና የአጻጻፍ ስርዓት ያላቸው ስለሆነ ተማሪዎች እናንተም በሚከተለው ምሳሌ መሰረት ተደጋጋሚ ልምምድ በማድረግ ክህሎታችሁን ማሳደግ ይጠበቅባችኃል።



የነጠላ ጽሑፍ ምሳሌ


### መልመጃ 6


1. ከዚህ በላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት መለማመጃ በማዘጋጀት በነጠላ መስመር ብቻ የፈለጋችሁትን የአማርኛ ፊደላት በመጻፍ ለመምህራችሁ በማሳየት አስተያየቶችን ተቀበሉ።


## የነጠላ የእንግሊዝኛ ፊደላት አጻጻፍ

የእንግሊዝኛ ፊደላት ሁለት አይነት አቀራረብ ያላቸው ሲሆን እነሱም ትልቁና ትንሹ ፊደላት ናቸው። ትልቆቹ ፊደላት ከላይና ከታች ወጣ ገባ ሳይኖረው በእኩል መጠን በአግድም በተሰመረ መስመር ላይ ማረፍ አለባቸው። የእያንዳንዱ ፊደላት የጎን ውፍረት እኩል መሆን ይኖርባቸዋል። በሌላ በኩል የትንሾቹ ፊደላት አጻጻፍ ደግሞ እንደ ፊደላቶቹ የቅርጽ ሁኔታ ከላይ ጭንቅላታቸው ከታች እግራቸው የሚረዝሙ አሉ። እነሱም እንደ መጠናቸው በአግድም መስመር ላይ በእኩል ደረጃ ማረፍ አለባቸው። የጎን ውፍረታቸውም አንድ አይነት መሆን ይገባዋል። የነዚህን የፊደላት አጻጻፍ መሰረታዊ ዘዴ የሚከተለውን ምሳሌ በመመልከት መረዳት ይኖርባችኃል።


# ትልቁ እንግሊዝኛ ፊደላት መለማመጃ ምሳሌዎች









## ትንሹን የእንግሊዝኛ ፊደላት መለማመጃ ምሳሌዎች





### የነጠላ ቁጥሮች አጻጻፍ

ቁጥሮች ልክ እንደ ፊደላቶች የራሳቸው የአጻጻፍ ስርዓት ያላቸው ሲሆን በሚከተለው ምሳሌ መሰረት ተደጋጋሚ ልምምድ በማድረግ የጽህፈት ክህሎታችሁን አዳብሩ።



## መልመጃ 7


1. ከዚህ በላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት መለማመጃ በማዘጋጀት በነጠላ መስመር ብቻ የፈለጋችሁትን ቁጥሮች በመጻፍ ለመምህራችሁ በማሳየት አስተያየቶችን ተቀበሉ።

### 2.2.3 የድርብ ፊደላት አጻጻፍ ልምምድ

#### 2.2.3.1 በስኩዌር ወረቀት ላይ ድርብ ጽህፈት

ከሌሎች ወረቀቶች ይልቅ የስኩዌር ወረቀት ለዚህ ተግባር ልምምድ የሚመች ሲሆን ተደጋጋሚ ልምምዶችን በማድረግ ውብ የሆኑ ፊደላቶችን የመጻፍ ጥበብን መላበስ ይቻላል። የኪነ-ጽህፍት ስራዎችን ከሰራችሁ በኃላ እርስ በርስ ሀሳብ መለዋወጥ፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለይቶ የማውጣትና ገንቢ አስተያየቶችን በነጻነት የመስጠትና በቀረቡት አስተያየቶችም ተጠቅሞ ጉድለቶችን የማረም ልምድ ማዳበር ይጠበቃል።

ከዚህ በታች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት መለማመጃ ወረቀት በማዘጋጀት በድርብ አጻጻፍ የፈለጋችሁትን ፊደላት በመጻፍ ለመምህራችሁ በማሳየት አስተያየቶችን ተቀበሉ።



የፊደላትን የተለያየ መጠን፣ ስፋትና አወቃቀር የሚያመለክት ጽሁፍ

### 2.2.3.2 በተጓድኝ መስመሮች አማካኝነት ድርብ ጽህፈት

ሁለት ተጓዳኝ መስመሮችን በማስመር ጽሑፎችን መጻፍ ፊደላቶቹ ወይም ቁጥሮቹ ከተፈለጉበት ቦታ ከፍ ወይም ዝቅ ብለው እንዳይቀመጡ ያደርጋል።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ | ለ | ሐ | መ | ሠ |
| ረ | ሰ | ሸ | ቀ | በ |
| ተ | ቸ | ኀ | ነ | ኘ |
| አ | ከ | ኸ | ወ | ዐ |
| ዘ | ዠ | የ | ደ | ጀ |
| ገ | ጠ | ጨ | ጰ | ጸ |
| ፀ | ፈ | ፐ | | |

## መልመጃ 8

1. ከዚህ በላይ በተሰጠው ምሳሌ መሰረት መለማመጃ በማዘጋጀት በድርብ ጽሑፍ የፊለጋችሁትን ፊደላት በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።

### 2.2.3.3 በሰፊ ብዕር ማርከር ወይም ሁለት እርሳሶችን አስሮ የድርብ ጹሁፍ ልምምድ

ፊደላትንም ሆነ ቁጥሮችን መጻፍ በምንፈልግበት ጊዜ ሁለት ተጓዳኝ መስመሮችን ካሰመርን በኃላ ስፋት ባለው ብዕር ማርከር ወይም ሁለት እርሳሶችን አንድ ላይ በማሰር መስመር ጠብቆ ሰፋፊ ፊደላትን መጻፍ ይቻላል። ተጓዳኝ መስመሮች የሚጠቅሙን የጽሑፎችን ራስጌና ግርጌ በእኩል ቦታ እንዲቀመጡ ነው።

**መልመጃ 9**

1. ሁለት እርሳሶችን አንድ ላይ በማሰር የተለያዩ ፊደላት በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።


### 2.2.3.4 ፊደላትን በጥላና ብርሀን (በጌጠኛ አጻጻፍ) ዘዴ መጻፍ


ይህ የፊደላት ያጻጻፍ ዘዴ የበለጠ ውበት ያላቸውንና የሰውን አይን የሚስቡ ፊደላት የሚጻፉበት የአጻጻፍ ሁኔታውም መጀመሪያ የፊደላቱን ዋና አካል መጻፍ ቀጥሎ ደግሞ ጥላ መሆን የሚገባውን ክፍል መጻፍና መቀባት ነው።


ጥላና ብርሀንን ስንጠቀም ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ይኸውም የመጀመሪያ ፊደል ጥላ ወደ ግራ የተጻፈ ከሆነ የሚቀጥለው ፊደል ጥላ መተመሳሳይ መንገድ በቀኝም ከሆነ እንደዚሁ መጻፍ አለበት። የጥላና ብርሀን ወይም ጌጠኛ ፊደላት የተለያየ የአጻጻፍ ዘዴዎች ያሏቸው ስለሆኑ በባለሙያዎች የተሰሩ ስራዎችን በመመልከትና የራስን ፈጠራ በማከል ሰፊ ልምምድ ማድረግ አለባችሁ።


**መልመጃ 10**

ከዚህ በታች በተሰጠው ምሳሌ መሰረት መለማመጃ ወረቀት በማዘጋጀት በጌጠኛ አጻጻፍ የፈለጋችሁትን ፊደላት በመጻፍ ለመምህራችሁ አሳዩ።









የጥላና ብርሃን ወይም የጌጠኛ ፊደላት አጻጻፍ ምሳሌ

## 2.3 የወረቀት ሞዛይክና የብሎክ /ሪሊፍ/ ህትመት

### 2.3.1 የሞዛይክ ምንነት፣ መስሪያዎችና አሰራር

ሞዛይክ በጣም ትንንሽ የሆኑ ቁርጥራጭ ነገሮችን በመጠቀም ትልቅ ስዕልን በማጣበቅና በመለጠፍ የአሰራር ዘዴ በሰሌዳ ላይ መፍጠር መቻል ነው። የምንቆራርጣቸው ነገሮች በቀለምና በመጠን እንዲሁም በቅርጽ የተለያዩ መሆን ይኖርባቸዋል።

የሞዛይክ ስራዎችን ለመስራት በምንዘጋጅበት ጊዜ በአካባቢያችን የሚገኙ ነገሮችን በአይናችን ልብ ብለን በመመልከት ቀለማቸውን፣ የመለስለስና የመሻከር ሁኔታቸውን፣ ቅርጻቸውን፣ የመድመቅና የመፍዘዝ ሁኔታቸውን በደንብ መመልከትና መገንዘብ ይኖርብናል። ይሄም ስራችን የተሻለና ጥራት እንዲኖረው ያደርጋል።

የሞዛይክ ጥበብ የሚሰራባቸው ነገሮች የብርጭቆ ስብርባሪዎች፣ የብረታ ብረት ቁርጥራጮች፣ የተለያዩ ወረቀቶች፣ ጨሌ (ዶቃ)፣ እብነ በረድና የመሳሰሉት ናቸው።

የሞዛይክ ስራን በምንሰራበት ጊዜ በመጀመሪያ ልንሰራው ያሰብነውን በንድፍ ሰሌዳ ላይ በመንደፍና የጥቁረትና የንጣት ደረጃውን መለየት።

በመቀጠል የሞዛይክ ጥበብን የምንሰራበትን ማቴሪያል መለየትና በተለያዩ ቅርጾች መቆራረጥ፣ የብርሃና የጥላ ሁኔታውን መለየት፣ የመፍዘዙን እና የመድመቁን ሁኔታ መሰረት አድርገን ለያይተን ማስቀመጥ።

ከዚያም የምንፈልገውን ቦታ በንድፍ ስራው ላይ ኮላና መሰል ነገሮች በመቀባት በየደረጃው ማጣበቅ ማለትም የብርሃንና ጥላ ሁኔታውን እንዲሁም ቴክስቸሩን ወዘተ መሰረት አድርገን መስራት ማለት ነው። በመጨረሻ ቫርኒሽ በመቀባት እንደ አስፈላጊነቱ ማሳመር እንችላለን።





ስዕል 1 በሞዛይክ ጥበብ የተሰሩ ስራዎች

የሞዛይክ ስራዎችን እንደ አስፈላጊነቱ ቀለማትን እየተጠቀምን ማስጌጥና ማስዋብ እንችላለን። ሞዛይክን የምንሰራባቸው ነገሮች በጣም ብዙ ነገሮች

እንደሆኑ ተረድታችኋል:: አሁን ደግሞ በዚህ የክፍል ደረጃ ወረቀቶችን ተጠቅማችሁ ሞዛይክን ትሰራላችሁ።

### 2.3.2 የወረቀት ሞዛይክ

በቅድሚያ ወረቀትን በመጠቀም ኮላዥ መስራት እንደሚቻል ሁሉ ሞዛይክንም መስራት እንደሚቻል መረዳት ያስፈልጋል። የወረቀት ሞዛይክ ጥበብ ለህጻናት በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ጥበቦች አንዱ ሲሆን ህፃናት የተለያዩ ቀለም ያላቸው ወረቀቶችን፣ መጽሄቶችን፣ መጽሃፍቶችን፣ ጋዜጦችን ወዘተ በመቆራረጥና በመለጣጠፍ ስለ ውበት ያላቸውን ግንዛቤ እና የፈጠራ ችሎታቸውን የሚያሳድጉበት ነው።

#### የወረቀት ሞዛይክ አሰራር

1. የተለያዩ ቀለም ያላቸው ወረቀቶችን፣ መጽሄቶችን፣ መጽሃፍቶችን ወዘተ ማሰባሰብ
2. የተሰበሰቡትን መስሪያዎች በሚፈለገው ቅርጽና የቀለም ፍካት ደረጃ በትንንሽ መቆራረጥ። የምንቆራረጥበት መጠን የተለያየ ሊሆን እንደሚችል መረዳት ያሥፈልጋል።
3 በወረቀት፣ በካርቶን ወዘተ ላይ የተነደፈውን ንድፍ ማጣበቂያ መቀባትና የተቆራረጡትን ቁርጥራጮች በቦታ ቦታቸው እንደ ጥቁረትና ንጣጣቸው መለጣጠፍ።
4. አስፋላጊ ከሆነ በስዕሉ ጀርባ ላይ ስዕሉ ከተሰራባቸው ቀለማቶች ተመሳሳይነት የሌላቸው ወረቀቶችን መለጣጠፍ ይሄም ስዕሉ ይበልጥ ውበት እንዲኖረው ያደርገዋል።
5. የተሰራውን ሞዛይክ ፅሀይ ላይ እንዲደርቅ ማድረግ።

#### መልመጃ 11

1. የተለያዩ ወረቀቶችን በመጠቀም ሞዛይክን በመስራት ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምራችሁ አሳዩ።



ስዕል 2 የተለያዩ የወረቀት ሞዛይክ ስራዎች

### 2.3.3 የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመት

ህትመት የአንድን ነገር ምስል፣ ፁሁፍ፣ ዲዛይን ከሰራን በኋላ በመቅረፅ፣ በመፈልፈል (በመቧጠጥ) አሊያም በተፈጥሮ የምናገኛቸውን ነገሮች በቀላሉ ጀርባቸውን በመቀባት በሌላ አካል ላይ በምንፈልገው ብዛት ደግሞ ደጋግሞ ማራባት ማለት ነው።

የህትመት ስራዎች ብዙ አይነቶች ሲሆኑ በከፍተኛ የህትመት መሳሪያዎች የሚሰሩ ለምሳሌ ሲልክ ስክሪን ህትመት፣ የፎቶ ግራፍ ህትመት በቀላሉ ሊሰሩ ከሚችሉት ደግሞ የቀጥታ ህትመት፣ የብሎክ ህትመት (የድንች፣ የካሮት ወዘተ) እና የወረቀት ስቴንስል ህትመት ተጠቃሾች ናቸው።

የህትመት ስራ የሚከናወነው በከፍተኛ መሳሪያዎች ቢሆንም ለምሳሌ ቲ-ሸርቶች፣ ኩፍያዎች፣ ማህተሞች ወዘተ በቀላሉ ግን በአካባቢያችን በምናገኛቸው የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ ነገሮችን በመጠቀም የህትመት ስራን በቀላሉ መስራት እንደሚቻል መረዳት ያስፈልጋል። በዚህ የክፍል ደረጃ የህትመት መሰረታዊ አሰራር ዘዴዎች የቀጥታ ህትመት፣ የወረቀት ስቴንስል ህትመትና የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመት ተብለው ይጠራሉ።

በታችኛው የክፍል ደረጃ እንደ ተማራችሁት የቀጥታ ህትመት ብዙም የግል ፈጠራችንን ሳንጨምርበት በአካባቢያችን የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነገሮችን ቴክስቸራቸውን በቀለም በመቀባት በቀጥታ በወረቀት፣ በጨርቅ፣ በእንጨት፣ በግድግዳና በመሳሰሉት ነገሮች ላይ የማተም ሂደት ሲሆን መረዳትና መግንዘብ ያለብን ነገር ቀለም የምንቀባው ክፍል ሻካራውን መሆን አለበት። የቀጥታ ህትመት ተግባርን ለማከናወን ከሚያስፈልጉን መሳሪያዎች መካከል የተለያዩ አበባዎች፣ ቆርኪ (የቢራ፣ የለስላሳ፣ የቅባት ክዳኖች)፣ እጆቻችንና ጣቶቻችን፣ ጫማዎች ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው።

የስቴንስል ህትመት ደግሞ በቀላሉ በወረቀት ላይ ተፈላጊውን ንድፍ በመስራት በከተር ወይም በምላጭ ቀለም እንዲነካው የምንፈልገውን ክፍል ቀርጾ በማውጣት በሌሎች ወረቀቶች በቀዳዳዎቹ አማካኝነት ቀለም በስፖንጅ ወይም በጨርቅ በመጫን ህትመቱ በሌላ አዲስ ወረቀት ላይ እንዲወጣ የምናደርገው ዘዴ ነው። ሦስተኛውና በዚህ ክፍል ደረጃ በስፋት የምንመለከተው የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመትን ነው።

## የብሎክ (ሪለፍ) ህትመት

የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመት አይነት የሚታተመውን ክፍል ከማይታተመው ለይቶ በማውጣት የሚከናወን ሲሆን ይህም እንዲታይ የማንፈልገውን ነገር በመቦርቦርና በመቧጠጥ የምንፈልገውን ነገር ደግሞ እንዲወጣ በማድረግ ቀለሙን በመቀባት በሌላ ወረቀት ላይ ማተም ነው።

ለዚህ የአሰራር ዘዴ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው ለተለያዩ ድርጅቶች የሚጠቀሙበት ማህተምን ነው። ማህተም በምናይበት ጊዜ እንዲታተም የተፈለገው ነገር ከፍ ብሎ ያልተፈለገው ነገር ደግሞ ጎድጉዶ ይታያል።

በዚህ አሰራር ግን መታሰብ ያለበት ጉዳይ እንዲታተም የምንፈልገው ነገር በተቃራኒው ዞሮ መቀረፅ ይኖርበታል። ይህ ማለት ለምሳሌ ፊቱን ወደ ቀኝ የዞረ ሰው ከሆነ እንዲታተም የምንፈልገው ወደ ግራ አድርገን በመፈልፈል (በመቅረፅ) መስራት ይጠበቃል።

የብሎክ /ሪሊፍ/ ህትመት ከሚሰራባቸው ነገሮች ውስጥ ድንች፣ ካሮት፣ ቡሽ የሆኑ ጫማዎች፣ ቀይ ስር፣ ጎማ፣ ፕላስቲክ፣ ሳሙና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

## 2.3.4 የድንች ህትመት


ድንች ቀላል ከሚባሉት የብሎክ ህትመት መስሪያዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን የአሰራር ሁኔታውም የሚከተለውን ይመስላል።

- ድንቹን፣ (ቀይስሩን) እኩል ለኩል ለመሃል መቁረጥ
- በተቆረጠው የድንች ክፍል ላይ የምንፈልጋቸውን ምስል ወይም ዲዛይን መንደፍ
- ከምስሉ (ዲዛይኑ) ካረፈበት ውጭ ያለውን ክፍል በስለት በመፋቅ ምስሉ ወጣ እንዲል ማድረግ
- ወጣ ብሎ የሚታየውን ምስል ወይም ዲዛይን ቀለም በመቀባት የህትመት ውጤት እንዲያርፍበት በተፈለገው ቦታ ለምሳሌ ወረቀት፣ ጨርቅ ላይ እያተሙ ማውጣት ነው። አሰራሩም የመከተለውን ምስል ተመልከቱ።



ማሳሰቢያ፦ የምንሰራቸው ምስሎች በድንቹ ላይ ዞሮ መሳልና መቅረፅ ይኖርበታል።





ስዕል 3 የድንች ህትመት

**መልመጃ 12**

1. ድንችን በመጠቀም የሚያስደስታችሁን ምስል በመሳልና በመቅረጽ የብሎክ (ሪሊፍ) ህትመትን ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ በማሳየት ሀሳብ ተለዋወጡ።

## 2.3.5 የሳሙና ሪሊፍ ህትመት

እንደ ድንች ሁሉ ሳሙናም ቀላል ከሚባሉ የብሎክ ህትመት መስሪያዎች የሚመደብ ሲሆን አሰራሩም እንደሚከተለው ነው።

- **አስፈላጊ ግብአቶችን ማሟላት፡-** ጠፍጣፋ ሳሙና፣ እርሳስ ወይም አስክርቢቶ፣ ከተርና ተያያዝኝ መቁረጫዎች፣ የስፖንጅ ቁርጥራጮች፣ ቡርሽ፣ ቀለም፣ ጨርቅ፣ ወረቀት ወዘተ
- በሳሙናው ላይ የምንፈልጋቸውን ምስል ወይም ዲዛይን መንደፍ
- ከምስሉ (ዲዛይኑ) ካረፈበት ውጭ ያለውን ክፍል በስለት በመፋቅ ምስሉ ወጣ እንዲል ማድረግ
- ወጣ ብሎ የሚታየውን ምስል ወይም ዲዛይን ቀለም በመቀባት የህትመት ውጤት እንዲያርፍበት በተፈለገው ቦታ ለምሳሌ ወረቀት፣

ጨርቅ ላይ እያተሙ ማውጣት ነው።

**የአሰራሩ ሁኔታ የሚከተለውን ይመስላል።**




ስዕል 4 የሳሙና ብሎክ (ሪሊፍ) ህትመት አሰራር ደረጃዎች



ስዕል 5 የመጨረሻው የስራ ውጤት ታትሞ ሲታይ

ሳሙናዎችን በመጠቀም የሚያስደስታችሁን ምስል በመሳል እና በመቅረጽ የብሎክ(ሪሊፍ) ህትመትን ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻቹህና ለመምህራችሁ በማሳየት ሀሳብ ተለዋወጡ።

## 2.4 ሞዴሊንግ (በጭቃ)

### የኪነ-ቅርጽ ጽንሰ-ሀሳብ

የቅርፅ ጥበብ ከእይታዊ ጥበባት ዘርፎች ውስጥ አንዱ ነው። የኪነ ቅርጽ ጥበብ ከጥንት ጀምሮ ሲሠራበት የቆየ ሲሆን በዋነኛነት ከሌሎች የእይታዊ ጥበባት አቀራረቦች ለየት የሚያደርገው ጉድፍ፣ ቀለም ቅብ፣ ሞዛይክና የመሳሰሉት በዝርግ ነገሮች ላይ የሚሠሩና ጠፍጣፋ ሆነው የሚታዩ ሲሆን የኪነ ቅርጽ ጥበብ ደግሞ በእጃችን ልንዳስሠው እና እየዞርን ልናየው የምንችለው መሆኑ ነው።

የኪነ ቅርፅ ጥበብ በተለያዩ መሣሪዎች የሚሰራና የተለያዩ አይነት አቀራረቦች ያሉት ሲሆን 4 የመስሪያ ስልቶች (ቴክኒኮች) አሉት። እነሱም፦ ሞዴሊንግ፣ ካርቪንግ፣ አሰምብሊንግና ካስቲንግ ናቸው። በዚህ የክፍል ደረጃ ከመሰረታዊ ስልቶች አንዱ የሆነውን ሞዴሊንግ የምትማሩ ይሆናል።

### 2.4.1 የሞዴሊንግ ተግባር ስራ

ሞዴሊንግ በዋናነት የተቦካ ጭቃን በቀላሉ ከአካባቢያችን ልናገኝ ከምንችለው ንፁህ የአፈር ዓይነት ውሃን ተጠቅመን በማቡካትና ለቅርፅ ስራ በማዘጋጀት ጭቃውን እየጨመርን የምንፈልገው የመጨረሻ ስራ እስክናገኝ ድረስ የምንስራበት ስልት ሲሆን ስራው በአብዛኛው የሚሰራው እጅን በመጠቀም ነው።

ሞዴሊንግ በሁለት አይነት የኪነ ቅርጽ አቀራረብ ተግባራዊ የሚሆን ሲሆን እነዚህም በሪሊፍ እና በዙሪያ ቅርጽ ነው።

በሪሊፍ መልኩ የሚሠሩ የሞዴሊንግ ኪነ ቅርጽ ሥራ የሚሠራው ጠፍጣፋ ወይም ዝርግ በሆነ ቁሳቁስ ላይ ሆኖ የተለያዩ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሚሰራውም ስራ ወደ ላይ ከፍ ብሎ ሊታዩ በሚችሉ መልኩ ነው። የሪሊፍ ጥበብን ለመስራት የተለያዩ መስሪያዎችን መጠቀም የሚቻል ሲሆን በዚህ ደረጃ ግን የጭቃ ሪሊፍ ስራን እናያለን።



ስዕል 6 ሞዴሊንግ በሪሊፍ መልክ ሲሰራ

በዙሪያ ቅርጽ መልኩ የሚሠሩ የኪነ ቅርፅ ስራዎች ከሪሊፍ በተለየ መልኩ ራሣቸውን ችለው መቆም የሚችሉ ሲሆን በየትኛውም አቅጣጫ እየተዘዋወሩ ሊታዩ የሚችሉ ናቸው። በተጨማሪም በዚህ መንገድ የሚሠሩ የሞዴሊንግ ኪነ ቅርጽ ሥራዎች የአንድን ሠው ወይም ነገር ቅርፅ በዙሪያው የሚታወቀውንና ያለውን ተፈጥሮውን ለማየት የሚያስችሉ ናቸው።



ስዕል 7 በዙሪያ ቅርጽ መንገድ ሞዴሊንግ ሲሰራ

መሠረታዊ የሞዴሊንግ ኪነ ቅርፅ መስሪያ መሣሪያዎች የምንላቸው ቅርፅ ማውጫ፣ የተቦካ ጭቃ ናቸው።

ቅርፅ ማውጫ፦ የተለያዩ ነገሮችን ተጠቅመን ለምንሠራው የሞዴሊንግ ቅርፅ ጥበብ የተለያዩ የቅርፅ ማውጫ መሣሪያዎች ያስፈልጉናል። መሣሪያዎቹን በአካባቢ የሚገኙ ቁሣቁሶችን እንጨት፣ ፕላስቲክ፣ አጥንት፣ ብረት ወዘተ... ተጠቅሞ በቀላሉ ሊዘጋጁ የሚችሉ ናቸው። እነዚህ መሳሪያዎች በጭቃ ሞዴል ጥናት ወቅት እንደየ ቅርፆቻቸው ሁኔታ ለልዩ ልዩ ፎርሞች ማውጫነት ያገለግላሉ።



ስዕል 8 የጭቃ ሞዴል

የተቦካ ጭቃ በቀላሉ ከአካባቢያችን ልናገኝ ከምንችለው ንፁህ የአፈር ዓይነት ውሃን ተጠቅመን በማቡካት ማዘጋጀት የምንችል ሲሆን ጭቃውም በጣም ሣይቀጥንና ራሱን ችሎ መቆም በሚችል መልኩ መሆን አለበት።

ተግባር 1፦ ትንንሽ የሰውና የእንስሳት ምስሎችን ጭቃን በመጠቀም መስራት

እይታዊ ጥባበትን ለመስራት መሰረታዊ ቅርጾችንና ፎርሞችን ማወቅና መገንዘብ አስፈላጊ መሆናቸውን ከዚህ በፊት ተምራችኋል። ስለሆነም የሰውና የእንስሳትን ቅርጾች ከመስራታችሁ በፊት መሰረታዊ ፎርሞችን በመደጋገም መለማመድ ይኖርባችኋል።

ለስራው የሚያስፈልጉ ነገሮች፦ በደንብ የቦካ ጭቃ፣ ጠረጴዛ፣ ትንንሽ ከእንጨጥ የተሰሩ የቅርጽ ማውጫ መሳሪያዎችና ሸቦዎች

**አሰራር**

- ☞ በመጀመሪያ የሚሰራውን ሞዴል ማቀድና ከተሰራ በኋላ ምን እንደሚመስል ለመረዳት በወረቀት ላይ መንደፍ
- ☞ የነደፍነውን ስራ በቀጭን ሽቦዎችና ትንንሽ እንጨቶችን በመጠቀም አርማቸር መስራት
- ☞ በመቀጠል በደንብ ከሸክላ አፈር የተዘጋጀ የቦካ ጭቃ ማዘጋጀትና ማቅረብ

**ማሳሰቢያ**፡ ጭቃው በደንብ ለስራው ምቹ መሆኑን የምናረጋግጥበት በእጃችን በምንነካው ጊዜ ከእጃችን መጣበቅ የለበትም። ምክንያቱም ጭቃው በእጃችን በምናድቦለቡልበት ጊዜ ከእጃችን ጋር የሚላከክ ከሆነ የምንፈልገውን ቅርጽ በቀላሉ ማግኘት አያስችለንም።

- ☞ እጃችንን በመጠቀም ጭቃውን በሽቦች ከተሰራው አርሚቸር ላይ ማልበስና የሚፈለገው ስራ አስኪመጣ ድረስ የቅርጽ ማውጫዎቹን በመጠቀም መስራት
- ☞ ቅርጹ ተሰርቶ ካለቀ በኃላ እንዳይሰነጠቅ በፕላስቲክ ሸፍኖ ማስቀመጥ
- ☞ በደንብ ከደረቀ በኃላ በጭራሮ ማቃጠል እንደ አስፋላጊነቱ ቀለም በመቀባት ማስጌጥ





ስዕል 9 ከጭቃ የተሰሩ ሞዴሊንግ ስራዎች

## መልመጃ 13

1. በመጀመሪያ በሸቦችና በትንንሽ እንጨቶች አርማቸር በመስራት የሚያስደስታችሁን የሰዎች ሆነ የእንስሳት ሞዴሊንግ በጭቃ በመስራት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አሳዩ።

## 2.5 ቴያትርን የመስራት ችሎታ

### 2.5.1 የቴያትር ጥበብን ለመስራት መነሻ የሚሆኑ ዋናዋና ነገሮች



ስዕል 10

በዚህ ርዕስ ላይ በሚስደሰታችሁ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጽሁፈ ተውኔት በማዘጋጀትና በመለማመጃ ክፍሎች ልምምድ በማድረግ በቡድን ቴያትርን ትሰራላችሁ። በመሆኑም ለስራችሁ የሚሆኑ ዋና ዋና የቴያትር ነጥቦችን እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. **ስክሪፕት (ጽሁፈ-ተውኔት)**፡- ቴያትር በሚሰራበት ወቅት በመጀመሪያ በቴያትሩ መግለጽና መተላለፍ የሚፈልገውን መልዕክት ቀድሞ በጽሁፍ የሚገለጽበት ድርሰት ነው። ይህ ማለት ግን የቴያትሩ ድርሰት የግድ በጽሁፍ መጻፍ አለበት ማለት አይደለም። ምክንያቱም አጫጭር ቴያትሮች በባህላዊ ዝግጅቶች እና በቀብር ስነስርዓቶች እንዲሁም በመሳሰሉት ያለጽሁፍ ተዘጋጅተው የሚተወኑ እንዳሉ መረዳት ያስፈልጋል።

**2. አልባሳት፡-** አልባሳት የምንለው ተዋንያን በልምምድ ወቅትም ሆነ የቴያትሩ ዝግጅት ተጠናቆ ለታዳሚ በሚቀርብበት ወቅት የገጸ ባህሪውን ትክክለኛ መልክና ሁኔታ በመላበስ ለማሳየት የሚለብሷቸው ጨርቆች ናቸው። ይህም ተዋኒያን የተሰጣቸው ገጸ ባህሪን ይበልጥ እውነተኛ እንዲሆን አድርጎ ለማቅረብ የሚያስችል ነው። ለምሳሌ የሀዘን ገጸ ባህሪን ጥቁር ጨርቅ ለብሶ ሊያሳይ ይችላል።

**3. የቴያትር ቦታ፡-** የቴያትር ጥበብ በተገቢው ዝግጅት የሚቀርብበት ስፍራ ሲሆን የቦታው አመራረጥ እንደ ዝግጅት አይነቱ የተለያየ ቦታ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ በዛፍ ጥላ፣ በእርሻ ቦታዎች እንዲሁም በጣም የተሻሻለ ሲሆን ደግሞ ለቴያትር መስሪያነት ተብለው በተዘጋጁ ቴያትር ቤቶች ሊካሄድ ይችላል።

**4. ቁሳቁሶች፡-** በመድረክ ላይ የምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች በሙሉ የሚጠሩበት ስያሜ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ተዋኒያን በእጅ የሚይዟቸው ትንንሽ እቃዎች (የሻይ ስኒ፣ ደብዳቤዎች፣ መጽፍት ወዘተ...)፣ ግላዊ ቁሳቁሶችን (የእጅ ስዓት፣ የሞባይል ስልክ፣ ጌጣጌጦች ወዘተ...)፣ አልባሳታዊ ቁሳቁሶች( የእጅ ጓንት፣ ከዘራ፣ የእጅ ቦርሳ ወዘተ...) እና የመድረክ ቁሳቁሶች (ጠረጴዛ፣ አበባ፣ የግድግዳ ስዓት፣ የአበባ ማስቀመጫ፣ ወንበር ወዘተ...) በምሳሌነት መጥቀስ እንችላለን።

**5. ልምምድ፡-** የቴያትር ልምምድ በጥበቡ ውስጥ መሰረታዊ ከሚባሉት አንዱ ሲሆን ተዋኒያን ከልምምድ በፊት የወሰዱትን ጽሁፈ ተውኔት ከማንበብ ጀምሮ እስከ ቴያትሩ መክፈቻ ቀን ድረስ የሚኖርበት ሃላፊነት ነው። አንድ ተዋናይ በአንድ ተውኔት ላይ መመዱቡን ካወቀበት ጀምሮ የልምምድ ስራውን መጀመር ይጠበቅበታል። የስራውም መጀመሪያ ጽሁፈ ተውኔቱን ደጋግሞ ማንበብና የተውኔቱን ዋነኛ ጽንሰ ሀሳብ፣ ፍልስፍና፣ መልዕክትና ድባብ መረዳት ይሆናል።

## መልመጃ 14

1. በመምህራችሁ ተዘጋጅቶ በሚቀርብ የተቀረጹ የህጻናት ቴያትር ስራዎች በማየት አሰራሩንና አጠቃላይ ሁኔታውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

## 2.5.2 የቴያትር ፈጠራ ችሎታን ማሳየት

### መልመጃ 15

1. በቡድን በመሆን የአካባቢያችሁን ሁኔታ የሚገልጽ ቴያትር ተገቢውን ዝግጅትና ልምምድ በማድረግ በተሰጣችሁ ጊዜ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ። ዝግጅቱን ከጨረሳችሁ በኃላም የጋራ ግምገማ አድርጉ።

## የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ ሁለት ትምህርት የተጠናቀቀ ሲሆን በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጣችሁን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦላችኃል።

| ተ.ቁ | ነጥቦች | አሳክቻለሁ | አላሳካሁም |
|---|---|---|---|
| 1 | የሙዚቃ ኖታዎችን ለመፃፍና ለማንበብ የሚያስፈልጉ መሰረታውያንን አውቃለሁ። | | |
| 2 | የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ወይም ስታፍ ላይ ኖታዎችና የዕረፍት ምልክቶች አቀማመጣቸውን እንዴት መሆን እንዳለበት አውቃለሁ። | | |
| 3 | መስመሮችን በመጠቀም የሙዚቃ ኖታዎችን መከፋፈል እንደሚቻል አውቃለሁለሁ። | | |
| 4 | ድንገተኛ ምልክቶችና ሙዚቃ ስንጫወት ከግማሽ እስከ ሙሉ ድምፅ መጨመር ወይም መቀነስና ወደ ነበረበት ቦታ እንደሚመልስ አውቃለሁ። | | |
| 5 | የሙዚቃ መክፈቻ ቁልፎች ከስታፍ በስተግራ በመቀመጥ የድምጾችን ባህሪ መወሰናቸውን አውቂያለሁ። | | |
| 6 | ረዳት መስመሮች ከስታፍ በታችና በላይ የሚቀመጡ ድምፆችን ስታፍን ወክለው የሚቀርቡ አጫጭር መስመሮች እንደሆኑ አውቃለሁ። | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7 | የጊዜ አመልካች ምልክቶች ሁለት ቁጥሮች ላይና ታች ሆነው በመቀመጥ በባር ውስጥ ምናስቀምጠውን ምት ብዛትና የኖታውን ዘር ለመለየት እንደሚያስችሉ ተረድቻለሁ። | | |
| 8 | በስታፍ ላይ የተፃፉ ዜማዎችን ለማንበብ ኖታዎች ያረፈበት ቦታ የራሱ መጠሪያ ስምና ድምፅ እንዳለው ተረድቻለሁ። | | |
| 9 | የሞዛይክ መስሪያዎችንና አሰራርን አውቃለሁ። | | |
| 10 | ወረቀትን በመጠቀም ሞዛይክ መስራት እችላለሁ። | | |
| 11 | የሞዴሊንግ ምንነትንና አሰራርን መግለጽ እችላለሁ። | | |
| 12 | ጭቃን በመጠቀም ትንንሽ ኪነ ቅርጾችን መስራት እችላለሁ። | | |
| 13 | ቴያትር የሚቀርብበት ቦታዎችንና መስሪያ ቁሳቁሶችን መግለጽ እችላለሁ። | | |
| 14 | አጫጭር የቴያትር ጽሑፎችን መጻፍ እችላለሁ። | | |
| 15 | ገጸ ባህሪን ተላብሶ መድረክ ላይ መተወን እችላለሁ። | | |

## ማጠቃለያ

☞ የሙዚቃ መፃፊያ ሰሌዳ ከአምስት መስመሮችና ከአራት ክፍት ቦታዎች የሚመሰረት ነው። የሙዚቃ ቁልፎች ከሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ መጀመሪያ ላይ በመቀመጥ የስታፍ ክፍት ቦታዎችንና መስመሮችን ስያሜ እንዲያገኙ በማድረግ ዜማ መፃፍ የሚያስችሉ ሲሆኑ በዋነኛነት ጥቅም ላይ የሚውሉት ጅ እና ኤፍ ቁልፎች ናቸው።

☞ የመክፈያ መስመር እኩል ምት ያላቸውን ኖታዎች በእኩል መንገድ ለመከፋፈል ያገለግላል። እኩል ምት ያላቸው ኖታዎች የሚቀመጡበት በሁለት መክፈያ መስመሮች መካከል የሚገኝ ቦታ ምድብ ወይም

ባር በመባል ይታወቃል። የመዝጊያ መስመሮች ደግሞ ሙዚቃ ተፅፎ ማለቁን የሚያረጋግጡ ሁለት ነጠላ መስመሮችን በአንድ ላይ የምናገኝበት ነው። ረዳት መስመር ከስታፍ በታችና በላይ ያሉ ድምፆችን ለመጻፍ የሚረዱ ስታፍን ወክለው የሚቀርቡ አጫጭር መስመሮች ናቸው።

- የጊዜ አመልካች ምልክቶች ኖታዎችን በባር በባር እኩል ለመከፋፈል የሚያገለግሉ ቁጥሮች ሲሆኑ የላይኛውና ታችኛው ቁጥር የሚባሉ ሲሆን የራሳቸው ትርጉም ያላቸው ናቸው። ከእነዚህ በተጨማሪ ተለዋዋጭ ምልክቶች የሚባሉት ደግሞ የሙዚቃን ሁኔታ የሚለውጡና ለማሳመር አስፈላጊ የሆኑ የትዕዛዝ ምልክቶች ናቸው።

- ድንገተኛ ምልክቶች በስታፍ ላይ የተቀመጠና አጠገባቸው ያለውን ወይም በአንድ ባር ያለን ሌላ ተመሳሳይ ድምጽ ያለውን ኖታ ድምጹን በግማሽ ለመጨመርና ለመቀነስ እንዲሁም ወደነበረበት ቦታ ለመመለስ የሚረዱ የሙዚቃ ምልክቶች ናቸው። በአጠቃላይ በሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳ ላይ የተጻፉ ድምጾችን በሙዚቃ መሳሪያና በድምጻችን ልንጫወታቸው እንችላልን።

- የሞዛይክ ጥበብ ከእይታዊ ጥበብ አቀራረቦች መካከል አንዱ ሲሆን የሰው ልጅ በተለያዩ ጊዜያትና ዘመናት የደረሰበትን የእድገት ሁኔታ፣ የአስተሳሰብ ብቃት፣ የሚኖርበትን አካባቢ፣ የሚያምንበትን ጉዳይ፣ የሚሠማውን ስሜት ሲገልፅበት የቆየ የጥበብ ዘርፍ ነው። የሞዛይክ ስራዎች የተለያዩ ቁሳቁሶችንና መሣሪያዎችን የሚጠይቅ ሲሆን የሥራው ሂደትም ከፍተኛ የሆነ የፈጠራና የትዕግስት እንዲሁም በንቃት መሳተፍን ይጠይቃል።

- የብሎክ ወይም የሪሊፍ ህትመት በተለያዩ ቁሳቁሶችና መሳሪያዎች የሚሰራ ሲሆን ከነዚህም መካከል በድንች፣ በጎማ፣ በእንጨት፣ በድንጋይና የመሳሰሉት ቁሳቁሶች ተጠቃሽ ሲሆኑ የሚታተመውን ክፍል ከሌላው አበጥ እንዲል ና ዞሮ እንዲቀረጽ በማድርግ የሚታተም የህትመት አይነት ነው።

- ቴያትር፡- አልባሳትን በመጠቀም ተዋንያን ገጸባህሪን ተላብሰው በመድረክ ላይ የሚተውኑበት ጥበብ ሲሆን በሀገራችንም እየተለመደና እየተሰራበት የመጣ ጥበብ። በመሆኑም እነዚህን ጥበባት ባህላችሁንና

ታሪካችሁንና የምትገልጹባቸውና ለሌላው ዓለም የምታስተዋውቁባቸው በመሆናቸው ጥበቡንና ጥበበኞችን ማክበርና ማድነቅ እንዲሁም መንከባከብ ይጠበቅባችኃል።

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በመጽሀፉ ውስጥ የቀረበውን ጹሁፍ ሳትመለከቱ ጥያቄዎቹን መልሱ። ጥያቄዎቹን ሠርታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ከመምራችሁ ጋር መልሶቻችሁን አመሳክሩ።

**መመሪያ አንድ፡-** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል "እውነት" ስህተት ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሽ።

---1. የሙዚቃ ድምፆችን መፃፊያ ቦታ ድንገተኛ ምልክት በመባል ይታወቃል።

---2. ረዳት በስመሮች ከስታፍ በታችና በላይ የሚገኙ ኖታዎችን ለማስቀመጥ የሚረዱ አጫጭር መስመሮች ናቸው።

---3. ከሁለቱ የጊዜ አመልካች ቁጥሮች ውስጥ የታችኛው ቁጥር የኖታውን ዝርያ ያሳያል።

---4. ጂ ቁልፍ ከመካከለኛ እስከ መጨረሻ ወፍራም ያሉ ድምፆችን ይይዛል።

---5. ከስታፍ ከሶስተኛው መስመር በላይ የሚቀመጡ ዘንግ ያላቸው ኖታዎች ዘንጋቸው ወደ ላይ ይወጣል።

---6. የሞይሊን ቅርጻ ቅርጽ የሚሰራው በጭቃ ብቻ ነው።

---7. ከብሎክ /ሪሊፍ/ ህትመት ይልቅ የቀጥታ ህትመት ከፍተኛ ጥንቃቄና ትዕግሰት ይጠይቃል።

---8. የድንች ህትመት ከብሎክ /ሪሊፍ/ የህትመት አሰራር ዘዴ ውስጥ ይመደባል።

---9. ሞዛይክን ከምንሰራባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ወረቀት ነው።

**መመሪያ ሁለት፡- ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ።**

1. እንዲታተም የምንፈልገውን ምስል በወረቀት ላይ በመሳልና ቀርጸ በማውጣት የሚከናወን ህትመት

   ሀ. ቀጥታ ህትመት ሐ. የስቴንስል ህትመት

   ለ. የብሎክ ህትመት መ. ሁሉም

2. ገጸ ባህሪን ተላብሰው በመድረክ ላይ የሚተውኑ ሰዎች

   ሀ. ተዋንያን ሐ. ታዳሚያን

   ለ. ዳይሬክተር መ. ሁሉም

3. ለሞዛይክ መስሪያነት የሚያገለግለው የቱ ነው?

   ሀ. ዶቃዎች ሐ. ወረቀቶች

   ለ. የመስታውት ስብርባሪዎች መ. ሁሉም

4. ከሚከተሉት ኖታዎች ውስጥ አነስተኛ ምት ያለው ኖታ የቱ ነው?

   ሀ. ሙሉ ኖታ ሐ. ሩብ ኖታ

   ለ. ግማሽ ኖታ መ. አንድ ስምንተኛ ኖታ

5. ሁለት ምት በአንድ ባር ውስጥ በሚቀመጥበት ጊዜ የሚቀመጥ የጊዜ አመልካች ቁጥር ትክክለኛው ነው?

   ሀ. $\frac{3}{4}$ ለ. $\frac{2}{4}$ ሐ. $\frac{4}{4}$ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

6. ከሚከተሉት ውስጥ ሙዚቃን በሙዚቃ መጻፊያ ላይ ፅፎ ለማንበብ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ውስጥ ይመደባል።

   ሀ. የሙዚቃ መክፈቻ ቁልፍ ሐ. ኖታ

   ለ. የጊዜ አመልካች ቁጥሮች መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

7. የሙዚቃ መጻፊያ ሰሌዳን ወክለው ከስታፍ ከታችና ከላይ የሚቀመጡ አጫጭር መስመሮች ምን ተብለው ይጠራሉ።

   ሀ. መርጃ መሳሪያ ሐ. ረዳት መስመሮች

   ለ. መክፈቻ ቁልፎች መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

8. ከመካከለኛ እስከ መጨረሻ ቀጭን ያሉ ድምፆችን የሚይዝ የሙዚቃ መክፈቻ ቁልፍ የቱ ነው።

ሀ. ጂ ቁልፍ ለ. ኤፍ ቁልፍ ሐ. ስታፍ መ. ሁሉም

**መመሪያ ሦስት፡** ከዚህ በታች በ (ሀ) ረድፍ የተቀመጡ ጥያቄዎችን ካነበባችሁ በኃላ በ (ለ) ረድፍ ከተቀመጡ አማራጮች ጋር አዛምዱ።

| (ሀ) | (ለ) |
|---|---|
| ----1. ከነበረው ድምፅ በግማሽ ድምፅ ይጨምራል | ሀ. ♮ |
| ----2. ከነበረው ድምፅ በግማሽ ድምፅ ይቀንሳል | ለ. 𝄫 |
| ----3. ከነበረው ድምፅ በሙሉ ድምፅ ይቀንሳል | ሐ. # |
| ----4. ከነበረው ድምፅ በሙሉ ደምፅ ይጨምራል | መ. X |
| ----5. ጨምሮ ወይም ቀንሶ የነበረውን ድምፅ ወደ መጀመሪያ ድምፅ ይመልሳል | ሠ. ♭ |

**መመሪያ አራት፡-** የሚከተለትን ጥያቄዎች አጭር መልስ በመስጠት መልሱ።

1. በሙዚቃ ትምህርት ውስጥ የመስመር አይነቶችን በመዘርዘር አገልግሎታቸውን ግለፁ።
2. ድንገተኛ ምልክቶችን ትርጉምና ጠቀሜታ ግለፁ።-
3. የጊዜ አመልካች ቁጥሮች በሙዚቃ ውስጥ ያላቸውን አስተቃፅኦ ተናገሩ።-
4. የጂ ቁልፍና የኤፍ ቁልፍ አንድነትና ልዩነትን አብራሩ።
5. ስታፍ ላይ የተቀመጠ ዜማ ስታነቡ የሚሰማችሁን ስሜት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።
6. ለብሎክ ህትመት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን ዘርዝሩ።.
7. መሰረታዊ የህትመት ጥበብ ዓይነቶች በመጥቀስ ምንነታቸውን ግለጹ።
8. የኪነ-ቅርጽ አሰራር ዘዴዎችን ጻፉ።
9. ለቴያትር መስሪያነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ጥቀሱ።

# ምዕራፍ 3 ታሪክና ባህል

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡

### ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን ባህላዊ ሙዚቃዎችና ጭፈራዎችን ትዘረዝራላችሁ።
- ባህላዊ ሙዚቃዎችና ጭፈራዎችን በተግባር ሰርታሁ ታሳያላችሁ።
- ባህላዊ ሙዚቃዎችና ጭፈራዎችን ስትጫወቱ የተሰማችሁን ስሜት ታካፍላላችሁ።
- የዋሻ ውስጥ እይታዊ ጥበብ ታሪክንና አጀማመርን ትረዳላችሁ።
- በተለያዩ ዋሻ ውስጥ የተሰሩ የቀለም ቅብና የድንጋይ ላይ ቅርጾችን ትለያላችሁ።
- በቅደመ ታሪክ ወቅት የተሰሩ የእይታዊ-ጥበብ ስራዎችን ታደንቃላችሁ።
- በማህበረሰቡ የሚሰሩ ባህላዊ የእጅ ስራዎች አሰራርና አገልግልታቸውን ትረዳላችሁ።
- የሀገራችሁን ባህላዊ ትውፊቶች ታውቃላችሁ።

## የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

3.1 ማህበረሰቡ የሚጠቀማቸው የባህላዊ ውዝዋዜ አይነቶች
3.2 የዋሻ ውስጥ ስዕሎች
3.3 የኢትዮጲያ ባህላዊ ጥበባት ታሪኮች

# 3.1 የባህላዊ ሙዚቃና ውዝዋዜ አይነቶች

## 3.1.1 ባህል እና የባህላዊ ሙዚቃ

### መልመጃ 1

1. ባህል ምንድን ነው? ምን አይነት ባህላዊ ውዝዋዜዎችን አይታችሁ ታውቃላችሁ? የምታውቋቸውን በመዘርዘር አንድነትና ልዩነታቸውን እንዲሁም የሚያስተላልፏቸውን መልዕክት ከጓደኞቸሳችሁ ጋር ተወያዩባቸው።

ባህል ማህበረሰቡ የዕለት ከዕለት ተግባሩን ለማከናወን በሚያደርገው እንቀስቃሴ ውስጥ የሚገኙ እንደ ቋንቋ፣ ሐይማኖት፣ ኪነ-ጥበብ፣ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ ታሪክ፣ ስነ-ስርዓት ወ.ዘ.ተ ማህበረሰባዊ መገለጫ ናቸው። በአጠቃላይ ባህል የሰውን ልጅ መንፈሳዊና ቁሳዊ ውጤቶችን አጠቃሎ የያዘ ሲሆን ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ ነው።

ሁሉም ማህበረሰብ የራሱን ሙዚቃን ፈጥሮ ይገለገላል። የሙዚቃው ተግባር ማዝናናት፣ ማስተማር፣ ቡድኑን ስርዓት ማስያዝ፣ ለአምላክ ምስጋና ማቅረቢያ ወዘተ ሊሆን ይችላል። ተግባሩ ምንም ይሁን ምን የሰው ልጅ ከሙዚቃ ውጪ አለመሆኑን ጥጠቁማል።

በመሆኑም ባህላዊ ሙዚቃ አንዱ የማህበረሰብ ተግባር ሆኖ ሰዎች ደስታቸውን፣ ሀዘናቸውንና ሌሎች ፍላጎቱን ለማስተላለፍ የሚጠቀምበትና ከማህበረሰቡ ጋር አብሮ የሚኖር ጥበብ ነው።

### የባህላዊ ሙዚቃ ጠቀሜታ

### መልመጃ 2

1. የምትኖሩበት አካባቢ ማህበረሰብ ባህላዊ ሙዚቃን ለምን ለምን ተግባራት ሲጠቀምበት አስተውላችኋል? ያስተዋላችኋቸውን የባህላዊ ሙዚቃ ጠቀሜታ በመዘርዘር የተወሰኑትን በተግባር ሰርታችሁ አቅርቡ።

ባህላዊ ሙዚቃ የአንድ አካባቢ ባህላዊ ክንውኖችን በቀላል መንገድ ለመግለፅና ለማስተዋወቅ የሚያስችል የባህል አንዱ ክፍል ነው። ማህበረሰቡ አመለካከቱን፣

ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ ምኞቱን፣ ፍቅሩን፣ ጥላቻውን፣ መውደዱን፣ ጀግንነቱን ወ.ዘ.ተ የሚገልጽበትና የማህበራዊ ተግባቦ መፍጠሪያ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

ባህላዊ ሙዚቃ እውቀትን፣ ችሎታን፣ ልምድን፣ አስተሳሰብን፣ ሀይማኖታዊ ስርዓትን፣ ስነ ምግባርን፣ ባህላዊ እሴቶችንና ሌሎች ባህላዊ ስርዓቶችን ማስተላለፍ የሚያስችል ነው። እንዲሁም ሀገራዊ ስሜትን በማህበረሰቡ ዘንድ በመፍጠር የሀገርን ዳር ድንበር ማስከበር የሚያስችል ስነ ልቦናዊ ዝግጅት እንዲኖር የማድረግና ጀግንነትን በማበረታታት የሀገር ፍቅርን ማስረጽ የሚያስችል ነው።

### 3.1.2 ባህላዊ ውዝዋዜዎች (ጭፈራዎች)

**መልመጃ 3**

1. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸው የውዝዋዜ (ጭፈራ) አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ በመዘርዘር ለክፍል ጓደኞቻችሁ ካነበባችሁ በኋላ የሚከወኑበትን ወቅትና ልዩነታቸውን አብራሩ።

ጭፈራ ባህላዊ ሙዚቃን ለማድመቅ ባህላዊ አልባሳትን በመልበስ በከፊልና ሁሉንም የሰውነት ክፍል በማንቀሳቀስ ደስታን ለመግለፅ የሚደረግ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን በርካታ ብሄር ብሄረሰቦች ያሏት ሀገር በመሆኗ የብዙ ባህላዊ ጭፈራ አይነቶች ያላት ሀገር ናት። ከነዚህ በርካታ የባህል ጭፈራዎች ውስጥ በአማራ ክልል ውስጥ የሚገኙትን እንደሚከተለው እንመልከት።

በአማራ ክልል ውስጥ የሚገኙ ባህላዊ ጭፈራዎች የጎጃም፣ የወሎ፣ የጎንደር፣ የሸዋ ወዘተ ያጠቃልላል። በተጨማሪም የአዊ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደርና የዋግህምራ እንዲሁም የአርጎባ ብሔር ብሔረሰቦችንም አካቶ የያዘ ክልል ነው።

የጎጃም አጨፋፈር ስልት ነጠላ እንቅጥቅጥና ዝናብ እንቅጥቅጥ በመባል ይታወቃሉ። ነጠላ እንቅጥቅጥ የሚባለው የእጅና የእግር እንቅስቃሴ ሲሆን ዝናብ እንቅጥቅጥ መላ ሰውነትን በማንቀጥቀጥ የሚሰራ የአጨዋወት ስልት ነው።



ስዕል 1 የጎጃም ባህላዊ ጭፈራን የሚያሳይ

ይህንን በምስሉ ላይ የምትመለከቱትን አለባበስ በማየት በአካባቢያችሁ ከሚገኙ የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ ቡድኖች ጋር ጉብኝት በማድረግ የወንዶችን አለባበስ ሁኔታ እንደሚመስል ከቻላችሁ ፎቶ ግራፎችን በማንሳት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡና በውስጡ የሚተላለፉ መልዕክቶች ላይ በመነሳት ስለ ጎጃም ባህላዊ ጭፈራ ጥልቅ ሃሳብ አዳብሩ።

በወሎ ማህበረሰብ የተለያዩ አጨፋፈር ስልቶች ይገኛሉ። ታዋቂ የሆኑ አጨፋፈር ስልቶች መካከል ትምትም፣ መጋሎና ላሌጐማ የሚባሉት ይጠቀሳሉ። አብዛኞቹ የወሎ አጨፋፈር ስልቶች የአንገት፣ የትከሻና የእግር እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ለምሳሌ በራያ አካባቢ ወንዶችንና ሴቶችን የሚያሣትፍ ጭፈራ ያለ ሲሆን ወንዶች ብቻቸውን ክብ በመስራት ቀጫጭን ሸመሎችን በመያዝ ወደ ላይ እየዘለሉ ተመልሰው መሬት ላይ ቁጭ ብድግ እያሉ የሚጨፍሩት ጭፈራም አለ።



ስዕል 2 የወሎን ባህላዊ ጭፈራ የሚያሳይ

በአካባቢያችሁ ከሚገኝ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ወይም ወደ ባህል ሙዚቃ ቡድኖች ሄዳችሁ ልምድ በመውሰድ የወሎ ባህላዊ ጭፈራ ከሚባሉት አንዱን በመምረጥ የአጨፋፈሩን ስልት በትክክል ተገንዝባችሁ ልምምድ በማድረግና የአለባበስ ስርዓቱን አሟልታችሁ ለክፍል ተማሪዎችና ለመምህራችሁ ሰርታችሁ አቅርቡ።

የጐንደር አጨፋፈር ስልት ደግሞ ድስቅና፣ መንጥቅ በመባል የሚታወቅ ሲሆን የአንገትና የትክሻ እንቅስቃሴ ያለው ወንዶችና ሴቶችን በጋራ የሚያሣትፍ ነው። እንዲሁም ክብ በመስራት በአውራጅ በተቀባይ እየታጀበ የሚከናን የአጨፋፈር አይነት ነው።



ስዕል 3 የጎንደር ባህላዊ ጭፈራን የሚያሳይ

በምስሉ ላይ ከምትመለከቱት ውጭ በጎንደር ባህላዊ ጭፈራ ወቅት ወንዶችም ሆነ ሴቶች የሚጠቀሙባቸው የአለባበስ አይነቶችን ተመልክታችሁ የምታውቁ ከሆነ በማስታወስ (ምልከታው በአካል / በቴሌቪዥን) በክፍል ውስጥ በመወያት ከቻላችሁም በተግባር ሰርታችሁ ለማሳየት ሞክሩ።



ስዕል 4 የሸዋ ባህላዊ ጭፈራን የሚያሳይ

የሸዋ አጨፋፈር ስልት የዋንጫ ልቅለቃ በመባል የሚታወቅ ሲሆን በአንገትና በትክሻ እግርን በማፈራረቅ መንሽ ወይም ላዳ፣ ባርኔጣ፣ ካባ በመልበስ የተለያዩ የእርሻ መሳሪያዎችን በመያዝ ጭምር ይጫወታሉ። የምንጃር ከበድ ያለ እንቅስቃሴ ያለው ስልትም በዚሁ አካባቢ ይገኛል።

የአዊ አጨፋፈር ስልት ከወገብ በታች የአካል እንቅስቀሴ መሰረት ያደረገ ነው። ወንዶች ጥሩምባ በመንፋት ሴቶች የቅርቀሀ ጥላ ይዘው በማሸከርከር በጋራ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።





ስዕል 5 የአዊ ባህላዊ አጨፋፈርን የሚያሳይ



ስዕል 6 የሰቆጣ ሴቶች ባህላዊ ጭፈራን የሚያሳይ ፎቶ

ዋግህምራ (ሰቆጣ)፡- ዋግህምራ አካባቢ የሚጨፈረው የጭፈራ ስልት የራሱ የሆነ መገለጫ ያለው ሲሆን የአንገት የትከሻና የወገብ እንቅስቃሴ ላይ የሚያተኩር ነው። በተጨማሪም ከፍተኛ ሀይል የሚጠይቅና የአካል ተለ ከሚታወቁበት ሙዚቃ መካከል "አሀይ ላሎ ላሎ፣ ኡይ ላሎይ ላሎይ፣ ላሎዮ ላሎዮ.. አንዱ ነው " ሌላው የሻደይ አከባበር ሲሆን የዋግህምራ ሴቶች ከሀምሌ 16-26 ሻደይ አበባ እያሉ የሚጫወቱትና የሚዝናኑበት ጨዋታ ነው።

## 3.2 የዋሻ ውስጥ ጥበብ

### 3.2.1 የዋሻ ውስጥ ጥበብ ታሪክ አጀማመር

ስነ-ጥበብ የሰው ልጅ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነበር። በዋናነት የመፍጠር ፍላጎትና ተፈጥሮ ስነ-ጥበብን ለመሥራት ወሳኝ ምክንያት ሆኖ ቆይቷል። ጊዜውም የሰው ልጅ ታሪኩን በፅሁፍ ማስፈር ከመጀመሩ በፊት፣ መጠለያውን

ዋሻ ምግቡን ደግሞ በአደንና በፍራፍሬ ለቀማ አድረጎ ሲኖር በነበረበት ወቅት ነው። በዚህ ርዕስ የሥነ-ጥበብን አመጣጥና ቀደምት ታሪክ አጠር ባለ መልኩ የምናይ ይሆናል። በአውሮፓ የተገኙ ፈረንሳይ ውስጥ የሚገኘው የላስክአክስ ዋሻ እና ሰፔን ላይ የሚገኘው የአልታሜራ የዋሻ ውስጥ ስዕሎች ከ40 ሽህ አመታት በፊት አካባቢ የተሰሩ መሆናቸው ይገመታል። በጥንት ጊዜ በዋሻ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች የተለያዩ አራዊቶችን ምስል በዋሻቸው ግድግዳዎች ላይ ያሰፍሯቸው ነበር። በዋሻ ግድግዳዎች ላይ የተሰሩት ስዕሎች በትክክል ለምን ጉዳይ እንደተሰሩ በውል የማይታወቅ ቢሆንም አንዳንድ ምሁራን ስዕሎቹ የተሰሩት እርስ በእርስ ለመግባባት፣ ለአምልኮታዊ ሂደትና ለተለያዩ የጋራ ዝግጅቶች መሆኑን ይናገራሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከዕለት ተዕለት ኑሯቸው ጋር በተያያዘ ለመቁረጫ፣ ለማረጃና ለመሳሰሉት ተግባራቶች የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን ከእንጨት፣ ከድንጋይና ከአጥንት ያዘጋጁ ነበር።

በኢትዮጲያ ደግሞ የዋሻ ውስጥ ስነ-ጥበብ የተከናወነባቸው ቦታዎች በዋናነት ድሬድዋ ላይ የሚገኙት የፓርክ ኤርክና የለጋ ኦዳ ዋሻወች ናቸው።

### 3.2.2 የዋሻ ውስጥ ስዕሎች

የሰው ልጅ በዋሻ ውስጥ ይኖር በነበረበት ጊዜ በዋሻዎቹ ጣራና ግድግዳዎች ላይ የሰራቸው ስዕሎች በተጨባጭ ሊያሳዩን የሚችሉት ዋሻዎች አውሮፓ የሚገኙት የላስክ አክስና አልቴሚራ፣ ኢትዮጲያ ውስጥ የሚገኙት ፓርክኤርክ እና ለጋ ኦዳ ናቸው።

#### 1. የላስክ አክስ ዋሻ

በቅደመ ታሪክ ስነ-ጥበብ የዋሻ ውስጥ ከሚገኝባቸው ስፍራዎች ውስጥ አንዱ ሲሆን መገኛውም በደቡብ ምዕራብ ፈረንሳይ ውስጥ ነው።

በዚህ ዋሻ ጣራና ግድግዳ ላይ ቁጥራቸው 600 አካባቢ የሚደርሱ የቀለም ቅብ ስራዎችና በድንጋይ ላይ የተቀረጹ ምስሎች ያሉ ሲሆን በአብዛኛውም የእንስሳት ምስሎች ናቸው። ከእነዚህ እንስሳትም አብዛኛዎቹ የፈረስ ምስል ሲሆን ሌሎች እንስሳት እንደ አጋዘን፣ የዱር ፍየል፣ የጎሽ የመሳሰሉት እንስሳትም ይገኛሉ። ይህ አስደናቂ ዋሻም በአለም አቀፍ የትምህርት፣ ሳይንስና ባህል ተቋም በቅርስነት ተመዝግቧል።




ስዕል 7 በላስክ አክስ የሚገኙ ስነ-ጥበባዊ ስራዎች

## 2. የአልታሚራ ዋሻ

ቀደምት የሆኑ የቀለም ቅብና የድንጋይ ላይ ሪሊፍ ቅርጾች የሚገኙበት ስፍራ ሲሆን የሚገኘውም በሰሜን ስፔን ውስጥ ነው። በዚህ ዋሻ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ አይነት ስነ-ጥበባዊ ስራዎች ያሉ ሲሆን እነዚህም ቀለም ቅብች፣ በከሰል የተሰሩ ንድፎች እና ግድግዳ ላይ የተሰሩ ሪሊፍ ቅርጾች ናቸው። በዋሻ ውስጥ የሚገኙት በአብዛሀኛው የእንስሳት ምስሎች ሲሆኑ ከነዚህም መካከል ከርከሮ፣ አጋዘንና ፈረስ ተጠቃሽ ናቸው። ይህ ዋሻ በአለም አቀፍ ቅርስነት ተመዝግቧል።





ስዕል 8 በአልታሚራ ዋሻ ውስጥ የሚገኙ ምስሎች

## 3. ፓርክ ኤጂክ ዋሻ

በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጲያ በድሬደዋ አካባቢ የሚገኝ ዋሻ ሲሆን በዚሁ ዋሻ ጣራና ግድግዳ ላይ ቁጥራቸው 60 የሚደርሱ የሰውና የእንስሳት ምስሎች ይገኛሉ። ቀለም ቅቦችን ይሰሩባቸው የነበሩ ቀለም ያላቸው ድንጋዮች የተገኘ ሲሆን በተጨማሪም ለተለያየ አገልግሎት ይጠቀሙባቸው የነበሩ የድንጋይ መሳሪያዎች፣ የእንስሳት አጥንቶች ተገኝተውበታል።




ስዕል 9 በፓርክኤርክ ዋሻ ውስጥ የሚገኙ ምስሎች


## 4. የለጋ አዳ ቅድመ ታሪክ የዋሻ ላይ ስዕሎች

የለጋ አዳ ዋሻ ከድሬደዋ ደቡብ ምዕራባዊ አቅጣጫ ከሚገኙ ዋሻዎች መካከል አንዱ ሲሆን በዚህ ዋሻ ውስጥ በላይኛውና በታችኛው የዋሻው ንጣፎች ላይም ከ600 በላይ በቅብ ስዕሎች ያጌጡ ምልክቶችና ጽሑፎች ሰፍረው ይገኛሉ። የዋሻው ግድግዳ ተጨማሪ ሌሎች ስዕሎች እንዳሉት የሰነድ መረጃዎች ያሳያሉ።

በመጥፋት ላይ ከሚገኙ ብርቅዬ ታሪካዊ ሀብቶችም አንዱ እንደሆነ የሚነገርለት የለጋ አዳ ዋሻ ጥንታዊ ጥበቦች የሰው ልጅ ከረጅም ጊዜ በፊት ለተግባቦት አገልግሎት ይጠቀምባቸው የነበሩ ምልክቶች የእድገት ደረጃ በማሳየት ለዘርፉ ተመራማሪዎች ፍንጭ የሚሰጥ ነው። የሚስተዋሉት የእንስሳት ሥዕሎችም ምናልባትም በዚያን ዘመን ይኖሩ የነበሩትን የእንስሳት ዓይነቶች የሚያመላክት ይሆናል ተብሎ ይገመታል። ከዚህ ጎን ለጎንም የሥዕሎቹ ጥበቦቹ በዚያን ዘመን ይኖሩ የነበሩትን ሕዝቦች የአስተሳሰብ የእድገት አድማስ የሚያመላክቱ ናቸው። አብዛኛውን የሥዕል ጥበቦቻቸውን አሸቆጥቁጠው የቀቡትም በቀይና በጥቁር ቀለም ነበር።

በዋሻው ከተሳሉት ስዕሎች መካከል ዝሆን፣ ፈረስ ላይ የተቀመጠ ሰው፣ ምግብ እየተጎራረሱ የሚመገቡ ሰዎች፣ ጊንጥ፣ የእጅ መሣሪያዎች እና ሌሎች ይገኙበታል። እነዚህ ጥበቦችም የሰው ልጅ በዚያን ዘመን ሲገለገልባቸው የነበሩ የእጅ መሣሪያዎችንና በአካባቢው የነበሩ እንስሳትና የሰዎች የሕይወት ዘይቤም ምን እንደነበር ጭምር ፍንጭ የሚሰጡ ናቸው።





ስዕል 10 በለጋ አዳ ዋሻ ውስጥ የሚገኝ ምስሎች

**መልመጃ 4**

1. የሰው ልጅ እንዴት ስነ-ጥበብን እንደጀመረና ለምን ዓላማ ሲጠቀምባቸው እንደነበር በጹሁፍ አዘጋጅታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

## 3.3 የኢትዮጲያ ባህላዊ ጥበባት ታሪክ

### 3.3.1 የባህል ጥበብ (በእይታዊ-ጥበቡና እጅ ስራዎች አንጻር)

ኢትዮጵያ የብዝሃ ባህል ያላቸው ህዝቦች ሀገር እንደመሆኗ የነዚህ ቱባ ባህሎች መግለጫ የሆኑ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሀብቶች ባለቤት ናት። ከነዚህ መከከል ብንጠቅስ እንኳን መጽሀፈ ስዕላት፣ ሳንቲሞች፣ መስቀሎች፣ የስፌት ስራዎች፣ የሸክላ ስራዎችን ማንሳት እንችላለን። እነዚህ ጥንታዊ የማህበረሰቡ የጥበብ ስራዎች ለተጠቃሚው ማህበረሰብ የእለት ተእለት ተግባራትን ከመከወኛነት ባሻገር በአንድ ዘመን የነበረና ያለ የጎብረተሰብ ክፍል የአኗኗር ዘይቤ፣ ወግ፣ ልማድ፣ ፍልስፍና፣ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃና ባህልን ለተተኪው ትውልድ በማስተዋወቅ በኩሌ አስተዋፅኦ አላቸው። በመሆኑም እነዚህን ውድ የባህል ማንነቶቻችንና መገለጫዎች በአግባቡ በመንከባከብና ጠብቆ በማቆየት ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ አደራ ለእያንዳንዳችን የተሰጠ ሃላፊነት ነው።

በስነ -ጥበቡ ረገድ ኢትዮያ ከአሏት ተነግረው ከማያልቁ ውድ ሀብቶቿ መካከል መጸሀፈ ስዕላት አንዱ ነው። መፅሐፈ ሥዕላት የጥንታዊት ኢትዮጵያን የስዕል አሳሳል፣ የስዕል ቅብ፣ የስዕል አልባሳት፣ የስዕል አቀማመጥ የሚያስተምር ጥንታዊ መፅሐፋችን ነው። ይህ መፅሐፍ የተደረሰው በአፄ ልብነ ድንግል

ዘመነ መንግስት ሲሆን የኢትዮጵያ የስዕል ጥበብ ፍልስፍናን ጠቅልሎ የያዘ መፅሀፋችን ነው። ይህ መፅሀፍ በዘመናችን የኢትዮጵያ የስዕል አሳሳል ጥበብን ለአለም ለማስተዋወቅ ለሚጥሩ ባለሙያዎች ትልቅ ግብአት እየሆነ ያለ ውድ ሀብታችን ነው። በዚህ መጸሃፍ መሰረትም ቤተ-ክርስቲያናት ውስጥ፣ በገዳማት ግድግዳዎች፣ በሀይማኖታዊ ድርሳናት እንዲሁም በእንጨቶች ላይ የተለያዩ ሃማኖታዊ ስዕሎች ይሳሉ የነበረ ሲሆን ለአብነትም የሚከተሉትን ስዕሎች እንመለከታለን።





ስዕል11

እነዚህ ሀይማኖታዊ የቀለም ቅብ ስዕል አድኖ ጎንደር የሚገኘው የደብረብርሀን ስላሴ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ናቸው።

የአሳሳል ሁኔታቸው ደግሞ ስናይ በመጀመሪያ ቀለማቶቹን እንመልከት።

ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስነ ስዕል ልዩ መልኮች አንደኛው አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ቀለማት ግልጋሎት ላይ መዋላቸው ነው። ከጥቁርና ነጭ ቀለማት በተጨማሪ ሰማያዊ፣ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት ብቻ ለስዕል ስራ ይውላሉ። እነዚህ ቀለማትም እንደቅዱስና መለኮታዊ ቀለማት ይቆጠራሉ። እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ቀይ፣ ቢጫና አረንጓዴ ቀለማት በየአካባቢው ከሚገኙ ዕጽዋቶች ተጨምቀው ይሰሩ የነበረ ሲሆን ሰማያዊ ደግሞ ከውጭ አገራት እንዲመጣ ይደረግ ነበር።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ስዕሎቹ ጥልቀት አልባነት እና የጀርባ ከባቢ አለመኖራቸው ነው።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስነ ስዕል ውስጥ ጥልቀት፣ ርቀትና ቅርበት እንዲሁም የጀርባ ከባቢን የሚያሳይ ገጽታ ማየት ያልተለመደ ሲሆን ስዕሎቹም ባለ ሁለት አውታር ብቻ ናቸው።

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የስዕሎቹ የፊት አቀማመጥ እንመልከት። የቤተ ክርስቲያን ምስሎች ባለሶስት አውታር ካለመሆናቸውም በላይ እንቅስቃሴ አይኖራቸውም። ብዙ ጊዜ ሰዎች፣ ቅዱሳን እና የመሳሰሉት ሲሳሉ እንቅስቃሴ አልባ ሆነው ነው። አልፎ አልፎ ብቻ ፊረስ ጋላቢ ቅዱሳን በተወሰነ ድርጊት ውስጥ ሆነው ይታያሉ። የሰው ልጅ ፊት ሶስት ዓይነት ብቻ አቀማመጦች ይኖሩታል። ይሄውም ቅዱሳን እና ፃድቃን ሙሉ በሙሉ ፊት ለፊት ሆነው ወይንም ሁለት ሶስተኛው ፊታቸው እየታየ ይሳላሉ።

ይህ የሚሆንበት ምክንያት ምስሉ በተመልካቹ ላይ ኃይሉን እንዲፈነጥቅ ከማሰብም በመነሳት ነው። ኃጥኣን እና እርኩሳን ደግሞ ፊታቸው የጎንዮሽ ወይም አንድ አይናቸው ብቻ እንዲታይ ይደረጋል። በሀይማኖታዊ ስፍራዎች የሚሳሉ ስዕሎች ላይ የሰዓሊያን ስም ሰፍሮ የሚገኝባቸው አጋጣሚዎች አሉ። ይሁንና ኃይማኖታዊ ስዕሎችን መስራት እንደኃይማኖታዊ ተግባር ስለሚቆጠር የሰዓሊያን ስም እምብዛም አይገኝም። ብዙ ጊዜም ሰዓሊያን የአብያተ ክርስትያናትን ግድግዳዎች በኃይማኖታዊ ስዕሎች እንዲያስውቡ ስራ ሲሰጣቸው ተግባራቸውን ከመጀመራቸው አስቀድሞ በሱባዔ ፈጣሪቸውን ለምነው ነው።

ሌላው ከሀይማኖታዊ ስዕሎች ወጣ ስንል ቁሳዊ የባህል ሀብቶቻችን እናገኛለን። ቁሳዊ የባህል ሀብቶች ሰዎች በአኗኗር ስልታቸው ውስጥ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውን እንዲረዱ በማሰብ በአካባቢያቸው ወይም ከሚኖሩበት ስፍራ የሚያገኟቸውን ቁሶች በግብዓትነት ተጠቅመው እንደየ እውቀታቸው፣ ማንነታቸው፣ ፍልስፍናቸው እና እምነታቸው እንዲሁም የኑሯቸውን ሁኔታ እንዲያንፀባርቁ አድርገው የሚሰሯቸውን ቁሶች ናቸው። ከእነዚህም ቁሳዊ ባህል ውስጥ እንዱና ዋነኛው ሀገረሰባዊ የእጅ ስራ ነው።

ሀገረሰባዊ እጅ ስራ አብዛኛውን ጊዜ በእጅ እና ባህላዊ በሆኑ መሳሪያዎች የሚሰሩ ቁሶች ናቸው። እነዚህም በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች በሚኖሩ ማህበረሰቦች የሚሰሯቸው ሲሆን ለአብነት የሽመና ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ የስፌት ስራ፣ የብረት ስራ፣ የቀርከሃ ስራ፣ የእንጨት ስራ፣ ባህላዊ አልባሳት፣ የቆዳ ስራ ተጠቃሽ ናቸው።

## መልመጃ 5

1. የምታውቋቸውን የስፌት ውጤቶች በመዘርዘር የሚሰሩበትን ቁሳቁሶችን አሰራራቸውን ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

የስፌት ስራዎች በአንድ ጎብረተሰብ አካባቢ በሚገኙ ተፈጥሯዊ በሆኑ የሳር ዓይነቶች የሚሰሩ ሲሆን የአንድን ጎብረተሰብ ማንነት፣ እምነት፣ ልማድ፣ ባህል እና ወግ የሚያሳዩ ናቸው። እነዚህ ስራዎችን የሚሰሩ ጥበበኞች የተለያዩ ቁሳቁሶችን የሚጠቀሙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥም ወስፌ፣ ግራምጣ፣ አለላ፣ ቆዳ ተጠቃሽ ናቸው።

በሀገራችንም ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውሉ የስፌት ስራዎች ያሉ ሲሆን በዋናነት የሚከተሉት ናቸው። መሶብ፣ አገልግል፣ ቁና (ወራንታ)፣ ወንፊት፣ ሰበጥራ፣ ሰፌድ፣ ሙዳይ፣ የጀበና ማስቀመጫ (ማቶት)፣ ሌማትና የመሳሰሉት ናቸው።

## መልመጃ 6

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ የስፌት ስራዎችን በመዘርዘር ማህበረሰቡ ለምን አገልግሎት እንደሚጠቀምባቸው ወላጆቻችሁንና ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ ዝርዝር ጽሁፍ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አቅረቡ።





ስዕል 12 በማህበረሰቡ የሚሰሩ የተለያዩ የስፌት ውጤቶች

ሌላው ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ከቆዳ የሚሰሩት ባህላዊ ቁሶች ናቸው። ከተለያዩ የእንስሳት ቆዳ የሚሠሩት እንደ መቀመጫ፣ አገልግል፣ ጋሻ እና ከበሮ ያሉ ባህላዊ መገልገያዎች የበርካቶችን ቀልብ የሚስቡ የጥበበ ስራዎች ናቸው።





ስዕል 13 በማህበረሰቡ የሚሰሩ የቆዳ ውጤቶች

## መልመጃ 7

1. በአካባቢያችሁ የእጅ ስራዎች የሚሰሩባቸው ስፍራዎች በመሄድ አጠቃላይ የሚሰሯቸውን ስራዎች፣ አሰራር፣ የሚሰጡትን ጠቀሜታ ከተመለከታችሁትና ከጥበበኞቹ አንደበት በመስማት የተረዳችሁትን በጹሁፍ በማዘጋጀት ለመምህራችሁ ሪፖርት አቅርቡ።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪም ባህላዊ አለባበስም ውድ ሀብቶቻችን ውስጥ የምናገኘው ሲሆን ጥንት ኢትዮጲውያን በራሳቸው ጥሬ ሀብትና በራሳቸው ዜጎች ጥበብ የተሰሩ የጥጥና የቆዳ አልባሳትን ይጠቀሙ ነበር። ማንታቸውን የሚያሳዩ የራሳቸው ብቻ የሆነ የተለያዩ የአለባበስ ወጎችም ነበሯቸው። ተራው ህዝብ ከፍየል፣ ከበግና ከከብት የተሰሩ የቆዳ ልብስ ሲለብስ ነገስታቱና የጦር ባለሟሎች እንደየማዕረጋቸው ከአንበሳና ከነብር ቆዳዎች የተሰሩ በወርቅና አልማዝ ያጌጡ ልብሶችን መልበስ ያዘወትሩ ነበር።

በኋላ ግን በባህላዊ መንገድ ከጥጥ የተሰሩ ልዩ ልዩ መልክና ጥራት ያላቸው የልብስ አይነቶች የቆዳ ልብሶችን እየተኩ መጡ። የቆዳ ልብሶችም የተወሰነ ጌጣ ጌጥ እየተጨመረላቸው የሰርክ መሆናቸው ቀርቶ የጌጥ፣ የማዕረግ ወደ መሆን ተሸጋገሩ። የነብርና የቆዳ አልባሳት ግን እስከ ቅርብ ድረስ የጀግና መለያ አርማ በመሆን አገልግለዋል።

ኢትዮጲውያን ከዚህ ውጭ ለሰርግ፣ ለስራ፣ ለለቅሶ ወዘተ እያሉ የሚለብሷቸው የተለያዩ የልብስ አይነቶች እና ጌጣጌጦችም ነበሯቸው። ከጌጣጌጦች ውስጥ ማርዳና ድሪ ተጠቃሽ ናቸው።

- **ማርዳ፦** ከወርቅ፣ ከብር ሞለል ወይም ጠፍጠፍ ተደርጎ በአንጥረኛ እጅ የሚሰራ ፣ ከዶቃ ጋር ተሰክቶ በልጆች አንገት የሚታሰር የህፃናት ጌጥ ነው።
- **ድሪ፦** አንጥረኛ ብሩን እያቀለጠ እንደ ሰንሰለት እያደረገ የሚሰራው፣ በጣም የቀጠነ የብር ሰንሰለት፣ ከማተብ ጋር እየተጠመጠመ ሴቶች በአንገታቸው የሚያደርጉት የብር፣ የወርቅ ድሪ።



ስዕል 14 የባህላዊ አልባሳት ጌጦች



ስዕል 15 የኢትዮጵያ ባህላዊ መዋቢያ ጌጣጌጦች

### መልመጃ 8

የሚከተለውን ሰንጠረጅ በማንበብ የጎደለውን ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ሙሉ።

| የኢትዮጵያ ባህላዊ የልብስ አይነቶች | የኢትዮጵያ ባህላዊ ጌጣጌጦች |
|---|---|
| ኩታ | ወለባ |
| ነጠላ | አንባር |
| ጋቢ | ማርዳ |
| ጥልፍ ቀሚስ | ጉትቻ |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## 3.3.2 የባህል ጥበብ ታሪክ (ከሙዚቃ አንጻር)

### መልመጃ 9


1. እናንተ በምትገኙበት አካባቢ የበዓላት ዘፈኖችን እንዴት እንደሚጠቀሙትና ከሌላው አካባቢ ጋር ልዩነቱንና አንድነቱን መምህራችሁ የሚያሳዩዋችሁን ቪዲዮ በመመልከት አስታየት ስጡ።

በሀገራችን ኢትዮጵያ በስፋት የሚዘወተሩ በሁሉም አካባቢዎች ጥቅም ላይ የሚውሉ ባህላዊ ሙዚቃና ጭፈራዎች ይገኛሉ። በተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች

በዓላትን በሚያከብሩበት ወቅት ባህላዊ ሙዚቃዎችን በመከወን በዓሉን ያደምቃሉ። ማህበረሰቡ ከሚጠቀምባቸው የበዓላት ዘፈኖች ውስጥ የሚከተሉትን መመልከት ይቻላል።

ሀ. **የዘመን መለወጫ በዓል**፦ ሴቶች አዲስ አመት መምጣቱን ለማብሰር እንቁጣጣሽ እያሉ አበባ በመያዝ አዲሱ ዓመት የሰላምና የፍቅር እንዲሆን መልካም ምኞት የሚያበስሩበት ነው።

ለ. **የመስቀል በዓል**፦ የመስቀል በዓል በመላው ኢትዮጵያ ክፍል መስከረም 17 ቀን የሚከበር በዓል ሲሁን በጉራጌ ማህበረሰብ እንደ ዘመን መለወጫ በዓል ይቆጠራል። በአማራ ክልል የሚገኘውት የአዊ ማህበረሰቦች ደግሞ ጀኖ በመልበስ እርጥብ ዛፍ በመላጥ ወደ ዘመዶቻቸው ቤት እንደ ስጦታ ይዞ በመሄድ አብዚ የሚባል ባህላዊ ምግብ በመመገብ እዮሄ እያሉ በመዝፈን በዓሉ ይከበራል።



ስዕል 16 የመስቀል በዓል አከባበር

ሐ. **የገና በዓል**፦ የእየሱስ ክርስቶስን መወለድ ምክንያት በማድረግ የሚከበር ሀይማኖታዊ በዓል ሲሆን ወጣት ወንዶች ቆልማማ የገና እንጨትና ሩር በመያዝ ግጥሚያ አካሂደው ሲጨርሱ እየዘፈኑ (እየጨፈሩ) የሚያከብሩት በዓል ነው።



ስዕል 17 ልጆች በጎና በዓል ላይ ሲጫዎቱ

መ. **የኢድ አልፈጥር በዓል**፡- በእስልምና እምነት ሙስሊም ማህበረሰቦች ያላቸው ለሌላቸው በማካፈል (ዘካተል ፈጠር) ስጦታ በማበርከት የሚያከብሩት በዓል ነው። በዚህ ወቅት መንዙማ በቀስታ እንደ እንጉርጉሮ በመመሰጥ ድቤ በመያዝ አላህን በማመስገን የሚቀርብ ዜማ ነው።

ሠ. **የፋሲካ በዓል**፡- በኦርዶክስ እምነት የክርስቶስን ሞቶ መነሳት ምክንያት በማድረግ የሚከበር በዓል ነው። በዚህ በዓል በዓሉ ከመከበሩ አንድ ቀን ቀድሞ የስቅለት ቀን ህፃናት በእሳት የተለበለበ ወይም የተዝጎረጎረ የሙሻሙሼ እንጨት በመያዝ ሙሻሙሼ እያሉ በሰዎች ቤት በመዘዋወር ዳቦ፣ ዱቄት፣ ሽሮ፣ በርበሬ እየለመኑ ይዘምራሉ።

ረ. **የአረፋ በዓል**፡- በስልምና ሀይማኖት የሚከበር በብዛት በነሺዳ መልክ የተለያዩ ሀይማኖታዊ ዜማዎችን በማቅረብ የሚከበር በዓል ነው። ነሺዳ ድቤ በመያዝ በብዛት ልጆች የሚጠቀሙባቸው ዜማዎች ናቸው። መልዕክቱም አላህን ለማመስገንና የእንኳን አደረሳችሁ ምኞት ለማስተላለፍ ይጠቀሙበታል።



ስዕል 18 የአረፋ በዓል አከባበር

መ. **የቡሄ በዓል፡-** ነሀሴ 13 ደብረ ታቦር ቀንን ለማክበር ቡሄ በሉ እያሉ ህፃናትና ወጣት ወንዶች የሚያከብሩት በዓል ነው።

## የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ ሦስት ትምህርት የተጠናቀቀ ሲሆን በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጣችሁን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦላችኃል።

| ተ.ቁ | ነጥቦች | እችላለሁ | አልችልም |
|---|---|---|---|
| 1 | ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸው ባህላዊ መዚቃዎችና ጭፈራ (ውዝዋዜ) በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ በፊትም የነበሩና የሚቀጥሉ ባህላዊ ትውፊቶች እንደሆኑ አውቃለሁ። | | |
| 2 | ሰዎች የራሳቸው ባህልና የኑሮ ዘየ እንዳላቸውና ከሌሎች ጋር ሊመሳሰልም ሆነ ሊለያይ እንደሚችል ተረድቻለሁ። | | |
| 3 | የባህላዊ መዚቃ ፅንሰ ሀሳብ ማህበረሰቡን የሚወክሉ ነገሮችን የሚያንፀባርቅ በባህላዊ ቅኝት የሚገነባ መዚቃ መሆኑን ተረድቻለሁ። | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4 | በባህላዊ ሙዚቃ ጠቀሜታ ውስጥ ሙዚቃ ራሱ የባህል አንዱ ክፍል ቢሆንም ባህልን ለማስተዋወቅና በኑሮ ውስጥ ማህበራዊ መስተጋብር እንደሚፈጥር ተረድቻለሁ። | | |
| 5 | ባህላዊ ጭፈራ (ውዝዋዜ) ባህላዊ ሙዚቃ ሲቀርብ ሙዚቃውን ለማድመቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ እንደሆነ ተረድቻለሁ። | | |
| 6 | በዋሽ ውስጥ የተሰሩ የእንስሳት ምስሎች ና ሌሎች ስነ-ጥበባዊ ውጤቶችን መግለጽ እችላለሁ። | | |
| 7 | የኢትዮጲያ ባህላዊ የአሳሳል ጥበብ ታሪክን ማብራራት እችላለሁ። | | |
| 8 | የጥንታዊ አልባሳትንና ጌጣጌጦችን መዘርዘርና አሰራራቸውን መግለጽ እችላለሁ። | | |
| 9 | የስፌት ስራዎችን መጥቀስና አሰራራቸውን ማብራራት እችላለሁ። | | |
| 10 | በሙዚቃ የጀግንነት፣ የተፈራረቁ የሀገር ገሾዎችና የሌሎችንም ታሪክ መንገር እንደሚቻል ተረድቻለሁ። | | |

## ማጠቃለያ

- ባህል የማንነት መገለጫ ነው። ማንነት ደግሞ በእምነት፣ በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በሙዚቃ፣ በልማድ፣ በኪነ ጥበብ ወ.ዘ.ተ ይገለፃል። ባህል ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ የሚተላለፍ የማህበረሰብ ሀብት ነው።
- ባህላዊ ሙዚቃ የባህል አንዱ ክፍል ሆኖ ባህልን በቀላል መንገድ ለማስተዋወቅ የሚረዳ ትልቅ መሳሪያ ነው። ባህላዊ ሙዚቃ በባህላዊ ቅኝት የሚሰራና ከአካባቢ አካባቢ የሚወራረስ ሀብት ነው።
- ባህላዊ ጭፈራ ባህላዊ ሙዚቃን ለማድመቅ የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው። በሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ብሄረሰቦች መኖራቸው ብዙ ባህላዊ

ሙዚቃና ጭፈራ እንዲኖረን አድርጓል። በአጠቃላይ ማህበረሰቡ የራሱን ስሜትና ባህልን የሚያንፀባርቅበት ባህላዊ ሙዚቃና ጭፈራ አለው። ታሪክ በተለያየ መንገድ ይገለፃል። በዚህ ምዕራፍ ስር ያየነው በሙዚቃ የተለያዩ ባህላዊ ክንውኖችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ ይቻላል።

- ☞ የሰው ልጅ እንደዛሬው ዘምኖ በህንፃ መኖር ከመጀመሩ በፊት በዋሻ ውስጥ በሚኖርባቸው በነዚያ የጋርዮሽ ጊዜያት ነበር የመጀመሪያዎቹን ጥበበኞች የስዕል ጥበብ የጠራቻቸው። ያ ዘመን የሰው ልጅ በአደንና ፍራፍሬ ለቀማ ራሱን ያስተዳድር የነበረበት በመሆኑ እነዚህ የስዕል ጠቢባንም ስለ ዱር አራዊቱ አይነትና ባህሪ፣ ስለአደን ጥበቦችና ስለአዳኞችና ታዳኞች ድራማ ብሎም ስለወቅቱ የሰው ልጅ አለባበስና አኗኗር በሸራ ሳይሆን በየዋሻዎቹ ግርግዳና በየ ድንጋዩ ላይ የየአካባቢያቸውን ግብአት በመጠቀም ይስሉ ነበር። እነዚህ የስዕል አይነቶች ዛሬም ድረስ በደቡብ ፈረንሳይና በምስራቅ ስፔን በጥሩ ሁኔታ ተጠብቀው ይገኛሉ።

- ☞ ሀገረሰባዊ እጅ ስራ ሰዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ ቁሶችን በግብዓትነት ተጠቅመው የራሳቸውን ዕውቀት በመጨመር የጎብረተሰብ ባህል፣ እምነት፣ ወግ፣ አመለካከት ወዘተ እንዲያንፀባርቁ አድርገው የሚሰሯቸውን ቁሶች ናቸው። ለምሳሌ ባህላዊ ስዕሎች፣ አልባሳትና ጌጣጌጦች፣ የስፌት ስራዎች፣ የሽክላ ስራዎች ወዘተ...

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

በምዕራፍ ሦስት የቀረበውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በመጽሀፉ ውስጥ የቀረበውን ጽሁፍ ሳትመለከቱ ጥያቄዎቹን መልሱ። ጥያቄዎቹን ሠርታችሁ ከጨረሳችሁ በኋላ ከመምራችሁ ጋር መልሶቻችሁን አመሳክሩ።

**መመሪያ አንድ፦** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል "እውነት" ስህተት ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሽ።

---1. በባህል ሰዎች አለባበሳቸውን ብቻ ያስተዋውቃሉ።

---2. የጥንት ሰዎች ድንጋይን ከድንጋይ እያጋጩ የሙዚቃ ድምጽ ያወጡ ነበር።

---3. ሙዚቃ ከሰው ልጆች ህይወት ጋር ተሳስሮ የሚሄድ ጥበብ ነው።

---4. በዋሻ ውስጥ የጥበብ ታሪክ የተሳሉት ስዕሎች በአብዛሀኛውን የእንስሳት ምስሎች ናቸው።

---5. የዋሻ ውስጥ ስዕሎች የጥበብ ታሪክን ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች ፋይዳቸው የላቀ ነው።

---6. በኢትዮጵያ ባህላዊ ጥበባት ታሪክ የነብርና የአንበሳ ቆዳዎችን የሚለብሱት ተራው ህዝብ ነበር።

---7. ለባህላዊ ሀገረሰባዊ እጅ ስራዎች ማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ትኩረት ከፍተኛ ነው።

**መመሪያ ሁለት፡-** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ።

1. በለጋ አዳ የቅደመ ታሪክ የዋሻ ውስጥ የሚገኘው የትኛው ነው

   ሀ. የገዘሀን ምስል

   ለ. ፈረስ ላይ የተቀመጠ ሰው

   ሐ. ምግብ እየተነራረሱ የሚመገቡ ሰዎች

   መ. ሁሉም

2. አንጥረኛ ብሩን እያቀለጠ እንደ ሰንሰለት እያደረገ የሚሰራው በጣም የቀጠነ የብር ሰንሰለት ከማተብ ጋር እየተጠመጠመ ሴቶች በአንገታቸው የሚያደርጉት

   ሀ. ድሪ ለ. ማርዳ ሐ. አንባር መ. ሁሉም

3. በኢትዮጲያ የዋሻ ውስጥ ስነ-ጥበብ ታሪክ የምትታወቀው

   ሀ. አክሱም ሐ. ድሬደዋ

   ለ. ላሊበላ መ. እንጦጦ

4. የጥንታዊ አሳሳልን ባህሪያትን የማይገልጸው

   ሀ. ስዕሎቹ የሚሳሉት በውስን ቀለማት መሆኑ

   ለ. ስዕሎቹ ጥልቀት ያላቸው መሆናቸው

   ሐ. የፊት አቀማመጥ የሚሳሉትና ቅዱሳንና እርኩሳንን የሚገልጹ መሆናቸው

   መ. ሁሉም

**መመሪያ ሶስት፦** የሚከተለትን ጥያቄዎች አጭር መልስ በመስጠት መልሱ።

1. ለዋሻ ውስጥ ስነ-ጥበብ ታሪክ አጀማመር የጥናት ቦታ የሆኑት ስፍራዎች ጻፉ። ----------
---
---.
2. የጥንታዊ ስዕሎችን መገለጫዎችን ጻፉ። ----------
---
---
-------.
3. የኢትዮጵያን ታሪክ የሚገልጹ ባህላዊ አልባሳትንና ጌጣጌጦችን ጻፉ።
---
---.

**መመሪያ አራት፦** የተግባር ስራ።

1. በአካባቢያቸው የሚገኙ ባህላዊ ሙዚቃዎችን ሰብስባችሁ በመምጣት የሰበሰባችሁትን ሙዚቃዎች በተግባር ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

# ምዕራፍ 4 ጥበብን ማስተዋወቅ

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡

### ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- በጥበብ ውስጥ አንድነትን የሚገልፁ ሀሳቦችን ትረዳላችሁ።
- ጥበብን በመጠቀም የልዩነት ሀሳቦች እንዴት እንደሚቀርቡ ታውቃላችሁ።
- ሰዎች ጥበብን ተጠቅመው አንድነትና ልዩነቶችን መግለፅ እንዴት እንደሚችሉ ትረዳላችሁ።
- አንድነትና ልዩነት ያላቸው ሀሳቦችን በጥበብ እንዴት ማነፃፀር እንደምትችሉ ትገልጻላችሁ።
- ጥበብን በመጠቀም ስምምነትንና ልዩነት ያላቸውን ሀሳቦች ታቀርባላችሁ።
- ጥበብን በመጠቀም ስሜታችሁን በተግባር ትገልፃላችሁ።
- የተለያዩ ብሄረሰቦችን የባህል ልዩነትን በክውን ጥበባት ትገልጻላችሁ።
- የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ጽንሰ ሀሳብን ትረዳላችሁ።
- የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡትን ፋይዳ ትገልጻላችሁ።
- ማህበረሰቡ የሚሰራቸውን የእጅ ስራ ውጤቶችንና የሚሰራባቸውን ቁሳቁሶች ታውቃላችሁ።
- በአካባቢያቹህ የሚገኙ ጥበበኞችን ታከብራላቹህ ስራዎቻቸውንም ታደንቃላችሁ።
- የተለያዩ የእጅ ስራዎችን ለመስራት ተነሳሽነት ታሳያላችሁ።

## መግቢያ

ሥነ ጥበባት የተለያዩ ዘውጎች ያሏቸው ሲሆኑ ጥበብ የጠራቻቸው ሰዎች እንደየ መክሊታቸው በህይወት መንገዳቸው የታዘቡትንና የተመለከቱትን ለሌሎች ለማጋራት በተለያየ አቀራረብ ማለትም በስዕል፣ በግጥም፣ በድራማ፣ በቴያትር፣ በሙዚቃ፣ በዳንስ፣ በተውኔት፣ በፊልምና በሌሎች መንገዶች መልእክቶችን ተደራሽ ያደርጉባቸዋል።

አገራችን ባለብዙ ጠቃሚ እሴቶች ባለቤት በመሆኗ ህዝቦቿም ያሏቸውን እሴቶች ተጠቅመው በእለታዊ ኑሯቸው የሚገጥሟቸውን ግጭቶች ሲፈቱባቸው፣ ያጠፉትን ሲያርሙባቸው፣ የጎበጠውን ሲያቀኑበት፣ ሰነፍን ሲያተጉበት፣ ጎበዝን ሲያበረታቱበት፣ አንድነትን ሲሰብኩበት፣ ፍቅርን ሲዘሩበት ወዘተ የቆየ ነው።

### የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

4.1 የተለያዩ ጥበባትን በመጠቀም ስለ ልዩነትና ተመሳሳይ ሀሳቦች መወያየት

4.2 የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ

## 4.1 በስነ ጥበባት ሃሳብ መናገር

### 4.1.1 ልዩነትና ተመሳሳይ ሀሳቦችን በጥበባት መግለጽ

ስነ-ጥበባት ከጥንት ጀምሮ ማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤውን፣ አለባበሱን፣ አመጋገቡን፣ ማህበራዊ መስተጋብሩንና በአጠቃላይ በህይወት ዘመኑ የሚያጋጥሙትን ውጣ ውረዶች ለማንጸባረቅና እርስ በርእስ ለመለዋወጥ እንደ ከፍተኛ የህይዎት መርህ አድርጎ ሲጠቀምበት ኖሯል። ይህ ማለት ግን ማህበረሰቡ አሁንም ከበርካታ ዘመናት በፊት ሲጠቀምበት ከነበረው አጠቃላይ የአጠቃቀም ስልት ተላቋል ማለት አይቻልም። ስለሆነም ስነ ጥበባት እንደየ ዘመኑ፣ የማህበረሰቡ ንቃተ ህሊና፣ እንደ ህዝበ መንግስት አስተዳደሩ ወዘተ የሚለዋወጥ እደሆነ መመልከት ይቻላል።

እንደማሳያ ብንወስድ ማህበረሰቡ መንግስት ግብር በሚጨምርበት ወቅት በሙዚቃ ውስጣዊ ስሜቱን በመግለጽ የማስተካካያ አቤቱታውን ስልታዊ በሆነ መንገድ ሲያቀርብ፣ ሲከፋው ሲያንጎራጉር፣ በደስታው ሲጨፍርና ሀገር

በተወረረችበት ወቅት ደግሞ በፉከራና በቀረርቶ በማነሳሳት ሀገረን ከጠላት ለመጠበቅ ሲጠቀምበት ነበር።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በርካታ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባት ሀገር ናት። እነዚህ ብሄረሰቦች እያንዳንዳቸው የተለያየ ባህል አላቸው። ይህ የባህል መለያየት አንድነቱን በኢትዮጵያዊነት ልዩነቱን ደግሞ በባህል ውስጥ እንድናይ አግዞናል።

የሀሳብ ልዩነት ማለት ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ሀሳቦች መግለፅ ማለት ነው። የሀሳብ አንድነት የምንለው ደግሞ የተለያዩ ሰዎች በአንድ በተወሰነ ሀሳብ ዙሪያ ስምምነት ሲፈጥሩ ነው።

ጥበብን በመጠቀም ተመሳሳይና ተቃራኒ የሆነ ሀሳብን በተለያየ ሁኔታና ስልት ማንፀባረቅ ይቻላል። የሀሳብ ልዩነትንና አንድነትን በተለመደ ንግግር ከማቅረብ ጥበብን በመጠቀም እንደ ግጥም፣ ሙዚቃ፣ ተረት ተረት፣ ስዕል፣ እንቆቅልሽ፣ ምሳሌያዊ ንግግር ቀልድ ወ.ዘ.ተ ሀሳብን አሳምሮና አዋዝቶ መግለፅ የበለጠ መልእክቱ በአማረና በተዋበ መንገድ እንዲቀርብ ያደርጋል።

ሙዚቃ በርካታ ሃሳቦችን በአንድ በማጠቃለል በማይከብድና በማይሰለች መንገድ ለማስተላለፍ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ይህ ማለት ግን ሌሎች እይታዊና ክውናዊ ጥበባት ድርሻ የላቸውም ማለት አይደለም። በዚህ ክፍል ሙዚቃን በመጠቀም የሃሳብ ተመሳስሎትን ወይም ስምምነትንና ተቃርኖን እንዴት መግለጽ እንደ ሚቻል እንመለከታለን።

### 4.1.2 በፉከራ፣ በሽለላ /ቀረርቶ/ና ዘፈን የሀሳብ አንድነትና ልዩነትን መግለጽ

ፉከራና፣ ሽለላና ዘፈን የሙዚቃ ክፍሎች ሲሆኑ አንድነት ወይም ልዩነት ያላቸው ሀሳቦችን ለማንፀባረቅ ከፍተኛ የሆነ ጠቀሜታ አሏቸው።

ፉከራ ሰዎች ጀግንነትን ለመግለፅ የጦር መሳሪያ፣ ዱላ፣ የእርሻ መሳሪያዎች፣ ሰንደቅላማ ወዘተ በመያዝ ከወዲያ ወዲህ አካኪ ዘራፍ ዘራፍ እያሉ እየተዘዋወሩ የሚፎክሩት ነው።

ሽለላ (ቀረርቶ) ደግሞ ከፉከራ ጋር አብሮ የሚሄድ ፎካሪዎች ሲፎክሩ ሽላዮች ኧረ ጎራው ኧረ ጀግናው ኧረ ጎራው እያሉ የሚፎክሩትን ሰዎች አለንላችሁ ብቻችሁን አይደላችሁም ለማለት የምንጠቀመው የሽለላ አይነት ነው።

ከዚህም የተነሳ ሽለላ ወይም ቀራርቶ፣ ፉከራ ወይም ድንፋታ በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ ይዘው ይገኛሉ። እነዚህም ግጥሞች ደፋርነትን፣ ቆራጥነትን፣ ልበ ሙሉነትንና ጀግንነትን በኢትዮጵያውያን ልብ ውስጥ የሚቀርፁ ናቸው። ቀረርቶ የሚሰማ፣ ድንፋታ የሚያይ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ልበ ሙሉ ይሆናል፤ ባላጋራውንም ከፊቱ ያየ ይመስል ጸጉሩ ይቆማል ደሙ ይፈላል። በተለይ የሚፎክረው ሰው ሲቅበጠበጥ ቁጭ ብድግ ሲል ለተመልካች የራበው አንበሳን ይመስላል። እልሁ ያነቀው ጀግና ጠላቱን ያገኘ ያህል አይኑን አፍጥጦ ወዲያና ወዲህ ሲንጎራደድ ካራስ ነበር የበለጠ ያስፈራል።

ፉከራ ለጀግኖች ሃይልን ይሰጣል፣ ለፈሪዎች ህሊናን እንዲገዙ ያደርጋል። በተለይም በፉከራው ውስጥ የሚገኙት ቃላት በጣም ወኔ የሚቀሰቅሱ በመሆናቸው ለፈሪ እንኳን ድፍረትን ይሰጣሉ፤ ወጣቶችም ይህንን ባዩና በሰሙ ጊዜ አባቶቻቸውን ለመሆን እንዲሁም ለመብለጥ ይጥራሉ።

ዘፈን፡- ከባህላዊ የሙዚቃ ክፍሎች የሚመደብ ሲሆን ዜማና ግጥሙ የማህበረሰቡ የሆነና ሰዎች እንዲሚቻቸው የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ስሜቶቻቸውንና ፍላጎታቸውን የሚገልጹበት ስልት ነው።

## ሀ. ሀገርን በአንድነት ለመጠበቅ የሚቀርብ ፉከራ፣ ሽለላና ዘፈን

### መልመጃ 1

1. በአካባቢያችሁ ባህል ሀገርን በአንድነት ለመጠበቅ ማህበረሰቡ የሚጠቀምባቸውን ፉከራና ሽለላ እንዲሁም ዘፈን በክፍል ውስጥ አስመስላችሁ ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።



ኧረ ጎራው ኧረ ወንዱ ኧረ ጎራው ጎራው፣
ሂዋንና ሀዋ አደምና አዳም፣
ያቆዩዋትን ሀገር በፍቅር በመገን፣
እኛም እንጠብቃት በሰላም በመፈቃቀር፣
ታዲ ምን ያደርጋል ይህ ሁሉ መቃቃር፣
እንሁን ባንድነት እንሁን በፍቅር፣
ወደ ፊት እንጓዝ ወደ ኋላ እንዳንቀር።

ስዕል 1 ፉከራን የሚያሳይ

## ለ. ርስበርስ መካባበርን የሚገለጽ ፉከራና ቀረርቶ

### መልመጃ 2

1. በአካባቢያችሁ ማህበረሰቡ የሚጠቀማቸው እርስ በእርስ መከባበርን የሚያንፀባርቁ ፉከራና ቀረርቶ እንዲሁም ዘፈን በተግባር በክፍል ውስጥ ሰርታችሁ አሳዩ።

## ሐ. መታገስን ለማሳየት የሚቀርብ ፉከራና ቀረርቶ

### መልመጃ 3

1. እናንተ በምትኖሩበት አካባቢ ሰዎች ሲጋጩ ታግሰው ነገሮችን እንዲያልፉ የሚጠቀሙትን ፉከራና ቀረርቶ እንዲሁም ዘፈኖችን በተግባር ከውኑ።

### 4.1.3 በቴያትር ጥበብ የሀሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን መወያየት

**መልመጃ 4**

1. በቡድን በመደራጀት ሀገራዊ ፍቅር የሚፈጥሩና የሀሳብ ልዩነቶችን የሚያከብሩ ማህበረሰብን ለመፍጠር የሚረዱ ሀሳቦች ያሉት የቴያትር ጽሁፎችን በማዘጋጀት ቴያትር በተግባር በክፍል ውስጥ ሰርታችሁ አሳዩ።የተሻለውን በመመረጥም ለትምህርት ቤቱ ማህበረሰቦች አቅርቡ።

## 4.2 የምስል ጥበባት እና የእጅ ስራዎች ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ

### 4.2.1 የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ምንነት

የምስል ጥበባት ከሚለው ቃል ፍች ሥንነሳ መሣል፣ ማስመሰል፣ መንደፍ፣ መፍጠር፣ መቅረፅ የሚል ትርጉም ያለው ሲሆን ንድፍ፣ ኪነ ህትመት፣ ኪነ-ቅርፅ፣ ኪነ-ቅብ፣ ፎቶ ግራፍ፣ ኮላዥ ወዘተ የሚባሉ ስነ-ጥበባዊ ዘርፎችንም በውስጡ የያዘ ነው።

የምስል ጥበባት ከሰው ልጆች የአስተሳሰብ ዕድገት ጋር ተያይዘው የመጡና በየጊዜው ከነበረው የሥልጣኔ ደረጃ ጋር እያደጉ የመጡ ፈጠራዊ የሙያ ዘርፎች ሲሆን ከጥንት ጀምሮ በየደረጃው የሰው ልጆች ግላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ የሆኑ ጉዳዮቻቸውን እየገለጹበት የሚገኙ ጥበባት ናቸው። በተጨማሪም በየዘመኑ የኖሩ የጥበቡ ባለሞያዎች የውስጥ ስሜቶቻቸውን ማለትም ደስታቸውን፣ ብሶታቸውን፣ አካባቢያቸውን፣ ወዘተ የሚገልፁበት ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ ነው።

የእጅ ስራ ጥበብ የተለያዩ የመገልገያና የማስዋቢያ ቁሳቁሶችን የሚያጠቃልል ሰፋ ያለ ዘርፍ ሲሆን እነዚህም ውጤቶች በጎጆ ኢንዱስትሪ ደረጃ ሙሉ በሙሉ በሰው እጅ ወይም ቀለል ያሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የሚሠራ የጥበብ ውጤት ነው። በአብዛኛው የእጅ ስራ ወጤቶች ባህላዊ በሆነ መንገድ የሚሠሩ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ የተለያዩ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ቁሳቁሶችን በመጠቀም በተወሰነ ቁጥር የሚሠሩ ቁሳቁሶችን ያጠቃልላል። ከእነዚህም ውስጥ ለምሳሌ

ለመጥቀስ ያክል የሸክላ ውጤቶች፣ የስፌት ስራዎች የሽመና ውጤቶች፣ የወርቅና የብር ጌጣጌጥ ስራዎች፣ አልባሳት፣ ከብረታ ብረት የሚሠሩ ባህላዊ የመገልገያ ቁሳቁሶች፣ ከቀርቀሃና ከእንጨት የሚሠሩ ማስዋቢያና የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶች የቆዳ ውጤቶች (ቀበቶ፣ ቦርሳ፣ ጫማ) ወዘተ. ይገኙበታል።





ስዕል 2 በማህበረሰቡ ውስጥ በሚኖሩ የጥበብ ሰዎች የተሰሩ የእጅ ስራዎች

### 4.2.2 የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ

የምስል ጥበባትና የእጅ ሰራዎች የህዝቦችን ቀደምት ታሪክ ማንነትና አብሮነት በመስበክ የአንድን ሀገር ህዝቦችን የጋራ የሆነ ስነ-ልቦና እንዲኖራቸው የማድረግ አቅም ያላቸው ሲሆን የጥበብ ሰዎች የሚደነቁት ተፈጥሮ ባደለቻቸው የጥበብ ስራዎች ብቻ ሳይሆን በጥበብ ስራዎቻቸው ውስጥ ለማህበረሰቡ በሚያሥተላለፉት እውነተኛ መልዕክት ጭምር ነው። እነዚህ ጥበቦች ማህበረሰቡ በሚኖርበት አካባቢ የራሱን ባህል፣ ቅርስ፣ አመጋገብ፣ አለባበስ፣ አኗኗርና ልማዱን ጠብቆ ለማቆየትና ከትውልድ ትውልድ ለማስተላለፊያነት ይጠቀምባቸዋል። በሌላ መልኩ ደግሞ ማህበረሰቡን በጦርነት ወቅት በማነሳሳት አሸናፊ ለማድረግ፣ ከችግር ለማውጣት፣ ለማስተማሪያነት እንዲሁም ደግሞ ደስታውንም ሆነ ሀዘኑን እንዲገልጽ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ አሏቸው።

በተጨማሪም በማህበረሰቡ ውስጥ ለሚኖሩ ታዳጊ ሕጻናትም በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ ያላቸውን ልምድ የሚያንጸባርቁበት፣ ከአካባቢያቸው ጋር ያላቸውን መልካም ግንኙነት የሚገነቡበት፣ ከጓደኞቻቸው ጋር ግንኙነታቸውን የሚያጠናክሩበትና ልምዶችን የሚያገኙበትም ነው። በሌላ መልኩ ስነ ጥበብ

በየትኛውም ሁኔታ ግጭትን በማብረድ ወደ ጎብረት ና አንድነት ለማድረስ፣ ለማነቃቃት፣ በግጭት አልባ መንገድ የሀሳብ ተቃርኖን ለመግለጽ ዓይነተኛ መሣሪያ ነው።

ጠቅለል ባለ መልኩ እነዚህ ጥበቦች ለማህበረሰቡ ማህበራዊ፣ ባህላዊ ናኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ያሏቸው ሲሆን ለምሳሌ

**ማህበራዊ ጠቀሜታ**፡- የምስልና የእጅ ስራ ውጤቶች በቤት ውስጥ የተለያዩ ጠቀሜታዎች አሏቸው። ለምግብ ማቅረቢያነት፣ ለምግብ ማስቀመጫነት፣ ለቤት ማስጌጫነት ና ለተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ጠቀሜታ አሏቸው። ከዚህ በተጨማሪም ባለሙያዎቹ የእርስ በርስ ግንኙነታቸውን ለማጠናከርና ከሰዎች ጋር በቀላሉ ግልፅነት በተሞላበትና ደስ በሚል መንፈስና አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ እንዲግባቡ ያስችላቸዋል።

**ባህላዊ ጠቀሜታ**፡- እነዚህ ጥበቦች ካሏቸው ጠቀሜታ መካከል ባህላዊ ጠቀሜታ ነው። ተጠቃሚው ጎብረተሰብ የእለት ተእለት ተግባራትን ከመከወኛነት ባሻገር የአኗኗር ዘይቤውን፣ ወግ፣ ልማዱን፣ ማንነት፣ ባህሉን በማስተዋወቅ በኩል አስተዋፅዎ ያደርጋሉ።

**ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ**፡- የጥበቡ ባለሙያዎች ቁሶችን በተለያየ መጠንና ቅርፅ በመስራት ለተጠቃሚው የጎብረተሰብ ክፍል ያቀርባሉ። ባለሙያዎቹ የሰሩትን ቁሶች በመሸጥ የራሳቸውንና የቤተሰቦቻቸውን ህይወት ለመምራት የሚያግዝ ገንዘብ ያገኙበታል።

### መልመጃ 5

1. በቡድን በመሆን በአካባቢያቹህ የሚገኙ የስዕልና የእጅ ስራዎችን የሚሰሩ ሰወችን ተዘዋውራችሁ በመጠየቅ የሚያገኙትን ማህበራዊ፣ ባህላዊና ኢኮኖሚዊ ጠቀሜታ እንዲሁም በሚሰሩበት ወቅት የሚያጋጡሟቸው ተግዳሮቶችን በመጠየቅ ለመመህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ በጹሁፍ አቅርባችሁ ተወያዩ።

# የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ አራት ትምህርት የተጠናቀቀ ሲሆን በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጣችሁን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦላችኃል።

| ተ.ቁ | ነጥቦች | አሳክቻለሁ | አላሳካሁም |
|---|---|---|---|
| 1 | በክውን ጥበባት የሀሳብ ልዩነቶችንና አንድነቶችን መግለፅ እንደሚቻል ተረድቻለሁ። | | |
| 2 | ጥበብን በመጠቀም የሀሳብ አንድነትና ልዩነትን የተለያዩ የጥበብ አይነቶችን በመጠቀም ማስተላለፍ እንደሚቻል ተረድቻለሁ። | | |
| 3 | ባህላዊ መዚቃን በመጠቀም አንድነትን ማጠናከር እንደሚቻል ተረድቻለሁ። | | |
| 4 | ሀገርን በአንድነት ለመጠበቅ በፉከራና ሽለላ ሀሳብን በማንፀባረቅ ህዝቦችን ወደ አንድ መውሰድ እንደሚቻል ተረድቻለሁ። | | |
| 5 | ሀገርን ለማፍረስ የሀሳብ ልዩነትን በፉከራና ቀረርቶ በማቅረብ ሀገር የምትረበሽበት መልዕክት ሊተላለፍ እንደሚችል አውቂያለሁ። | | |
| 6 | የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ለማህበረሰቡና ለጥበበኛው የሚሰጡትን ጠቀሜታ እገልጻለሁ። | | |
| 7 | ገጸ ባህሪን ተላብሶ መድረክ ላይ መተወን እችላልሁ። | | |

## ማጠቃለያ

በክውን ጥበባት የተለያዩ ሀሳቦችን መግለፅ ይቻላል። ከክውን ጥበባት ውስጥ አንዱ ሙዚቃ የተለያዩ ስሜቶችን ለመግለፅ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ስለዚህ ከባህላዊ ሙዚቃ ክፍሎች ውስጥ ፉከራንና ቀረርቶን በመጠቀም ሀገርን ሚገነቡ፤አንድነትን የሚፈጥሩ፤ መማርና የመስራትን ጠቀሜታ የሚያሳዩ፤ፍቅርን የሚገልፁ፤ ሀገርን የሚያፈርሱ፤ አንድነትን የሚበታትኑና የተለያዩ ፉከራዎችንና ቀረርቶዎችን በማቅረብ ሀሳብን ማስተላለፍ ይቻላል።

የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ከሰው ልጅ የአስተሳሰብ ሁኔታና የስልጣኔ ደረጃ እንዲሁም የዘመን ተለዋዋጭነት በአሰራር ሂደታቸው እየተሻሻለ የመጡ ሲሆኑ የሰው ልጅ ፈጠራዊ የሆኑ ችሎታዎችኑ ከአካባው ጋር በማስተሳሰር ስሜቱን፣ ፍላጎቱን፣ አመለካከቱን፣ እምኑቱን፣ ባህሉን ወዘተ የሚገልጽባቸው ጥበባት ናቸው። እነዚህ ጥበባትም ለማህበረሰቡ በዙ ጠቀሜታዎች የሚሰጡ ሲሆን ከነዚህም መካከል ደስታን ይፈጥራሉ፣ አዕምሮን ያክማሉ፣ ታሪኮችንና መረጃዎችን መዝግበው ያቆያሉ፣ ለጥናትና ምርምር ያገለግላሉ፣ ለመገልገያነት ናለተለያዩ ጉዳዮች ወሳኝ ጠቀሜታዎች አሏቸው።

## የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

በምዕራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በመጽሀፉ ውስጥ የቀረበውን ጹሁፍ ሳትመለከቱ ጥያቄዎቹን መልሱ። ጥያቄዎቹን ሠርታችሁ ከጨረሳችኩ በኋላ ከመምህራችሁ ጋር መልሶቻችሁን አመሳክሩ።

**መመሪያ አንድ፦** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል “እውነት” ስህተት ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ “ሀሰት” በማለት መልስ/ሽ።

---1. የምስል ጥበባት ለማህበረሰቡ የሚሰጡት ጠቀሜታ የላቀ ነው።

---2. ዳንቴል፣ ጥልፍና የስፌት ስራዎች ከእጅ ስራ ውጤቶች ውስጥ ይመደባለ።

---3. በአብዛኛው የዕደ-ጥበብ ወጤቶች ዘመናዊ በሆነ መንገድ የሚሠሩ ናቸው።

---4. የአንድ አገር ስልጣኔና የአስተሳሰብ ደረጃ የሚለካው በታሪክ ውስጥ በየዘመናቱ የተሠሩ ታሪካዊ ቅርሶች መሠረት በማድረግ ነው።

**መመሪያ ሁለት፦** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ።

1. የተለያዩ ቁሳቁሶችንና መሳሪያዎችን በመጠቀም አንድን ምስል ወይም ፅሁፍ ዝርግ ወደሆነ ነገር ማለትም እንደ ወረቀት፣ ጨርቅ፣ የእንጨት ወዘተ የመገልበጥና የማባዛት ሂደት

ሀ. ህትመት ለ. ቀለምቅብ ሐ. ሞዛይክ መ. ሁሉም

2. የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ለህጻናት ከሚሰጡት ጠቀሜታ ውስጥ የሚመደበው

ሀ. እንደ መዝናኛና የደስታ ስሜት ምንጭ በመሆን ያገለግላቸዋል።

ለ. በራስ መተማመን እንዲኖራቸው ያስችሏቸዋል።

ሐ. በማየት የመማር ችሎታቸው እንዲሰፋ ያደርጋል።

መ.ሁሉም

**መመሪያ ሦስት፦** የሚከተሉትን ጥያቄዎች አጭር መልስ በመስጠት መልሱ።

1. የእጅ ስራ ውጤቶችን ዘርዝሩ።
2. የምስል ጥበባትና የእጅ ስራዎች ለማህበረሰቡ የሚጠቅሙትን ማህበራዊ ጠቀሜታ ጻፉ።
3. በምስል ጥበባት ውስጥ የሚካተቱ ዘርፎችን ዘርዝሩ
4. በጥበብ ሀሳብ እንዴት ሊገለፅ እንደሚችል አብራሩ።
5. ሙዚቃን በመጠቀም አንድነትን የሚያጠናክሩ ሀሳቦችን እንዴት ማቅረብ ይቻላል?
6. በሙዚቃ ሀገርን ማፍረስ ወይም መገንባት የሚችሉ ሀሳበችን እንዴት ማደራጀትና ማቅረብ እንችላለን?
7. በፉክራና በቀረርቶ ስሜታችሁን ስትገልፁ የሚሰማችሁን ስሜት ግለጹ።

# ምዕራፍ 5 ሥነ-ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶችና ወቅታዊ ጉዳዮች ጋር ማስተሳሰር

## የምዕራፉ ዓላማዎች፡

### ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፡-

- ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር የሚገናኙባቸውን ሁኔታዎች ትረዳላችሁ።
- በሌሎች ትምህርቶች የተማራችኋቸውና ከሙዚቃ ጋር በማገናኘት መናገር ትችላላችሁ።
- ሙዚቃ ሌሎች ትምህርቶች ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ትተነትናላችሁ።
- መዝሙርን በመጠቀም የትራፊክ አደጋን አስከፊነትና መከላከያ መንገዶችን ታውቃላችሁ።
- መዝሙርና ዳንስን በመጠቀም ኤድስ፣ የትራፊክ አደጋና አበረታች መድሃኒቶች የሚያደርሱትን ጉዳት ትረዳላችሁ።
- መዝሙርና ዳንስን በመጠቀም ኤድስ፣ የትራፊክ አደጋና አበረታች መድሃኒቶችን የመከላከል ክህሎት ታዳብራላችሁ።
- የአየር ንብረት ብክለት መከላከልን መዝሙር፣ ዳንስና ቴያትርን በማቀናጀት ሰርታችሁ ማሳየት ትላላችሁ።
- ጥበባት አንድን ማህበረሰብ ለማስተማርና የሀሳብ ልዩነትንና ተቃርኖን አቻችሎ ለማስኬድ ያላቸውን ሚና ትረዳላችሁ።
- መሰረታዊ የአርማ ምንነትንና አሰራርን ታውቃላችሁ።
- የፖስተር አሰራርን፣ ጠቀሜታን እና የሚያስተላልፉትን መልዕክት ትረዳላችሁ።
- አርማና ፖስተሮችን ታደንቃላችሁ።
- የአርማና የፖስተር ስራዎችን ትሰራላችሁ።

## መግቢያ

በዚህ ምዕራፍ ጥበባት ሀገራዊ የሆኑ አሳሳቢ ጉዳዮችን (ኤች.አይ. ቪ ኤዲስ፣ የትራፊክ አደጋ፣ ሙስና፣ ህገወጥ የህጻናት ዝውውር ወዘተ) ህብረተሰቡን ለማስተማርና ግንዛቤውን ለማሳደግ ያላቸውን ጠቀሜታ፣ የአርማ እና የፖስተር ጽንስ-ሀሳብና መሰረታዊ አሰራሮች የሚኖራቸውን ተግባራዊ ጠቀሜታ ትመለከታላችሁ።

ሙዚቃ፣ ቴያትር፣ ዳንስና ፊልም የሰዎችን ስሜት በተለየ ሁኔታ ማንፀባረቅ የሚያስችሉ ጥበባት ናቸው። እነዚህ ጥበባት ደግሞ ሰዎችን እያዝናኑ የሚያስተምሩና በአዕምሮም አይረሴነታቸው ከፍተኛ ነው። በመሆኑም በሀገራችን ያሉ አንገብጋቢና አሳሳቢ ጉዳዮችን በቀላሉ ህብረተሰቡን ለማስተማርና ግንዛቤውን ለማሳደግ ፋይዳቸው የላቀ ነው።

አርማና ፖስተር ግልጽና ቀላል የሆኑ ማህበረሰቡን የሚወክሉ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉ የግራፊክስ ጥበባት ሲሆኑ የሚያስተላልፉት መልዕክትም የማያሻማና ውስብስብ ያልሆነ ነው።

### የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች

5.1 ሥነ-ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ማስተሳሰር

5.2 ስለትራፊክ አደጋ፣ ኤች.አይ.ቪና ሌሎች ወቅታዊና አሳሳቢ ጉዳዮች ጥበባትን በመጠቀም ማስተማር

5.3 አርማና እና ፖስተር

## 5.1 ሥነ-ጥበባትን ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ማስተሳሰር

### 5.1.1 በሥነ-ጥበባት ተማሪዎች ይዘቶችን በቀላሉ እንዲገነዘቡ ማድረግ

ህጻናት የተለያዩ ትምህርቶችን በመዝሙር፣ በዜማ፣ በስዕልና በቴያትር ጥበባት መማር አንድን ጽንሰ ሀሳብ እየተዝናኑ በቀላሉ እንዲይዙትና ለረጅም ጊዜ እንዲያስታውሱት ይረዳቸዋል።

ሳይንስን፣ ማህበራዊ ሳይንስን፣ ሂሳብን፣ ቋንቋንና የመሳሰሉትን ከስነ-ጥበባት ጋር በማስተሳሰር ማስተማር የህጻናትን የፈጠራ ችሎታን በማሳደግ የመፍጠርና

የመመራመር አቅማቸውን ለማጎልበት፣ የሚፈለገውን ጭብጥ በቀላሉ እየተዝናኑ እንዲገነዘቧቸው፣ መረጃዎችን እንዲይዙባቸውና እንዲያስተላልፉባቸው እንዲሁም ስሜታቸውን በቀላሉ እንዲገልጹ ያስችላል።

በሌላ መልኩ ስነ-ጥበባትን የአዕምሮ ታማሚዎችን በሙዚቃና በስዕል ቴራፒ ከህመማቸው በቀላሉ እንዲታከሙ፣ ህጻናት የግልና የአካባቢ ንጽህናቸውን እንዲጠብቁ፣ እጽዋቶችን እንዲከባከቡ፣ ባህላቸውን ይበልጥ እንዲያውቁና እንዲጠብቁ፣ በስነ-ምግበር የተመሰገኑና ሰውን አክባሪ እንዲሆኑ፣ ሀገራቸውን እንዲወዱ፣ የእጅ ጽህፈታቸው ያማረ እንዲሆን ወዘተ ያስችላቸዋል። በመሆኑም የሚከተሉት መዝሙሮችና ተግባራቶች በመስራት ግንዛቤችሁን ማዳበር ይጠበቅባችኋል።

## መዝሙር፡- ደኑ ለሕይወቴ



ስዕል 1 ደንን የሚያሳይ ፎቶ

አዝ X 2
- አልሁኝ እኔው ለኔ ደኑ ለሕይወቴ
- ብሎም ለወገኔ ለርሃብ መድሃኒቴ

ለሕንፃው ለጎጆው ዋልታና ማገሩ፣

ለእርሻ መሣሪያዎችን ለሞፈር ቀንበሩ፣

ለሸማኔው እቃ ለቅሉ ለንዝርቱ፣

ደን ነው መሰረት ደን ነው ሕይወቱ።


አዝ X 2

ባህርዛፍ ቀረሮ ዝግባውም ጽዱ፣

ለአፈር ጥበቃ ይብዛ በመንገዱ፣

ይሁን ባህላችን ችግኝን ማፍላት፣

አፈር መንከባከብ ውሃ ማጠጣት።




## ጥሩ ሥነ ምግባር

አዝ X 2

ከጥንት ያቆየነው አኩሪ ባህል አለን፣

ጥሩ ሥነ ምግባር ፍቅር እንሰጣለን፣

ቅጥፈት ውሸት ቀርቶ ግለኝነት

ሥራ ክቡር ይሁን ነገን ነው ማየት

አምራች ዜጋ ይሁን ተተኪው ትወልድ

በአሉባልታ ወሬ ሳይወናበድ።

አዝ X 2

መንገድ ማሳየት ነው ጥሩ አመራር

ወዲያ ወዲህ ብለን ሳንደናገር።

ችግር ፈች ዜጋ እንዲለመልም

ምኞታችን ይሁን እሰከዘላለም።

አዝ X 2

ጥሩ ስነምግባር






የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን ከመዝሙሮችን ጋር አስተሳስሮ በሚዘምሩበት ወቅት የአነባብ ስልታቸውንና ትርጉማቸውን በቀላሉ እንዲገነዘቡና እንዲረዱ ያስችላቸዋል። ምሳሌ የሚከተለውን መዝሙር ተመልከቱና በተግባር ዘምሩ።

## መዝሙር ፦Greetings




## The music Man



2. I am a music man
What do you play?
I play the Meleket
Fu, fu, fu, fu
The sound of Meleket
Fu, fu, fu, fu

3. I am a music man
What do you play?
I play the Kebero
Boom, boom, boom, boom
The sound of Kebero
Boom, boom, boom, boom



ሌላው ሙዚቃን ከጤናና ሰውነት ማጎልመሻ ጋር በማስተሳሰር እንቅስቃሴ ማድረግ የተስተካከለ የሰውነት አቋም እንዲኖር፣ አተነፋፈስና የደም ዝውውር እንዲስተካከል ያደርጋል። ለምሳሌ የእርምጃ ምት፣ የመንጠር ምት፣ የመወዛወዝ ምትና የሩጫ ምት በመጠቀም በተግባር እንቅስቃሴዎችን መስራት የውዝዋዜ ችሎታችን ከማሳደጉ ባሻገር ጤናን ለመጠበቅ ይጠቅማል።እንቅስቃሴዎችን ከዚህ ቀጥሎ በቀረቡት ኖታዎች መጫወት ይቻላል።

## የእርምጃ ምት

እርምጃን ከሙዚቃ አንፃር ስንመለከተው የተመጣጠነና በእኩልነት ደረጃ እግርን በስርዓት ከጊዜ አንፃር እየቀያየሩ መንቀሳቀስ ማለት ነው:: የሙዚቃ ኖታዎችን በእግር እንቅስቃሴ በእርምጃ ምት አካሄድ መጠቀም እንችላለን::

**የእርምጃ ምት በሩብ ኖታ ሲገለፅ**



## የሩጫ ምት

ይህን ምት ከእርምጃ በፊጠነ ሁኔታ የምናደርገው የእንቅስቃሴ አይነት ነው::

**የሩጫ ምት በአንድ ስምንተኛ ኖታ ሲገለፅ፦**



በዚህ መንገድ ሌሎች ኖታዎችን እየጻፋችሁ እንቅስቃሴዎችን አድርጉ።

## 5.2 አሳሳቢና ወቅታዊ ጉዳዮችን ጥበባትን ተጠቅሞ ማስተማር

የስነ-ጥበብ ትምህርት የማህበረሰቡን ንቃተ ህሊና ከፍ ለማድረግ አይነተኛ መሳሪያ ሲሆን ሳይጨናነቁ እያዝናኑ ማህበረሰቡን አሳሳቢና ትኩረት ከሚሹ ጉዳዮች ጋር ለማስታዋውቅና ራሱንም እንዲከላከል(እንዲጠብቅ) የሚደረግበት ነው።

በሀገራችንም አንገብጋቢና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉትን ዋናዋናዎቹ ናቸው።

### የትራፊክ አደጋን ማስተማር

የትራፊክ አደጋ በዋነኝነት በአሽከርካሪዎች ሥነ ምግባር ጉድለት፣ ቸልተኝነትና ብቃት ማነስ፣ የተሽከርካሪዎች የቴክኒክ ጉድለት፣ የመንገድ ግንባታ ችግርና የእግረኞች የመንገድ አጠቃቀም ችግር ምክንያት የሚከሰት የእለት ተለት አስደንጋጭ ክስተት ነው። በመሆኑም በሰዎች ህይወት፣ በአካል እና በንብረት ላይ የሚደርሰውን የትራፊክ አደጋን መከላከልና መቀነስ እንዲቻል ሁሉም አሽከርካሪዎችና እግረኞች የትራፊክ ህግን አክብሮ በመንቀሳቀስ የሚጠበቅባቸውን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።ይህ ወቅታዊና አስከፊ የሆኑ ችግርን ለመከላከል ክውን ጥበባትን ተጠቅመን የማህበረሰቡን ግንዛቤ ከፍ ማድረግ እንችላለን።

**መዝሙሩ ጠንቃቃ ተማሪ**

አዝ ጥንቃቄን ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ
ሀሳቡን ሰብስቦ መንገድ ተሻጋሪ

የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል
የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል።

የትራፊክ መብራት ሲያበራ ቀዩን
መኪና ይቆማል ጠብቆ ህጉን

ወንዝ ስንሻገር ግራ ቀኝ አይተን

መጠንቀቅ አለብን ድልድይ ላይ ሆነን


ጥንቃቄን ያውቃል ጠንቃቃ ተማሪ

ሀሳቡን ስብሰቦ በመንገድ ተሸጋሪ

የትራፊክ መብራት ሕጎችንም ያውቃል

የሰዎችን ምክር ሁሌም ያዳምጣል

## ጠንቃቃ ተማሪ



## ኤች. አይ. ቪ/ኤድስን ማስተማር



ስዕል 2 ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ሪባን የሚያሳይ ፎቶ

ኤች.አይ.ቪ /ኤዲስ ማለት በሽታ ተከላካይ የሆኑ ነጭ የደም ሴሎችን የተባሉትን በመቀነስ ቀስ በቀስ የሰውነታችንን በሽታ የመከላከል አቅም አዳክሞ ለሌሎች ተደራራቢ በሽታዎች አሳልፎ የሚሰጥ የሰውን ልጅ ብቻ የሚያጠቃ በሽታ ነው።አንድ ሰው ኤች.አይ.ቪ በደሙ ውስጥ መኖሩ ሊታወቅ የሚችለው በደም ምርመራ ብቻ ነው።በመሆኑም የበሽታውን መተላለፊያ መንገዶችን ማውቅና ተግባራዊ ማደርግ ከእናንተ የሚጠበቅ መሆኑን መረዳት ይኖርባችኋል።

### መዝሙር፦ ኤድስ እንደያጠቃን

አስከፊው በሽታ ኤድስ እንዳያጠቃን

እኛ ተማሪዎች መጠንቀቅ አለብን

በዓለም ዙሪያ ሁሉ ህዝብን የበከለው

በሕክምና ዘርፍ ምንም መፍትሄ ያጣው

የሰዉ ልጆች ጠላት ቀሳፊው ኤድስ ነዉ

እንከላከለው ዛሬ ነገ ሳንል

የሀኪሞችን ምክር ሁሉም በመቀበል


ጥቁር ነጭ የማይመርጥ ድንበር የማያግደዉ

ሕጻን ሽማግሌ ጾታ የማይለየዉ

ሁሉንም ይፈጃል ቀሳፊዉ በሽታ

ከልተጠነቀቁ አይሰጥም ፋታ







## አበረታች መድሃኒት (ዶፒንግ) አስከፊነት ማስተማር



ስዕል 3 አበረታች መዳኒትን የሚያሳይ ፎቶ

አበረታች መድሃኒት ሰው ሰራሽ እና ጊዚያዊ በሆነ መንገድ የጡንቻ እድገትን የሚያነቃቁ፣ ብቃትንና አካላዊ እድገትን የሚያሻሽሉ፣ ህመምንና የድካም ስሜትን የሚቀንሱ የተከለከሉ ንጥረ ነገሮች(መድሃኒቶች) ናቸው።

በአብዛኛው ይህንን የተከለከለ ንጥረነገሮች የሚወስዱት ስፖርተኞች ሲሆኑ ከፍተኛ አፈጻጸም ያላቸውን አትሌቶችም ሆነ ኳስ ተጫዎቾች በሰውነታቸው ውስጥ የተከለከሉ ንጥረነገሮች (መድሃኒቶች) መውሰዳቸውን የዶፒንግ ምርመራ በሀገራችን ጭምር የተለመደ እየሆነ የመጣ ሲሆን ቡዙ ስፖርተኞችም ከጊዜያዊ እግድ እስከ መጨረሻ ውድድር አለም ማሰናበት ድረስ እየተቀጡ ይገኛሉ።ይህንን የሚያደርጉ ስፖርተኞች የእውነተኛና የንጹሃንን ስፖርተኞች ሞራልና ጥቅም የሚጎዳ በመሆኑ እናንተም ይህንን የማይጠቅም ተግባር ማውገዝና ራሳችሁንም ከማንኛቸውም አበረታች መድሃኒት መጠበቅ ይኖርባችኋል።

## ጎጅ ልማዳዊ ድርጊት ማስተማር

ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተሸጋገረ የመጣ፣ ረጅም እድሜን ያስቆጠረና በተለያየ አይነትና ደረጃ በህብረተሰቡ ውስጥ በልማድ እየተፈጸመ ያለ ተግባር ልማዳዊ ድርጊት ይባላል። ልማዳዊ ድርጊቶችን ለህብረተሰቡ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦና በህብረተሰቡ ላይ ከሚያደርሱት ተጽእኖ አንጻር በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። እነሱም ጠቃሚ እና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተብሎ ይከፈላል።

ጠቃሚ ልማዳዊ ድርጊቶች፡- ሳይንስን ወይም ሀይማኖትን መነሻ ያደረጉና ለህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ እሴቶች መልካም ዋጋ ያላቸው ልማዳዊ ድርጊቶች ይባላል። እነዚህ ጠቃሚ ልማዳዊ ድሪጊቶች ከሚባሉት ዉስጥ እድር፣ እቁብ፣ ደቦ፣ ማስታረቅ፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ የተቸገሩትን መርዳት፣ የወለደች ሴትን ማረስ፣ ጡት ማጥባት እንዲሁም ልጅ መንከበከብ፣ መዋደድ፣ መረዳዳት ወዘተ ሲሆኑ ለአገርና ህዝብ ደህንነት፤ ብልጽግናና ማህበራዊ/ባህላዊ/ ትስስር አጋዥ ናቸው።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች፡- ሳይንስ ወይም ሀይማኖታዊ መሰረት ሳይኖራቸው እንዲሁ በልማድ በማንኛውም ማህበረሰብ የሚፈጸሙና በተለያዩ ህብረተብ ክፍሎች ጥቅም ከመስጠት ይልቅ ጉዳት የሚያስከትሉ ተግባራት (ድርጊቶች) ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ይባላሉ። ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የህብረተሰቡን ህብትና ንብረትና ቅርስ የሚያዳክሙ (የሚያባክኑ) ማህበራዊ ግንኙነትን የሚያበላሹና የሚያራርቁ፤ ሰላምና ደህንነትን የሚነሱ ልማዳዊ ድርጊቶች

ናቸው። በሀገራችን በስፋት እየተፈጸሙ ካሉት ዉስጥ የሴት ልጅ ግርዛት፣ የልጅነት ጋብቻ፣ የጠለፋ ጋብቻ፣ እንጥል መቁረጥ፣ ግማ መፈልፈል፣ የተከለከሉ ወይም የተናቁ ስራዎች፣ በወሊድ ዙሪያ የሚፈፀሙ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች እና ጸታዊ ጥቃቶች ወዘተ ይጠቀሳሉ።

### መልመጃ 1

1. ተማሪዎች በአካባቢያችሁ የምትሰሟቸውን ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስና የትራፊክ አደጋ የተመለከቱ ሀሳቦችን ካደራጃችሁ በኋላ ከላይ በሰማችሁትና በዘመራችሁት መዝሙር መሰረት ሌላ መዝሙሮችን በጥንድ ወይም በቡድን በመሆን ሰርታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
2. በመጨረሻም ጓደኞቻችሁ ካቀረባችሁት መዝሙር ምን እንደተረዱና እንዴት ሃሳቡ በቀላሉ መተላለፍ እንደቻለ እንዲገልጹላችሁ በማድረግ ተወያዩ።

## ቴያትርን በመጠቀም የትራፊክ አደጋን፣ የኤች አይ ቪ ኤድስንና የአደንዛዥ እጽን፣ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ወዘተ አስከፊነት ማስተማር

### መልመጃ 2

1. ስለ ትራፊክ አደጋ፣ ኤች አይ ቪ፣ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች ና ስለ ንግድ ግብር ወዘተ...አጫጭር ቴያትሮችን በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ በማቅረብ ውይይት አድርጉባቸው።

## 5.3 አርማ እና ፖስተር

### 5.3.1 አርማ

### መልመጃ 3

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ድርጅቶች እና የፋብሪካ ምርት ውጤቶችን በመዘርዘር ምን አይነት የስዕል ወይም የፊደል ወካይ ምልክት እንዳለቸው ለመምህራችሁ ተናገሩ።

አርማ የአንድን ድርጅት፣ ምርት ወይም የምርት ስም ወዲያውኑ ለመለየት የሚያገለግል በስዕል፣ በፊደላት ወይም ደግሞ በስዕልና በፊደላት ውህደት የተሰራ የእይታ ምልክት ሲሆን ምልክቶቹም በንግድ ምልክት ህግ መሰረት ንብረትነታቸው ለባለቤቶቻቸው የተጠበቀ ነው። ይህ ማለት ሌላ ድርጅት ወይም ፋብሪካ አመሳስሎ ወይም በቀጥታ መጠቀም በህግ ያስጠይቃል ማለት ነው።

የንግድ ምልክቶቹ (አርማው) የድርጅቱን ወይም የፋብሪካውን ዋና መልዕክት ሊያስተላልፍ በሚችል መልኩ መሰራት ይኖርባቸዋል። በጣም ታዋቂ የሆኑ የድርጅት አርማዎች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል ኮካ-ኮላ፣ ናይክ እና አፕል ተጠቃሽ ናቸው።

አርማዎች የሚሰሩበት መንገድ የተለያዩ ሲሆኑ በዚህ ክፍል ደረጃ ሦስት አይነት የአርማ አይነቶችን እናያለን።

## 1. በጽሑፍ ብቻ የሚሰሩ አርማዎች

የድርጅቱ ወይም የኩባንያውን አርማ የምንወክልበት መንገድ ጥቂት ፊደላትን ብቻ በመጠቀም የሚሰራ የአርማ አይነት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን አርማዎችን ተመልከቱ




ስዕል 4 በጽሁፍ ብቻ የተሰሩ የኮካኮላና የዋልታ ቴሊቪዥን አርማዎች

## 2. ስዕላዊ አርማዎች

ስዕልን ብቻ በመጠቀም የድርጅት አሊያም የምርት ስም የሚወከልበት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን አርማዎች ተመልከቱ።



ስዕል 6 የአፕል፣ የናይክና የፔፕሲ አርማዎች በቅደም ተከተል

## 3. የፊደላትና የስዕል ውህደት

ስዕልን ከፊደላት ጋር በማዋሀድ የሚሰራ የአርማ አይነት ነው። ለምሳሌ የሚከተሉትን አርማዎች ተመልከቱ።




ስዕል 5 የፊደላትና የስዕል ውህደትን የሚያሳይ

### አርማ በሚሰራበት ወቅት

- ለመለየት በጣም ቀላል መሆን ይኖርበታል።
- በመጠን ሲያንሱም ሆነ ሲተልቁ የሚያስተላልፉት መልዕክት ግልጽ መሆን አለበት።

☞ የምንጠቀማቸው ቀለማትና ፊደላት ግልጽና ውስን መሆን ይኖርባቸዋል።

## አርማ በሚሰራበት ጊዜ መሰረታዊ ደረጃዎች

1. አርማው እንዲገልጽ የሚፈለገውን መልዕክትና እሴት መረዳት።
2. በአርማው ላይ ለመግለጽ የታሰበውን መልዕክት በእርሳስ በተለያዩ መጠኖችና ቅርጾች እየቀያየሩ መለማመድ።
3. ከተሰሩት ልምምዶች የተሻለ የሚገልጸውን መምረጥና ተደጋጋሚ ልምምድ በማድረግ ማሳደግ።
4. የተሻለና ከስዕሉ ጋር ሊዛመድ በሚችል መልክ ፊደላቶችን ማስቀምጥ።
6.ለመረጥናቸው ስዕሎች ሆነ ፊደላት ተስማሚና ምቹ የሆኑ ቀለማትን መጠቀም እንዲሁም የመጨረሻውን የአርማ ወላይ ዲዛይን ማስቀመጥ።

### መልመጃ 4

1. ከላይ በተመለከታችሁት አሰራር መሰረት በአካባቢያችሁ አርማ የሚያስፈልጋቸውን የንግድ አይነቶች ወይም ተቋማትን በመለየት በራሳችሁ ፈጠራ ወላይ ምልክቶችን በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።

## 5.3.2 ፖስተር

### መልመጃ 5

1. በአካባቢያችሁ የቤት ግድግዳ፣ አደባባይ፣ ትምህርት ቤት፣ ፊልም ቤት፣ መስሪያ ቤት ላይ ወዘተ የተለጠፉና የተሰቀለ ጹሁፍና ስዕል ያለባቸው ወረቀቶችና ሽራዎች አይታችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ ለመምህራችሁ ግለጹ።

ፖስተር ቀላልና በብዙ ነገሮች ያልተጨናነቀ፣ በቀላሉ ለመረዳት የሚቻልና ከተለጠፈበት ወይም ከተሰቀለበት ቦታ ሆኖ በተወሰነ ርቀት ላይ በግልጽ ሊነበብ የሚችል ትምህርት ሰጭና የተለያዩ ወቅታዊ ክንውኖችን በስዕላዊ መግለጫ ለማህበረሰቡ የሚቀርብበትና መልዕክት የሚተላለፍበት ጥበብ ነው። ለምሳሌ የፊልም ቤት ፖስተሮች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ ፖስተሮች፣ የንግድ ድርጅቶች ፖስተሮች፣ የስፖርት ፖስተሮች፣ የጤና ፖስተሮች ወዘተ።

ፖስተሮች የሚሰሩበት ቀለማት በቁጥራቸው የተመጠኑና የተመልካችን ዓይን የሚስቡ መሆን የሚገባቸው ሲሆን በጥንቃቄም የተመረጠ መሆን አለባቸው። በፖስተሩ ላይ ከተሰራው ሥዕል ጋር አብሮ የሚሄድ ጽሑፍ በሚጻፍበት ጊዜ ጽሁፉ በመጠኑም በአጻጻፍ ስልቱም የተመረጠና የተዋበ መሆን ይገባዋል። የሚጻፉት ፊደሎችም በጣም የበዙ ሳይሆኑ ከሥዕሉ ጋር በተመጣጠነ ሁኔታ በሩቅ ተነባቢ መሆን ይገባዋል። የአቀማመጥ ቅርጻቸውና ቀለማቸው የሥዕሉን ሁኔታ የሚቃረን ሳይሆን ከሥዕሉ ጋር የሚዛመድና ውህደት የሚፈጥር መሆን ይኖርባቸዋል።

## የፖስተር ጠቀሜታዎች

አሳሳቢና ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ለምሳሌ ሙስና፣ ኤች.አይ.ቪ ኤዲስ፣ ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶች፣ ህገወጥ የህጻናት ዝውውር፣ አደንዣዥ እጾችን መጠቀም ወዘተ ማህበረሰቡ እንዲከላከላቸው ለማስተማር።

የሀገርን ባህል፣ አለባበስ፣ ቅርሶች፣ ታሪካዊ ቦታዎች ወዘተ ለማህበረሰቡና ለውጭው ኗሪ ለማስተዋወቅና የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ተጠቃሚ ለማድረግ።


የንግድ ድርጅቶችን ምርት ለማስተዋወቅናተጠቃሚውን ለመሳብ እንዲሁም ወቅታዊ የሆኑ ጉዳዮችን በስፋት ለማዳረስ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

**በዚህ የክፍል ደረጃ የፖስተር አሰራር ቅደም ተከተል**

ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት መረዳትና በምን አይነት መንገድ መቅረብ እንዳለበት ማሰላሰል።


- ☞ በአዕምሮ ውስጥ የተሰላሰለውን በወረቀት ላይ በተለያዩ ዲዛይን እየደጋገሙ መለማመድና የተሻለውን መምረጥ።
- ☞ በሚፈለገው መስሪያ ሰሌዳ ላይ የጽሁፍ ቦታ ለይቶ ማስቀመጥና ስዕሉን መስራት።
- ☞ ለዕይታ ተስማሚና አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ የማያሳድሩ ቀለማትን መምረጥና በተፈላጊው ቦታ በጥንቃቄ መቀባት።
- ☞ የተቀባው ቀለም ከደረቀ ቡኃላ በጥሩ የአጻጻፍ ስልት ፊደላትን መጻፍ።

የተለያዩ የፖስተር አይነቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ መካከል የንግድ ማስታወቂያ ፖስተሮች፣ የጤና ጉዳይ ፖስተሮች፣ የቅስቀሳ ፖስተሮች ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው።












ስዕል 7 ከጤና ጋር የተያያዙ ፖስተሮች




ስዕል 8 የንግድ ፖስተሮች

**ስለ ወቅታዊ ሁኔታ ፖስተሮችን መስራት**

### መልመጃ 6

1. የፖስተር አሰራርን በተገነዘባችሁበት መንገድ የኤች.አይ.ቪ ኤዲስ አስከፊነትን በስዕልና በፊደላት ቅንብር ቀላል ፖስተር ሰርታችሁ በማቅረብ የሰራችሁትን ፖስተር አስመልክቶ ማብራሪያ ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ ተናገሩ።
2. ጎጅ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል ለህብረተሰቡ ማስተማሪያ የሚሆን በሥዕልና በፊደላት ቅንብር ፖስተር በመስራት ለመምህራችሁና ለክፍል ጓደኞቻችሁ ማብራሪያ ስጡ።

ከመምህራችሁ ጋር በመሆን ከሰራችኃቸው ስራዎች የተሻሉትን በመምረጥ በትምህርት ቤታችሁ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች ላይ በመለጠፍ የሌሎች ተማሪዎችን ግንዛቤ አዳብሩ።

# የማገናዘቢያ ነጥቦች

የምዕራፍ አራት ትምህርት የተጠናቀቀ ሲሆን በትምህርቱ ውስጥ የተጠቀሱትን ነጥቦች መጨበጥ አለመጨበጣችሁን ለማረጋገጥ ይህ ማመሳከሪያ ቀርቦላችኃል። የተነሳውን ነጥብ የምታውቁት ከሆነ የራይት ምልክት ነጥቡን የማታውቁት ከሆነ ኤክስ ምልክት ማድረግና እንደገና ተመልሳቹህ ትምህርቱን ከልሱ።

| ተ.ቁ | ነጥቦች | አሳክቻለሁ | አላሳካሁም |
|---|---|---|---|
| 1 | መዝሙርን በመጠቀም የትራፊክ አደጋን አስከፊነትና መከላከያ መንገዶችን ተረድቻለሁ። | | |
| 2 | መዝሙርና ዳንስን በመጠቀም ኤድስ መተላለፊያ መንገዱንና የማይተላለፍበትን መንገድ ተረድቻለሁ። | | |
| 3 | በመዝሙር፣ በዳንስና በቴያትር የቀረቡ መልዕክቶችን በመረዳት የአየር ንብረት ብክለትን መከላከል እንዳለብኝ ተረድቻለሁ። | | |
| 4 | አደንዛዥ መድሀኒት መጠቀም በጤና ላይና በስፖርታዊ ውድድር ላይ ችግር እንደሚያመጣ በመዝሙር ተረድቻለሁ | | |
| 5 | የአርማ አይነቶችን መናገር እችላለሁ። | | |
| 6 | ቀላል አርማዎችን መስራት እችላለሁ። | | |
| 7 | የፖስተር ምንነትን መግለጽ እችላለሁ። | | |
| 8 | የፖስተር ጠሜታን ማብራራት እችላለሁ። | | |
| 9 | በማንኛውም አርዕስተ ጉዳይ ላይ ቀላል ፖስተሮችን ማዘጋጀት እችላለሁ። | | |

# ማጠቃለያ

ሙዚቃ ከተለያዩ የትምህርት አይነቶች ጋር በተለያዩ መንገዶች አንደሚገናኝ የተመለከት ሲሆን የግንኙነት ሁኔታው ስንመለከት ደግሞ እንደየ ትምህርት አይነቶች የሚለያይ ነው። ሙዚቃ ከሌሎች ትምህርቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ከመዝሙር፣ ከኖታዎች አነባበብና በተዝናኖት ከመማር ጋር የሚገናኙ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪ ሙዚቃ ወቅታዊ ጉዳዮችን በተማሪዎችም ሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ በቀላሉ ለማስረጽ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

በሀገራን ኢትዮጵያ በአንገብጋቢነት የሚጠቀሱና ልንከላከላቸው የሚገባቸውን እንደ ትራፊክ አደጋ፣ ኤች አይ ቪ ኤድስና ሌሎች ጉዳዮችን በመዝሙር በመጠቀም መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪም እንደ አበረታች መድሃኒቶች፣ ህገ ወጥ የሰዎች ዝውውርና የመሳሰሉትን ወቅታዊ ጉዳዮችን ለማስተማርና በቀላሉ እያዝናኑ መልዕክትን ለማስተላለፍ ያለው ጠቀሜታ በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም።

አርማ ከግራፊክስ አርት ጥበብ ውስጥ አንዱ ሲሆን በጹሁፍ፣ በስዕል ወይም ደግም በሁለቱ ቅንብር የሚሰራ አንድን ተቋም፣ ድርጅትና የምርት ውጤቶች ለመለየት የሚያስችል ወካይ ምልክት ሲሆን ይሄም ውስብስብ ሳይሆን ግልጽና ቀለል ባለ ሁኔታ የሚሰራ ነው። ፖስተር የራሱ የሆነ የአሰራር ዘዴ ያለው መልዕክት በማያሻማ ሁኔታ በተመጠነ ሥዕልና ጹሁፍ ተዘጋጅቶ የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማዳበር የሚሰራ ጥበብ ነው። የአርማና የፖስተር ጥበቦች በጥልቀት ማሰብን የሚጠይቁ ሲሆን ተደጋጋሚ ልምምዶችን በማድረግ ውጤታማ መሆን እንደሚቻል መረዳት ያስፈልጋል።

# የምዕራፍ ማጠቃለያ መልመጃ

በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት መሠረት በማድረግ የሚከተሉት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል። በመጽሀፉ ውስጥ የቀረበውን ጹሁፍ ሳትመለከቱ ጥያቄዎቹን መልሱ። ጥያቄዎቹን ሠርታችሁ ከጨረሳችኩ በኋላ ከመምራችሁ ጋር መልሶቻችሁን አመሳክሩ።

**መመሪያ አንድ፡-** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን አባባል "እውነት" ስህተት ሀሳብ የያዘውን አባባል ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሽ።

--------1. ፖስተርና አርማ በመሰረታዊነት ልዩነት የላቸውም።

--------2. አርማ የሚዘጋጀው በምስል ብቻ ነው።

--------3. የፖስተር ስራ የኪነ-ጽህፈት ክህሎትን የሚጠይቅ ጥበብ ነው።

--------4. አርማና ፖስተርን አካባቢያዊ በሆኑ ማቴሪያሎችን ተጠቅሞ መስራት ይቻላል።

--------5. አንድ ድርጅት የሌላን ድርጅት አርማ አስመስሎ የመጠቀም መብት አለው።

**መመሪያ ሁለት፡-** ትክክለኛውን ሃሳብ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ።

1. ፖስተሮች

   ሀ. መልዕክት አስተላላፊ ናቸው።

   ለ. ብዛት ባላቸው ቀለማቶች የሚሰሩ ናቸው።

   ሐ. በምስል ብቻ የሚዘጋጁ ናቸው።

   መ. ሁሉም

2. የፖስተር ጠቀሜታን የሚገልጸው

   ሀ. ወቅታዊና አሳሳቢ የሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮችን ለመዋጋትና ለመከላከል።

   ለ. ባህልና ታሪክን ለማስተዋወቅ።

   ሐ. የንግድ ምርትን ለማህበረሰቡ ለማስተዋወቅ።

   መ. ሁሉም

3. የፖለቲካ ፓርቲዎች የምረጡኝ ቅስቀሳ ለማድረግ የሚጠቀሙበት

ሀ. ፖስተር ለ. አርማ ሐ. ሀናለ

**መመሪያ ሦስት፡-** የሚከተለትን ጥያቄዎች አጭር መልስ በመስጠት መልሱ።

1. ፖስተር እንዴት ይዘጋጃል።
2. የፖስተር ጠቀሜታዎችን ጻፉ።
3. የአርማ አይነቶችን ጻፉ።

**መመሪያ አራት፡** የሚከተሉትን ጥያቄዎች በሚገባ ካነበባችሁ በኃላ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ።

1. በዚህ መጽሐፍ ስር ያልተጠቀሱ የትምህርት አይነቶችን ከሙዚቃ ጋር የሚገናኙ የትምህርት አይነቶችን በመጥቀስ እንዴት እንደሚገናኙ አስረዱ።
2. በልጅነታችሁ እየዘመራችሁ የተማራችሁት የምታስታውሱትን የትምህርት አይነት በመዝሙር በክፍል ውስጥ አሳዩ።
3. የትራፊክ አደጋ አስከፊነትን ግጥም በመፃፍ በክፍል ውስጥ አቅርቡ።
4. ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ አስከፊነት ግጥምና ዜማ በመድረስ ሙዚቃ አቅርቡ።
5. አደንዛዥ እፅ የሚያስከትለውን ጉዳት ፖስተር ስርታችሁ በክፍል ውስጥ አሳዩ።
6. በአካባቢያችሁ የምታገኙትን የተቋም ወይም የንግድ ድርጅት አርማ ስሩ።

## ዋቢ መጽሀፍት

1.The right way to learn to draw----------A.GLAD-STONE JACKSON

2.ብርሀኑ አሻግሬ ስነ-ጥበብ ማስተማሪያ መጽሀፍ 5ኛ እና 6ኛ ክፍል 2005ዓ.ም አዲስ አበባ

3.Ashenafi, Kebede “The Music of Ethiopia: its Development and Cultural Settings. PhD

4. Musical Production”.In Yearbook for Traditional Music, Vol. 16, pp. 19-33, 1984.

5. በቀለ መኮነን ስነ-ጥበብ ማስተማሪያ መጽሀፍ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል 2005 ዓ.ም አዲስ አበባ